NEPS

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሥራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ

ኅዳር 2002
አዲስ አበባ

NEPS

Created with
nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

1.1 የህዝብ መጠን፣ አወቃቀርና ባህርያት ........................................................................................ 1

1.2 የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የስራ ስምሪትና ድህነት ቅነሳ ያላቸው ቁርኙነት ................................. 2

1.3 የስራ ስምሪት ባህሪያትና ክስተቶች ......................................................................................................5

1.3.1 የሰው ኃይል አቅርቦትና ተሳትፎ መጠን ገፅታ ...................................................................................... 5

1.3.2 የሥራ ስምሪት ሁኔታና ያለበት ደረጃ ........................................................................ 7

1.3.3 የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ ተቋማት ያሉበት ሁኔታ ..................................................................................10

## ክፍል ሁለት

## 2. የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ

2.1. የስራ ስምሪት ፖሊሲ አስፈላጊነት ...........................................................................................12

2.2 የስራ ስምሪት ፖሊሲ ዓላማዎች .................................................................................................13

2.3 ፖሊሲና ስትራቴጂ .........................................................................................................................13

2.3.1 ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘት ......................................................................14

2.3.2 የስራ ዕድል ፈጠራ (የኢኮኖሚው የሰው ኃይል ፍላጎት) ..........................................................16

2.3.2.1 የግሉን ዘርፍ ልማት በማፋጠን የስራ ዕድልን መፍጠር …………..………...........16

2.3.2.2 የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር የግሉን ዘርፍ ልማት የማፋጠን ስትራቴጂ …………..….19

2.3.2.3 የመንግሥት ሴክተር ሥራ ስምሪትን (Public sector employment) ውጤታማነት እና ብቃት ማሳደ.………………………………………..…………….…25

2.3.3 የሰው ኃይል ምርታማነትን ማሻሻል (የሰው ኃይል አቅርቦትን ማሻሻል) ...............................27

2.3.3.1 የግብርና ዘርፍ የሰው ኃይል ምርታማነትን ማሳደግ ……………………………….....27

2.3.3.2 ከግብርና ውጪ የግል ዘርፍ እና መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ ምርታማነት ማሳደግ …….35

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

2.3.4 የሥራ ገበያ ተቋማትን ማጠናከር፣ የአሰሪና ሠራተኛ አስተዳደርን ማሻሻል እና የሥራ ገበያ አገልግሎትን ማስፋፋት ....................................................................................39

2.3.4.1 የአሰሪና ሠራተኛ አስተዳደር እና የሥራ ገበያ ተቋማትን የማጠናከር ስትራቴጂዎች ..........................................................................40

2.3.5 የመድብለ ዘርፍ ጉዳዮች፡ የፖሊሲ እርምጃ አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች................. 44

2.3.5.1 የስነ ሕዝብ አወቃቀር ሽግግር (Demographic transition) ማምጣት ...............44

2.3.5.2 ግሎባላይዜሽን የሚያስከትላቸውን የስራ ስምሪት ፈታኝ ሁኔታዎች መግታት....... 44

2.3.5.3 የተዘዋዋሪ ሠራተኞችን መብት ማስከበር ............................................45

2.3.5.4 ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን መግታት .....................................46

2.3.5.5 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የስራ ቦታ .....................................................48

2.3.5.6 ሥርዓተ-ጾታን በስራ ፈጠራ ውስጥ ማካተት ..........................................48

2.3.5.7 የወጣቶችን የስራ ስምሪት ማስፋፋት .................................................49

2.3.5.8 ለአካል ጉዳተኞች የስራ ዕድሎችን ማመቻቸት .......................................50

2.3.5.9 የሕጻናት ጉልበት ስራን መከላከል ...................................................51

2.3.5.10 የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ .........................................52

## ክፍል ሶስት

## 3. የፖሊሲ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ ተቋማዊ ማዕቀፍ

3.1 የፖሊሲ ትግበራ ተቋማዊ ማዕቀፍ ....................................................................54

3.2 የፖሊሲ ውጤቶች ክትትልና ግምገማ ................................................................56

3.3 የፖሊሲ ትግበራ ስልት ...........................................................................59

3.4 የፖሊሲ ክለሳ ..................................................................................60

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የህዝብ መጠን፣ አወቃቀርና ባህርያት

በ1.1 ሚሊዮን ስኩዌር ሜትር የቆዳ ስፋትና 73.9 ሚሊዮን (50.46% ወንድ እና 49.54% ሴት) በሚገመት የሕዝብ ብዛት (በ2001)[1] ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ካላት ናይጀሪያ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ትገኛለች፡፡ ባላት የቆዳ ስፋት ስትለካ ደግሞ በዘጠነኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ግንቦት 1999 bተደረገው አገር-አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትንበያ መሰረት 84 በመቶ ያህሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር የአገሪቱ ክፍል የሚኖር ሲሆን ዋነኛ መተዳደሪያውም በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት እየቀነሰ የመሄድ አዝማሚያ ቢያሳይም (ከ1970ዎቹ እስከ 1982 መጀመሪያ 2.73 በመቶ እና ከ1982 አጋማሽ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ 2.6 በመቶ) አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ካለው የስነ ሕዝብ አወቃቀር አንፃር ከፍተኛ የሚባል ነው፡፡

በግንቦት 1999 በተደረገው አገር-አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትንበያ ውጤት መሰረት አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ያለ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 45 በመቶ የሚሆኑት ከ15 ዓመት የዕድሜ ክልል በታች የሚገኙ ናቸው፡፡ ትንበያው እንደሚያሳየውም አምራች የሰው ኃይል ተብሎ የሚቆጠረው (15-64 ዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎች) ሕዝብ ብዛት 52 በመቶ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በ2001 የተረጂነት ምጣኔም (የተረጂዎች መጠን በ100 አምራች ሰዎች) 93 በመቶ ሲገመት የህፃናትና አረጋውያን ጥገኞች ቁጥርም እንደቅደም ተከተሉ 87 እና 6 በመቶ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ከፍተኛ የጥገኝነት ምጣኔ መኖር ከፍተኛ የሕዝባዊ አገልግሎት ፍላጎት፣ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥር፣ ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢና ዝቅተኛ መጠን ያለው ሀገራዊ ቁጠባና የሀብት ክምችት እንዲኖር በማድረግ ለድህነት መከሰትና መባባስ ዓይነተኛ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት መራቆት እንዲፈጠርና እንዲባባስ በማድረግ በዘላቂታዊ ልማት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና ያሳድራል፡፡

ለከፍተኛ ሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ መኖር ዋነኛ ምክንያት ከፍተኛ የወሊድ መጠንና አነስተኛ ወይም እየቀነሰ የሚሄድ የሞት መጠን ጥምረት መኖር ነው፡፡ በ1998 ዓ.ም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የተከናወነው የዲሞግራፊክና የጤና ዳሰሳ እንደሚያመላክተው ምንም እንኳን የወሊድ ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ቢሄድም አሁንም ግን ከፍተኛ እንደሆነ

---

[1] በ1999 ዓ.ም በተካሔደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 73.9 ሚሊዮን ነበር፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ነው፡፡ በተመሳሳይ ዓመት የአንዲት ኢትዮጵያዊ እናት የወሊድ ምጣኔ በአማካይ 5.4 (6.0 በገጠርና 2.4 በከተማ) ልጆች ሲሆን በአፍሪካ ደረጃ ካለው በአንድ እናት አማካይ 5.1 ልጆች የወሊድ መጠንም ሆነ ከዓለም አማካይ 2.7 ልጆች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነው፡፡ በሌላ በኩል እጅግ አበረታች የሆነ የወሊድ መጠን መቀነስ በከተሞች አካባቢ የሚታይ ሲሆን በተለይም የአዲስ አበባ የወሊድ መጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ ካለው የ5.4 የወሊድ መጠን ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ በአንድ እናት የ2.0 ልጆች የወሊድ መጠን በታች ሆኖ ይገኛል፡፡

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መንግስት ለሚያደርገው የድህነት ቅነሳ ጥረት ትልቅ ፈተና እንደሆነ ከታወቀ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በመጨረሻ ዓመት የትግበራ ዘመኑ ላይ በሚገኘው የአምስት ዓመቱ የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ውስጥ ከተካተቱት ዋና ዋና ስትራቴጂዎች መካከል አንዱ የስነ ሕዝብ ዕድገትን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ከተቀመጡ ቁልፍ ተግባራት መካከልም በልማት ዕቅዱ ማጠናቀቂያ ዓመት (2002 ዓ.ም) ላይ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን በማስፋፋት የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ሽፋን ከነበረበት 15 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማድረስ ነው፡፡ በ2000 ዓ.ም የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ሽፋን 33 በመቶ ደርሷል፡፡ ተይዞ የነበረውም ዕቅድ የወሊድ መጠንን በ1997 ዓ.ም ከነበረበት የ5.4 ልጆች በአንድ እናት ቁጥር በ2000 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 4 ልጆች በአንድ እናት ለማውረድ ነበር፡፡ ጥናቶች የሚያመላክቱት የወሊድ ምጣኔው በሚፈለገው መጠን እንዳልቀነሰና አሁንም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ ያልተሟላ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት እንዳለ ነው፡፡

## 1.2 የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የስራ ስምሪትና ድህነት ቅነሳ ያላቸው ቁርኝት

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የተሸጋገረ ሲሆን ይህንንም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ጠብቆ እየተጓዘ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ባለፉት 6 ዓመታት (እስከ 2001 ዓ.ም) በአማካይ የ11.1 በመቶ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (GDP) ተመዝግቧል፡፡ በእነዚህ ዓመታትም ሁለት ያልተለመዱ መሠረታዊ ለውጦች በኢኮኖሚው አጠቃላይ ገፅታ ላይ ተስተውለዋል፡፡ እነዚህም ወደ ከፍተኛ ዕድገት ደረጃ የተደረገ ሽግግርና የዕድገት ምንጮች ስብጥር ናቸው፡፡ በቀደሙት ዓመታት (እስከ 1995 ዓ.ም) የኢኮኖሚ ዕድገቱ የዝናብ ስርጭትን ተከትሎ በሚታዩ ከግብርናው ዘርፍ ምርት መቀነስና/መዋዥቅ ጋር ተያይዘው በሚከሰቱት የንግድ ሚዛን መዛባት የተነሳ የሚዋዥቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ኢኮኖሚው በከፍተኛ ሁኔታ በማንሰራራት ዘላቂ የሆነ ዕድገት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ ይህም ዕድገት በኮንስትራክሽን፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ንግድና ቱሪዝም፣ባንክና ኢንሹራንስ እንዲሁም በሪል ስቴት ዘርፍ በታዩት ከፍተኛ እንቅስቃሴዎች ታግዟል፡፡ የግንባታውን ዘርፍ እንቅስቃሴ በማነቃቃትና በማፋጠን ረገድ በተለይም መንግስት በስፋት ያካሄዳቸው ለወደፊት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሰረተ ልማት አውታሮች (እንደ መንገድ፣ የገጠር መሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ጨምሮ፣የስልክ ፣መብራትና መስኖ ልማት ወዘተ) ግንባታ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ መስፋፋት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ከፍተኛ ድርቅ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የተከሰተበትን የ1995 ዓ.ም እንኳን ከግምት ውስጥ አስገብተን በቅርብ ዓመታት ያለውን የዕድገት እንቅስቃሴ ብንመለከት አማካይ ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (GDP) መጠን 9.5 በመቶ ሲሆን (የድርቅ ወቅትን ሳይጨምር ከተመዘገበው አማካይ ዕድገት መጠን 2 በመቶ በማነስ) እስከ 2001 ዓ.ም በነበሩት ስድስት ዓመታት ውስጥ ደግሞ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት 6.5 በመቶ ነበር፡፡ ይህን በተመለከተ ሠንጠረዥ 1.1 ላይ ያለውን ይመልከቱ፡፡

በድርቅ ዓመታት ከነበረው ተፅዕኖ የማገገሚያ ጊዜን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተደረገውን ማስተካከያ ጨምሮ እንኳን የነበረው የዕድገት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና አበረታች ነው፡፡ በግንቦት 2000 ዓ.ም የወጣው የዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (IMF) አንቀፅ አራት ሪፖርትም ኢትዮጵያን ነዳጅና የከበሩ ማዕድናት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ከሌላቸው የአፍሪካ ሀገራት መካከል ፈጣን ዕድገት በማስመዝገብ ቀዳሚነቱን እንደያዘች አረጋግጧል፡፡ ይህ የዕድገት መጠንም ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ነዋሪዎችን መጠን በግማሽ ለመቀነስ የተያዘውን ግብ ለማሳካት ከሚፈለገው አማካይ የ7 በመቶ ዕድገት መጠን የላቀ ነው፡፡ እስከ 2001 በነበሩት ስድስት ዓመታት የሀገር ውስጥ ምርት የ8 በመቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢም በሰማኒያዎቹ አጋማሽ ላይ ከነበረበት 120 የአሜሪካን ዶላር በ2001 ወደ 223 የአሜሪካን ዶላር ደርሷል፡፡[2]

**ሠንጠረዥ 1.1 የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) አማካይ ዓመታዊ ለውጥ በመቶኛ (%)**

| ዝርዝር | ዓመታዊ ለውጥ በመቶኛ | | | | | | | የድርቅ ዓመትን ሳይጨምር የስድስቱ ዓመታት አማካይ | የድርቅ ዓመታትን ያጠቃለለ አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1995 | 1996 | 1997 | 1998 | 1999 | 2000 | 2001 | | |
| ግብርናና ግብርና ተዛማጅ | -10.5 | 16.9 | 13.5 | 10.9 | 9.4 | 7.5 | 6.0 | 11.6 | 8.0 |
| ኢንዱስትሪ | 6.5 | 11.6 | 9.4 | 10.2 | 10.2 | 10.4 | 9.2 | 10.4 | 9.7 |
| *ማምረቻ* | 0.8 | 6.6 | 12.8 | 10.6 | 8.3 | 7.1 | | 9.1 | 7.7 |
| *ግንባታ/ኮንስትራክሽን* | 13.6 | 19.5 | 7.5 | 10.5 | 10.9 | 11.3 | | 11.9 | 12.2 |
| አገልግሎት | 6.0 | 6.3 | 12.8 | 13.3 | 14.3 | 17 | 15.0 | 12.7 | 11.6 |
| *የማከፋፈል አገልግሎት* | 5.5 | 6.4 | 14.7 | 14.2 | 16 | 15.2 | 15.0 | 13.3 | 12.0 |
| *ሌሎች አገልግሎቶች* | 6.5 | 6.1 | 10.9 | 12.5 | 13.1 | 14.2 | 15.0 | 11.4 | 10.6 |
| GDP እ.አ.አ በ1999/00 ዋጋ መሰረት | -2.1 | 11.7 | 12.6 | 11.6 | 11.4 | 11.6 | 10.2 | 11.8 | 9.5 |
| የተጣራ ነፍስ-ወከፍ | -4.9 | 10.5 | 8.8 | 7.8 | 8.2 | 8.3 | 7.6 | 8.7 | 6.5 |
| አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት | 10.9 | 7.3 | 6.1 | 10.6 | 15.8 | 25.3 | 36.4 | 12.7 | 13.0 |

*ማስታወሻ- 1995 ዓ.ም የድርቅ ወቅት ነበር፡፡*

*ምንጭ- ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፡፡*

---

[2] የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (1997 ዓ.ም)፡- የአምስት ዓመት የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ከኢኮኖሚ ዕድገት እንቅስቃሴ ጋር ከተያያዙት ዓላማዎች አንዱ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (MDGs) ከሆኑት መካከል ግብ አንድን ማሳካት ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት ከምንጠቀምባቸው ቁልፍ መንገዶች አንዱ ደግሞ በቂ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ የስራ ዕድሎችን መፍጠር ነው። የኢትዮጵያ የድህነት ማጥፋት አጀንዳ ማዕከል ያደረገው ግብርናና ገጠር ልማትን መሰረት ያደረገ አቀጣጫ በመከተል መሰረተ ሰፊ ልማት ማምጣት ላይ ነው። በ1997 ዓ.ም የወጣውን የቤተሰብ ገቢና ወጪ ፍጆታ ዳሰሳ ሪፖርት መሠረት በማድረግ በተካሄደ ጥናት የኢኮኖሚ ዕድገቱ በከፍተኛ ደረጃ ለድህነት ቅነሳ አስተዋፅኦ (በተለይም በገጠር) ማድረጉን ያመለክታል። የአንድ ኢትዮጵያዊ አማካይ  የተጣራ የነፍስ-ወከፍ ወጪ በ1988 ዓ.ም ከነበረበት መጠን በአማካይ 50 በመቶ ያህል ጨምሯል። ይህም በገጠር አካባቢዎች የድህነት ክስተት በ1988 ከነበረበት 47.5 በመቶ በ1997 ወደ 39.3 በመቶ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አስተዋፅኦ አድርጓል። በተመሳሳይ ሁኔታም የድህነት ክፍተት በ1988 ከነበረበት 13.4 በመቶ በ1997 ወደ 8.7 በመቶ በመውረድ የድህነት ጥልቀት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን ሲያመላክት በሌላ በኩል ደግሞ በከተሞች አካባቢ የድህነት ክስተት በ1988 ከነበረበት 33 በመቶ በ1997 ወደ 35.1 በመቶ ሲጨምር የድህነት ጥልቀቱ ደግሞ ከ9.9 በመቶ ወደ 7.7 በመቶ ቀንሷል።

ሌሎች ነገሮች እንደተጠበቁ ሆነው እስካሁን የተገኘውን የኢኮኖሚ ዕድገት በዘላቂነት ማስቀጠል የኢትዮጵያን የልማት ግቦች ለማሳካት ቁልፍ መሳሪያ ነው። አሁን በስፋት እየተካሄደ ያለውን ዕድገት ሊያፋጥኑ የሚችሉ እንደ መንገድ፣ ስልክ (ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ጨምሮ)፣ መብራት (የገጠር መብራት ማዳረስን ጨምሮ) እና የመስኖ  ልማትን የማስፋፋት ስራዎች የተመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት በቀጣይ ዓመታት በዘላቂነት ለማስቀጠል ያለሙ ናቸው።

የኢኮኖሚ ዕድገት በስራ ፈጠራ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ስንመለከት ከኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ይልቅ የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንቅስቃሴ ሂደት ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ነው። ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለስራ ፈጠራና ድህነት ቅነሳ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ካስፈለገ መሰረተ ሰፊና ደሀ-ተኮር ሊሆን ይገባዋል። የኢትዮጵያ ዕድገትም ይህንን የተከተለ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው 84 በመቶ የሚሆነው የሀገራችን ሕዝብ በገጠር የሚኖርና ኑሮውም የተመሰረተው በግብርና ላይ ነው። በ1997 ዓ.ም የገጠር የድህነት መጠን በ1992 ዓ.ም ከነበረበት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱ በራሱ የኢኮኖሚ ዕድገቱ መጠነ ሰፊና ደሀ-ተኮር ለመሆኑ አመላካች ነው። በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው የግሉን ዘርፍ ልማት በማሳደግና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ትኩረት በመስጠት በተለይም ከቤቶች ልማትና ከሙያና ቴክኒክ ሙያ ስልጠና ጋር በማቀናጀት የስራ ዕድል መፍጠር በልማት ዕቅዱ ውስጥ ዋነኛ ስትራቴጂዎች ናቸው። ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ሶስት ዓመታት ከተማ ተኮር የሆኑ የተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እየተነደፉ ስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ተነሳሽነትና ጥረት በስፋት እየታየ ነው። የዘመናዊው ኢንዱስትሪ ዘርፍ ጠባብ መሰረት ስራ በመፍጠር ረገድ ያለው አቅም አናሳ መሆን ከገጠር ወደ ከተማ ከሚደረግ ፍልሰት ጋር ተዳምሮ ለከተሞች ድህነት መባባስ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። በተጨማሪም መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የሚፈጠሩት የስራ ዕድሎች እንኳን እንደ ተገቢና አመቺ ስራ አለመታየታቸው ሌላው ምክንያት ነው፡፡

የኢትዮጵያን የሥራ ገበያ አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ከፍተኛና ፈጣን የሰው ኃይል አቅርቦት ዕድገት መኖሩ ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሚሆነው ሀገሪቱ ካላት የሥነ-ሕዝብ አወቃቀር የተነሳ የሰው ኃይል ዕድገቱ ከአጠቃላይ ሕዝብ ዕድገቱ በጣም ፈጣን መሆኑ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በየዓመቱ አምራች የሆነውን ኃይል ለቀው ከሚወጡት አረጋውያን ይልቅ በርካታ ከ15 ዓመት በታች የነበሩ ሰዎች አምራች ኃይሉን ይቀላቀላሉ፡፡

## 1.3 የስራ ስምሪት ባህሪያትና ክስተቶች

በሀገራችን ውስጥ በኢኮኖሚ ዕድገትና በስራ ስምሪት መካከል ያለውን ግንኙነት በአግባቡ መረዳት እንዳይቻል እንቅፋት ከሚሆኑት ነገሮች መካከል መጠነ ሰፊ፣ በሚገባ የተዘረዘረና ወጥ የሆነ ጊዜን የተከተለ መረጃ አለመኖር ዋነኛው ነው፡፡ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ከ1960ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በ1977፣ 1987 እና 1997 ዓ.ም በተደረጉ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የታገዙ የተለያየ መጠን ያላቸውን የሰው ኃይል ዳሰሳና ተያያዥ ጥናቶችን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡

ነገር ግን የእነዚህ ዳሰሳ ጥናቶች ውጤት ተመራማሪዎችን አሳማኝ በሆነ መልኩ የሥራ ገበያውን ዕድገትና ለውጥ በትክክል ለመከታተል አላስቻላቸውም ነበር፡፡ በቅርቡም በ1992 እና 1997 ዓ.ም በተካሄዱት የሰው ኃይል ዳሰሳ ጥናቶች መጠነ ሰፊ የሆነ ወካይ የገጠርና ከተማ አቀፍ የሰው ኃይል መረጃዎችን ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ዓመታዊ የስራ ስምሪት ዳሰሳ ጥናቶች በጥቅምት 1996፣ መጋቢት 1997 እና እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ መጋቢት 1999 ዓ.ም ላይ አካሂዷል፡፡ የእነዚህ የዳሰሳ ጥናቶች ሽፋንም በከተሞች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በዋነኛነት ስራ አጥነት የገጠር ሳይሆን የከተማ ችግር መሆኑ ስለታመነበት ነው፡፡ የከተማ ስራ አጥነት በተለይም የወጣቱ ክፍል ስራ አጥነት መንግስትን ሲያሳስበው የቆየና አሁንም እያሳሰበው ያለ ጉዳይ ነው፡፡

### 1.3.1 የሰው ኃይል አቅርቦትና ተሳትፎ መጠን ገፅታ

ባለፉት አስርት ዓመታት ሀገሪቷ የነበራት የሰው ኃይል አቅርቦት በሁለት እጥፍ ጨምሯል፡፡ የሰው ኃይል አቅርቦቱ በ1976 ዓ.ም ከነበረበት 14.7 ሚሊዮን በ1987 ወደ 26.5 ሚሊዮን እና በ1997 ወደ 33 ሚሊዮን አድጓል፡፡ በዚህ ዓይነት ፍጥነት (በየዓመቱ 4.4 በመቶ) ለሚያድግ የሰው ኃይል የስራ ስምሪት ዕድል መፍጠር ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈታኝ እየሆነ መጥቷል፡፡ የሰው ኃይል የስራ ተሳትፎ መጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ በ1992 ከነበረበት የ77 በመቶ በ1997 ወደ 82 በመቶ ከፍ በማለት መጠነኛ ለውጥ አምጥቷል፡፡ የገጠር የሰው ኃይል የስራ ተሳትፎ ከ79 በመቶ ወደ 85 በመቶ ሲጨምር የከተማ የሰው ኃይል የስራ ተሳትፎ ደግሞ ከ63 በመቶ ወደ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

65 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ የከተማ የሰው ኃይል የስራ ተሳትፎ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች[3] ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስራ ተሳትፎ መጠን ከሴቶች ይልቅ የወንዶች እና እንዲሁም ከአዋቂዎች ይልቅ የወጣቶች የስራ ተሳትፎ ድርሻ የጎላ ነው፡፡ የሴቶች የስራ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ በወጥነት በመጨመር በ1992 ከነበረበት 65 በመቶ በ1997 ወደ 75 በመቶ ሲደርስ የወንዶች የስራ ተሳትፎ ብዙም ለውጥ ሳያሳይ ባለበት የ88 በመቶ ድርሻ ላይ ነው፡፡ የሴቶች የስራ ተሳትፎ መጠን በከተሞች ከ54 በመቶ ወደ 58 በመቶ በገጠር ደግሞ ከ69 በመቶ ወደ 78 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ15 እስከ 24 ዓመት ባለው ዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች የስራ ተሳትፎ መጠን በ1992 ከነበረበት የ72 በመቶ ድርሻ በ1997 ወደ 75 በመቶ ደርሷል፡፡ በገጠር የሚገኙ ወጣቶች የተሳትፎ መጠን (በ1992 ዓ.ም 77.5 በመቶ እና በ1997 ዓ.ም 82.1 በመቶ) በከተማ ከሚገኙ ወጣቶች የስራ ተሳትፎ መጠን (በ1992 ዓ.ም 45.4 በመቶ እና በ1997 ዓ.ም 50.5 በመቶ) ጋር ሲነፃፀር እጅግ የጎላ ልዩነት አለው፡፡ ለዚህ የጎላ ልዩነት ተጠቃሽ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ በከተማ ውስጥ ያለው የትምህርት ተሳትፎ ሲሆን ይህም ከገጠር ይልቅ በከተማ የተሻለ የትምህርት ተሳትፎ እንዳለ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በገጠሮች አካባቢ ከፍተኛ የድህነት መጠን መኖርም ምናልባት ለአብዛኛው በገጠር የሚገኝ ወጣት የስራ ተሳትፎ መጨመር ሁነኛ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡

**ሠንጠረዥ 1.2 የሰው ኃይል ተሳትፎ መጠን በዕድሜና ፆታ (በመቶኛ)**

| | 1992 ዓ.ም | | | 1997 ዓ.ም | | | ለውጥ (%) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | በከተማ | በገጠር | ድምር | በከተማ | በገጠር | ድምር | በከተማ | በገጠር |
| ዕድሜ 15+ | | | | | | | | | |
| ጠቅላላ | 76.74 | 62.53 | 79.01 | 81.52 | 64.69 | 85.11 | 6.24 | 3.47 | 7.71 |
| ወንድ | 87.77 | 73.66 | 90.68 | 88.96 | 72.44 | 91.91 | 1.35 | -1.66 | 1.36 |
| ሴት | 65.93 | 53.54 | 68.71 | 74.72 | 57.99 | 78.08 | 13.33 | 8.31 | 13.64 |
| ዕድሜ 15-24 | | | | | | | | | |
| ጠቅላላ | 71.80 | 45.38 | 77.51 | 75.32 | 50.47 | 82.10 | 4.91 | 11.21 | 5.92 |
| ወንድ | 79.46 | 50.51 | 85.11 | 80.76 | 51.63 | 88.13 | 1.64 | 2.22 | 3.55 |
| ሴት | 70.12 | 41.52 | 70.12 | 71.10 | 49.67 | 76.72 | 1.40 | 19.62 | 9.41 |
| ዕድሜ 25+ | | | | | | | | | |
| ጠቅላላ | 79.26 | 74.18 | 79.50 | 84.68 | 74.79 | 86.63 | 6.85 | 0.82 | 8.97 |
| ወንድ | 92.16 | 88.10 | 92.82 | 93.19 | 87.53 | 94.24 | 1.12 | -0.64 | 1.53 |
| ሴት | 66.94 | 62.15 | 67.75 | 77.02 | 64.04 | 79.21 | 15.06 | 3.05 | 16.91 |

ምንጭ፦ ከ1992 እና 1997 የሰው ኃይል ዳሰሳ ጥናት መረጃን መሰረት አድርጎ የተሰላ፡፡

[3] ለምሳሌ በኬንያ 85 በመቶ እና በዩጋንዳ 79 በመቶ (ምንጭ፡- Leibbrandt and Mlatsheni, 2004 ሲሆኑ ይህም የተወሰደው ከ World Bank 2007 ላይ ነው፡፡)

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

### 1.3.2 የሥራ ስምሪት ሁኔታና ያለበት ደረጃ

በቅርብ ዓመታት ከሚታዩት መሻሻሎች በስተቀር ስራ አጥነትና[4] በከፊል ስራ-ጥነት በኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም ዋነኛ ማህበራዊ ችግሮች እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ ለዚህም ዋነኛ ተጠቃሽ ምክንያት የሚሆነው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ብሎም ከፍተኛ የሰው ኃይል ዕድገት መኖሩና የሀገሪቱ ኢንዱስትሪ መሠረት ጠባብ መሆን እየጨመረ ለሚሄደው የሰው ኃይል በቂ የስራ ዕድል መፍጠር አለመቻሉ ነው፡፡ የሀገሪቱ የስራ አጥ ሕዝብ ቁጥር መጠን በ1992 ዓ.ም ከነበረበት 3.6 በመቶ በ1997 ዓ.ም ወደ 2.6 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ የስራ አጥነት (ያለ ምንም ስራ መቀመጥ) በገጠር አካባቢዎች የተለመደ አይደለም፡፡ ከፊል ሥራ-ጥነት ማለትም በስራ ላይ ተሰማርቶ ከሚገኘው የሰው ኃይል ውስጥ ተጨማሪ ስራ መስራት የሚችሉ ሰዎች መኖር በስፋት በገጠር የሚታይ ችግር ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ማለት ችግሩ በከተማ አይታይም ማለት አይደለም፡፡ እንደ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሰው ኃይል ዳሰሳ ጥናት የከፊል ስራ-አጥ ቁጥር በወጣት ወንዶችና መካከለኛ ዕድሜ ባላቸው አዋቂዎች መካከል ከፍተኛ ሲሆን እንዲሁም ከሴቶች ይልቅ በወንዶች መካከል በከተማም ሆነ በገጠር ከፍተኛ ነው፡፡ የከፊል ስራ-አጥነት መጠን በተለይም በከተማ ከሚገኙ ዕድሜያቸው ከ25 እስከ 39 ዓመት በሚገመተው ወጣት ወንዶች ውስጥ በ1997 ዓ.ም ከ20 እስከ 25 በመቶ የሚገመት ድርሻ ነበረው፡፡ የከፊል ሥራ-አጥነት መጠን ከ40 ዓመት ዕድሜ በኂላ ባሉ አዋቂዎች ዘንድ በከተማም ሆነ በገጠር እየቀነሰ መሄዱ ታይቷል፡፡

ከፍተኛ የሆነ የከተማ ስራ አጥነት መጠን አሁንም መሠረታዊ የፖሊሲ ፈተና ነው፡፡ እንደ 1998 ዓ.ም የከተማ ስራ ስምሪትና ስራ አጥነት ዳሰሳ ጥናት በከተማ ውስጥ ያለው የስራ አጥነት መጠን እየቀነሰ በመሄድ በ1995 ዓ.ም ከነበረበት የ26.2 በመቶ በ1996 ዓ.ም ወደ 22.9 በመቶና እንዲሁም በ1998 ይበልጥ ዝቅ በማለት 16.7 በመቶ ደርሷል፡፡ በእነዚህ ዓመታት የሴቶች የስራ አጥነት መጠን ከወንዶች የስራ አጥነት መጠን ጋር ሲነፃፀር በ1995 ዓ.ም 35.2 በመቶ፣ በ1996 ዓ.ም 30.6 በመቶና በ1998 ዓ.ም 22.1 በመቶ በመሆን በመደበኛነት ብልጫ ሲኖረው በተመሳሳይ ዓመት የወንዶች የስራ አጥነት መጠን እንደቅደም ተከተሉ የ17.6 በመቶ፣ 15.8 በመቶና 11.5 በመቶ ነበር፡፡ በከተማ የሚታውን ሥራ አጥነት በተለይም የወጣቱን ሥራ አጥነት አሳሳቢነት መንግስት በመረዳቱ በቅርብ የተደረጉ የስራ አጥነት ክትትል ፕሮግራሞች ሽፋን የስራ አጥነት ችግሮች ከገጠር ይልቅ በከተማ የሚታዩ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በከተሞች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡

ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት በኢትዮጵያ ውስጥ በከተሞች ለሚታየው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ዋነኛ ድርሻ እንዳለው ይታመናል፡፡ ለዚህ ፍልሰት መጨመር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ የመጣው የእርሻ መሬት እጥረትና የግብርና ምርታማነት መቀነስ መሠረታዊ ምክንያቶች

[4] ሥራ አጥነት የሚለካው የሚከተሉትን ሶስት መመዘኛዎችን በጣምራ በመውሰድ ነው፡፡ እነርሱም ስራ የሌለው፣ ለስራ የተዘጋጀ እና ስራ በመፈለግ ላይ ያለ ናቸው፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

እንደሆኑ አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል የሚያስማማ ሀሳብ ነው፡፡ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት ወቅታዊ ባህርይ ያለውና በሁሉም አካባቢዎች የሚታይ ነው፡፡

አብዛኛው በሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል የሚገኘው በግብርና የኢኮኖሚ ዘርፍ ሲሆን፣ ይሄው የሰው ኃይል የሚያገኘው ገቢ ዝቅተኛ በመሆኑ ከድህነት እንዲወጣ አላስቻለውም፡፡ በርካታ ቁጥር ያለው የሰው ኃይልም ከፊል ሥራአጥነት፣ ዝቅተኛ ገቢና አነስተኛ ተቋማዊ ድጋፍና ጥበቃ መገለጫዎቹ በሆኑት መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ እነዚህ ዕውነታዎች ሠራተኛ የሆኑ ድሆች (Working poor) ችግር እንዲኖር የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር ድህነት ገሀድ ከሆነ ስራ አጥነት (open unemployment) ይልቅ ያነሰ ገቢ በማግኘት ምክንያት የሚከሰት እንዲሆን ያደርጉታል፡፡

በ1997 ዓ.ም የተካሄደውን የከተማ የስራ ስምሪትና ስራ አጥነት ዳሰሳ ጥናት ዋቢ አድርገን በስራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል ብዛት በዋና ዋና የስራ ዘርፎች ከፋፍለን ስናይ ወደ ሶስት አራተኛ የሚጠጋው በከተማ ውስጥ በስራ ላይ የተሰማራው ሕዝብ በአብዛኛው ተቀራራቢ ድርሻ ባላቸው ሶስት ወሳኝ የስራ ዘርፎች ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ እነዚህም አገልግሎቶች የሱቅና ገበያ ንግድ ሰራተኞች (25.5 በመቶ)፣ በአነስተኛ ስራዎች የተሰማሩ (23.6 በመቶ) እና የዕደ ጥበባትና ተያያዥ ስራዎች የተሰማሩ (22.1 በመቶ) ናቸው፡፡ ፕሮፌሽናል ባለሙያዎች የቴክኒክና ረዳት ፕሮፌሽናሎችን ጨምሮ 10 በመቶ ያህሉን በስራ ላይ የተሰማራ የሰው ኃይል ድርሻ ሲይዙ በህግ አውጪነት የሚሰሩና ከፍተኛ ኃላፊዎች 2.5 በመቶ የሚሆን አነስተኛውን የከተማ ተቀጣሪዎች ድርሻ ይዘዋል፡፡

በሥራ ላይ የተሰማራውን ሕዝብ በዋና ዋና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከፋፍለን ስንመለከት ደግሞ እንደሚጠበቀው አብዛኛው በከተማ ስራ ላይ የተሰማራው ሰው በጅምላና ችርቻሮ ንግድ ስራና በአምራች ኢንዱስትሪዎች ሲሆን እንደቅደም ተከተላቸው የ22.7 በመቶና 15.3 በመቶ ድርሻ ይይዛሉ፡፡ በሌላ በኩል ሆቴልና ሬስቶራንት፣ የሕዝብ አስተዳደር፣የቤት ውስጥ ስራ፣ ግብርና፣ትምህርት፣ ጤና፣ ማህበራዊ ሥራ እና ሌሎች ሕዝባዊ፣ ባህላዊና የግል እንቅስቃሴዎች ከ7 እስከ 10 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ እንደ ማዕድንና ቁፋሮ፣ የገንዘብ ተቋማት፣መብራት፣ ነዳጅና ውሀ አቅርቦት እንዲሁም ሪል ስቴት ዘርፎች የስራ ስምሪት በመፍጠር በኩል አነስተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡

በተመሳሳይም በዳሰሳ ጥናት ውጤቱ እንደተመለከተው በከተማ ስራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል በቅጥር ሁኔታ (በሁሉም የከተማ ደረጃ) ከፋፍለን በምንመለከትበት ጊዜ አብዛኛው ሰው ራሱን በራሱ ቀጥሮ የሚያሰራ (42 በመቶ) ሲሆን በመንግስት ስራ ላይ የተሰማራው 19 በመቶ እና በግል ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩት 18 በመቶ ይሆናሉ፡፡ በሠንጠረዥ 1.3 ላይ እንደሚታየው በቅጥር ስራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል ከአጠቃላይ የሠራተኛ ሕዝብ ቁጥር 45 በመቶውን ያጠቃልላል፡፡ በቅጥር ስራ የተሰማራው የሰው ኃይል የመንግስት ተቋማት፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የግል ተቋማትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም የቤት ውስጥ ተቀጣሪዎችን ያካትታል፡፡ ክፍያ በሌለው የቤተሰብ ስራ ላይ የተሰማሩትም (10 በመቶ) ሰፊ ድርሻ አላቸው፡፡ የዳሰሳ ጥናቱ ውጤትም ቅጥር የስራ ስምሪት (Wage employment) በአብዛኛው

Created with
nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በወንዶች የተያዘ መሆኑን ያመላክታል። ከግል ድርጅት ተቀጣሪዎች መካከል የወንዶቹ መጠን ከሴት ተቀጣሪዎች መጠን በሁለት እጥፍ ይልቃል። በተመሳሳይም በመንግስት ተቋማት በስራ ላይ የተሰማሩ ወንዶች መጠን ከሴቶቹ መጠን በ75 በመቶ ይበልጣል። በሌላ መልኩ በአመዛኙ ከወንዶች ይልቅ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በቤት ውስጥ ቅጥርና ክፍያ በሌለው የቤተሰብ ስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በራሳቸው ስራ ላይ የተሰማሩት ሴቶች መጠን ከወንዶቹ ከፍ ያለ ነው።

በ1997 ዓ.ም በተካሄደው የከተማ ስራ ስምሪትና ስራ አጥነት ዳሰሳ ጥናት መሠረት በስራ ላይ የተሰማሩ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ቁጥር 3,839,274 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 55 በመቶ የሚሆነውን የያዙት ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት 45 በመቶዎቹ ደግሞ ሴቶች ናቸው። በሠንጠረዥ 1.3 ላይ እንደሚታየው በሚያዝያ 1998 ዓ.ም በመንግስት ተቋማት ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ቁጥር በጥቅምት 1996 ዓ.ም ከነበረበት መጠን በ26 በመቶ ሲያድግ በሕዝባዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች ቁጥር ደግሞ በ8 በመቶ ጨምሯል። በተመሳሳይ ወቅት በግል ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩ ሠራተኞች ቁጥር በ57 በመቶ ሲያድግ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩት ሠራተኞች ቁጥር 35 በመቶ አድጓል። በቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት ደግሞ 13 በመቶ ቀንሷል። ራሳቸውን ቀጥረው የሚያስተዳድሩ፣ ክፍያ በሌለው የቤተሰብ ስራ የሚሰሩ፣ ቀጣሪዎችና ሌሎች ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ሰዎች ቁጥር በቅደም ተከተል የ34፣57፣ 71 እና 170 በመቶ ጭማሪ በተመሳሳይ ወቅት አስመዝግቧል። ይህም እንደሚያሳየው ከፍተኛ የሆነ ዕድገት የተስተዋለው በሕብረት ስራ ማህበራት አባላትና መሰሎቻቸው (170%) በመቀጠልም በአሠሪዎች(71)፣ በግል ተቋማት ተቀጣሪዎችና (87) ራሳቸውን ቀጥረው በሚያሰሩ (57) እና በመንግስት ሠራተኞች ነው።

**ሠንጠረዥ1.3: ጠቅላላ በስራ ላይ የተሰማራው ሕዝብ ድርሻ (ከ10ዓመት ዕድሜና በላይ) በስራ ስምሪት ሁኔታ፣ዓ.ምና በ(%)**

| የስራ ስምሪት ሁኔታ | ጥቅምት 1996 | | | ሚያዝያ 1996 | | | ሚያዝያ 1998 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ቅጥር ስራ ስምሪት | 51 | 44 | 48 | 52 | 46 | 49 | 48 | 42 | 45 |
| *የመንግስት* | 22 | 14 | 18 | 23 | 15 | 19 | 20 | 13 | 17 |
| *የመንግስት ድርጅቶች* | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 |
| *የግል ድርጅት* | 20 | 10 | 16 | 21 | 11 | 17 | 22 | 14 | 18 |
| *መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት* | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 |
| *የቤት ውስጥ* | 5 | 17 | 10 | 4 | 17 | 9 | 2 | 12 | 6 |
| ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር | 40 | 45 | 42 | 40 | 43 | 41 | 40 | 43 | 42 |
| ክፍያ የሌለው የቤተሰብ ስራ | 7 | 11 | 9 | 5 | 10 | 7 | 8 | 13 | 10 |
| አሠሪዎች | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 |
| ሌሎች (የሕብረት ስራ ማህበራት፣በትምህርት ላይ ያሉ፣ ወዘተ) | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 |
| ጠቅላላ ድምር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

*ምንጭ- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣* [5]

---

[5] በዳሰሳ ጥናቱ መረጃና በዚህ ሠንጠረዥ መካከል የሚታየው የመረጃ ቁጥሮች ልዩነት የመጣው በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ያለውን መጠን በመውሰድ መጠኑን ለማጠቃለል ሲባል በተሰራው ስሌት ምክንያት ነው።

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት 50 ከመቶ በላይ የሚሆነው የከተሞች ስራ ስምሪት የሚሸፈነው መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ነው፡፡ በ1994 ዓ.ም በተከናወነው መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ ዳሰሳ ጥናት መሠረት በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች ብዛት 997,380 ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 799,353 (80 በመቶ) ያህሉ የዘርፉ አንቀሳቃሾች ሲሆኑ የተቀሩት 198,027 (20 በመቶ) ተቀጣሪዎች ናቸው፡፡ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ በአንቀሳቃሽነትም ሆነ በዘርፉ ተቀጣሪነት ሴቶች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ በዘርፉ ከተሰማሩት ሰዎች፣ አንቀሳቃሾችና ተቀጣሪዎች ውስጥ የሴቶች ድርሻ እንደቅደም ተከተሉ 60፣59 እና 65 በመቶ ነው፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ ከመደበኛው ዘርፍ ጋር ያለው መስተጋብር ዝቅተኛ ነው፡፡ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ መካከልም ያለው ትስስርና መደጋገፍ ይህ ነው የሚባል አይደለም፡፡

**ሠንጠረዥ 1.4: መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩ ሰዎች ቁጥር በፆታ መደብ (በ1994 ዓ.ም)**

| ፆታ | በዘርፉ ውስጥ የተሰማሩ | | ተቀጣሪዎች | | በስራው ላይ የተሰማሩት አጠቃላይ ሰዎች ቁጥር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | መቶኛ(%) | ቁጥር | መቶኛ(%) | ቁጥር | መቶኛ(%) |
| ወንድ | 328,808 | 41.13 | 70,276 | 35.49 | 399,084 | 40.01 |
| ሴት | 470,545 | 58.87 | 127,751 | 64.51 | 598,296 | 59.99 |
| ድምር | 799,353 | 100.00 | 198,027 | 100.00 | 997,380 | 100.00 |

*ምንጭ- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣*

### 1.3.3 የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ ተቋማት ያሉበት ሁኔታ

የሥራ ገበያ ተቋማት በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት፣ በሰው ኃይል አገልግሎት አቅርቦትና ጥበቃ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የሥራ ገበያ ተቋማት በአጠቃላይ ደካማ በሆነ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ድክመት ባህርያት ከሚነፀባረቁባቸው ነገሮች መካከል ደካማ የቁጥጥር ስርዓት እና በተቋማት መካከል (የሠራተኛ እና አሰሪ ማህበራት) ያለው የማህበራዊ ምክክር ባህል እጥረት መኖር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ያሉት የቁጥጥር ስርዓት መሳሪያዎችና ተቋማትም ብዙውን ጊዜ መደበኛና የቅጥር ስራ ስምሪትን ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እስካሁን ድረስ መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍና ራሳቸውን ቀጥረው የሚያሰሩትን ለማካተት የተደረገ ምንም ዓይነት ጥረት የለም፡፡ ይህም ሁኔታ ከሥራ ገበያው ሚዛናዊ አለመሆን ጋር ተዳምሮ የስራ ጥበቃና ዋስትና ማነስና የማህበራዊ ምክክር ባህል አለመዳበር ዝቅተኛ ጥራት ያለው የሥራ ገበያ አገልግሎትን ሊያስከትል ችሏል፡፡

ኢትዮጵያ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነቶችን በማሻሻል የስራ ስምሪት መልካም ውጤቶች ለማሳደግ የተለያዩ አዋጆችን ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ ከነዚህም ውስጥ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 377/1996)፣ የሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 632/2001) እና የአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት መብት አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 568/2000) በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የሚኖሩትን ግንኙነቶች የሚገዙ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከስራ ስምሪት ጋር የተያያዙ ወደ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

20 የሚሆኑ የዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት (ILO) ኮንቬንሽኖችን ኢትዮጵያ ተቀብላ በማፅደቅ የሀገሪቱ ሕግ አካል አድራጋለች፡፡

በጥቅሉ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የሠራተኛ ማህበራት በአቅም ደረጃ ደካማ ቢሆኑም በመንግስት የልማት ድርጅቶች ያሉት የሠራተኛ ማህበራት በግል ድርጅቶች ውስጥ ከሚገኙ የሰራተኛ ማህበራት የተሻለ ጥንካሬ ያላቸው ናቸው፡፡ የግል ድርጅት አሠሪዎች ሠራተኞቻቸው በማህበራት እንዲደራጁ በማድረግ በኩል በስፋት ድጋፍ ሲያደርጉ አይታይም፡፡ ይልቁንም በግል ድርጅት የሚሰሩ ሠራተኞች የሠራተኛ ማህበራት በማቋቋም መሠረታዊ መብታቸውን ለማስከበር በሚያደርጉት ጥረት ከአሠሪዎቻቸው ተቃውሞ ይገጥማቸዋል፡፡ ይህን መሰሉ በዘመናት የዳበረ አሉታዊ አመለካከት የሠራተኛ ማህበራት የድርጅቶቻቸውን ምርታማነትና ትርፋማነት በማሳደግ ረገድ የሚኖራቸውን ሚና በአግባቡ እንዳይወጡ አግዷቸዋል፡፡ በጥቅሉ አሁን ተግባራዊ እየሆነ ያለው የሠራተኛ ማህበራት እንቅስቃሴ ለመብት ጥስት ተጋላጭ በሆኑ ስራዎች ከተሰማሩት (ማለትም መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ፣በቤት ውስጥ ስራና ተዘዋዋሪ ሠራተኞች) ይልቅ በመደበኛው ኢኮኖሚ ውስጥ በተሰማሩት የማተኮር ዝንባሌ አለው፡፡

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

# ክፍል ሁለት
# የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ

## 2.1. የስራ ስምሪት ፖሊሲ አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ በ20 ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የያዘችውን ሀገራዊ ራዕይ ዕውን ለማድረግ ለሀገሪቱ ዜጎች ሰፊ የስራ ስምሪት ዕድል መፍጠር ከአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ስምንት ዋነኛ ምሰሶዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የስራ ስምሪት፣ ገቢና የሥራ ገበያ ድህነትን በመቀነስና የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠን ረገድ ያለው የማይናቅ ሚና የሚታወቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል የስራ ስምሪት ዕድሎች መኖርና የእነዚህን ባህርያቸውን መረዳት የኢኮኖሚ ዕድገት በድህነት ቅነሳ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ለመምራት የሚያስችል ዋነኛ መሣሪያ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከድህነት ቅነሳ ብሎም ድህነትን ከማጥፋት ጋር የሚያገናኝ ድልድይ የስራ ስምሪት ዕድል ፈጠራ ነው፡፡ የስራ ስምሪት ዕድሎችና ባህርያት ድሀ-ተኮር የሆነ ዕድገት ለማምጣት ዓይነተኛ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ከሌሎች የምርት ግብዓቶች (ለምሳሌ ካፒታል) በተሻለ ሰፊ የሰው ኃይል ሀብት ላላቸው ታዳጊ ሀገራት ውጤታማ የሆነ የሰው ኃይል አጠቃቀም መኖር ዕድገትን ለማፋጠንም ሆነ ዕድገትን ድሀ-ተኮር በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና አለው፡፡ የስራ ስምሪትም ሆነ ከስራ ሥምሪቱ የሚገኝ ገቢ (ከራስ ስራ ወይም ከቅጥር ስራ) የኢኮኖሚ ዕድገትን ከድህነት ቅነሳ ጋር የሚያገናኝ ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡ ዘላቂ ድህነት ቅነሳ የማምጣት ጥረት የሥራ ስምሪት ዕድገት ይዘትና ስርጭት የሚያስገኘውን ጥቅም የተሻለ ዕድል ያላገኙ ወገኖችን በተለይም ወጣቱና የሙያ ስልጠና የሌላቸው ሰዎች ባካተተ መልኩ ከጅማሮው ማስፋት ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የስራ ዕድል የማግኘት አቅም ልዩነት የተመጣጠነ የስራ ስምሪት ስርጭት በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲኖር በማድረግ ረገድ ስጋት የሚያሳድር ነው፡፡ ይህንን ስጋት የማስወገድ ጥረትም የተቀናጀ የሥራ ገበያ አቅርቦትና ፍላጎት ጎኖችን ያማከለ የፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ተቋማዊ ለውጦችን ዕውን ማድረግን ይጠይቃል፡፡

የስራ ዕድል ፈጠራ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከድህነት ቅነሳ ጋር በማገናኘት ረገድ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችለው የስራ ገበያውን የሚወስኑ ባህርያትን ተገቢ በሆነ መልኩ በመምራት በጎ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የፖሊሲና ስትራቴጂ መሳሪያዎች በመጠቀም መምራት ሲቻል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ካላት ከፍተኛ የድህነት መጠንና ፈጣን የሆነ የሕዝብና የሰው ኃይል ዕድገት አንፃር የኢኮኖሚ ዕድገት ከድህነትና ከስራ ዕድል ፈጠራ ጋር ያለውን ግንኙነት ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ የምትመራበትና ደሀ-ተኮር የሆነ የጋራ ዕድገት እንዲኖር የምታደርግበት መንገድ ያስፈልጋታል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ስራ አጥነት፣ ከፊል ሥራ አጥነትና የሚሰሩ ደሀዎች መኖር

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የተለመደ በሆነበት ሁኔታ የገቢ ድህነት ችግር ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት በዘዴ ካልተከናወነ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ስራ አጥነትንና በከፊል ሥራ-አጥነት ውስጥ የሚገኙ ደሀዎችን ችግር ለማቃለል ወይም ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት የሰው ኃይል ፍላጎትን፣ አቅርቦትንና የሥራ ገበያውን የሚመሩ ተቋማትን በተቀናጀ መልኩ የሚያሳትፍ የፖሊሲ ማዕቀፍ በመፍጠር መከናወን ይኖርበታል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ የተዘጋጀውም የስራ ስምሪትን በማሻሻል ለድህነት ቅነሳ ሊያበረክቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በማለም ነው፡፡

## 2.2 የስራ ስምሪት ፖሊሲ ዓላማዎች

የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሶስት መሰረታዊ ጎኖች ሲኖሩት እነሱም ማህበራዊ ዋስትናን ማሳደግ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማፋጠንና ፖለቲካዊ መረጋጋትን ማስፈን ናቸው፡፡

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለድህነት ቅነሳ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የሚለካው በኢኮኖሚው ውስጥ መፈጠር በሚችለው የስራ ስምሪት ዕድልና ጥራት ነው፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገትን ደሀ-ተኮርና የጋራ እንዲሆን ለማስቻል የሥራ ገበያ አቅርቦት፣ፍላጎትና ተቋማዊ ጎኖችን ያገናዘበ የስራ ስምሪት ፖሊሲ በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ትልቅ ዕገዛ አለው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ አንዱ ዋነኛ ዓላማ ውጤታማና አመቺ የስራ ስምሪት ሁኔታዎች እንዲኖሩ የሚያስችል መመሪያዎችን በማውጣትና ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ማህበራዊ ደህንነትና እኩልነትን የሚያረጋግጥ ፍትሃዊነት ያለው ድህነት ቅነሳ ማበረታታት ነው፡፡

**የኢኮኖሚ ዕድገት፡-** የስራ ስምሪት ፖሊሲው ድህነትን በመቀነስ የኑሮ ደህንነትን በማረጋገጥ ረገድ ካለው ማህበራዊ ዓላማ በተጨማሪ የሀገሪቱ ዋነኛ ሀብት የሆነውን ሰፊ የሰው ኃይል በአግባቡ ምርታማ በሆነ ስራ ላይ በማሰማራት ቀጣይና ዘላቂ የሆነ ፈጣን ዕድገትና ልማት የማምጣት ኢኮኖሚያዊ ዓላማ አለው፡፡

**ፖለቲካዊ መረጋጋት፡-** በርካታ በስራ ላይ ያልተሰማራ የሰው ኃይል በሚኖርበት ጊዜ በተለይም ይህ በስራ ላይ ያልተሰማራ የሰው ኃይል ቁጥር በወጣትና በተማረው ሕብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ከሆነ ለፖለቲካዊና ማህበራዊ አለመረጋጋት ዋነኛ ምንጭ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የስራ ስምሪት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የሥራ ገበያ አቅርቦትና ፍላጎት ጎኖችን ያገናዘቡ የስራ ስምሪት ዕድሎችን በመፍጠር መሰል አለመረጋጋቶችን እንዳይከሰቱ ለማድረግ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

## 2.3 ፖሊሲና ስትራቴጂ

መደበኛ የሆነውንና መደበኛ ያልሆነውን የግሉን ዘርፍ ምርታማነት ማሳደግም ሆነ ሁለቱ ዘርፎች ያላቸውን ግንኙነትና ተደጋጋፊነት የሚያጠናክሩበት መንገድ ማመቻቸት አመቺና ገቢ የሚያስገኙ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

### 2.3.1 ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘት

የስራ ስምሪት ችግሮችን መፍታት የሰው ኃይል ምርታማነትን በማሳደግ ዘላቂ ልማት ለማምጣት መሠረታዊ ተግባር ነው፡፡ ወደፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግስት ዘርፍ ትልቁ ትልቁ ቀጣሪ ሆኖ ሊቀጥል ስለማይችል የሥራ ስምሪት ዕድሎችን የማስፋፋት ሚና የግሉ ዘርፍ ድርሻ ነው የሚሆነው፡፡ ሲቪል ሰርቪሱ የግሉን ዘርፍ ዕድገት በአግባቡ የመምራትና የማመቻቸት ድርሻውን በሚገባ እንዲወጣ በተቻለ መጠን በአነስተኛ ቁጥር ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በበቂ ደረጃ ከፍሎ የሚያሰራ መሆን መቻል አለበት፡፡ በመሆኑም መደበኛና መደበኛ ያልሆነውን የግሉን ዘርፍ ምርታማነት ማሳደግና ግንኙነታቸውንና ተደጋጋፊነታቸውን ማጠናከር አመቺ የስራ ስምሪት ዕድሎችን በመፍጠር ድህነትን ለመቀነስ ትልቅ ዕገዛ አለው፡፡

በኢትዮጵያ አብዛኛው ድሀ ሕብረተሰብ በገጠር የሚኖር ሲሆን በዋነኛነትም አነስተኛ ምርታማነትና አነስተኛ ገቢ ባለው የእርሻ ስራ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ከድህነት ለመውጣት የሚያስችለው መንገድ በከፍተኛ ደረጃ የገጠሩን ኢኮኖሚ ምርታማነት (በግብርናም ሆነ ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ ዘርፎች ወይም ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረጉ የፍልሰት እንቅስቃሴዎች) ከማሳደግ ጋር የተቆራኘ ነው የሚሆነው፡፡

በተመሳሳይም መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ እና የሰው ኃይል በስፋት የሚሰማራበትን መደበኛ ዘርፍ ምርታማነትና ገቢ የማስገኘት አቅም መጨመር የከተማ ድህነትን በማስወገድ ረገድ የማይተካ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ድሀ ህብረተሰብ በተሰማራባቸው የሥራ ዘርፎች ላይ በማተኮር ሰፊ የስራ ዕድሎችና የገቢ ምንጮች እንዲፈጠሩ ማድረግ ከመንግስት ይጠበቃል፡፡

የስራ ዕድል ፈጠራ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ያሉት ሲሆን፣ የመጀመሪያው ገፅታ የኢኮኖሚው የስራ መፍጠር አቅም ነው፡፡ ይህ **የስራ ገበያው ያለው የሰራተኛ ፍላጎት** (Labor Demand Aspect) ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ በኢኮኖሚው ውስጥ በሚፈለገው መልክ የተለያየ ሙያና ዕውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት ሲሆን ይህም **የሰራተኛ አቅርቦት ጉዳይ** (Labor Supply Aspect) ሊባል ችላል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ እነዚህን የስራ ስምሪት ሁለት ጠቃሚ ገጽታዎች በማጣጣም ዙሪያ መቀረፅ አለበት፡፡ በሌላ በኩል በሶስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው **የስራ ገበያ ተቋማዊ አደረጃጀትን** (Labor Market Institutions) የሚመለከት ነው፡፡ አራተኛው ከስራ ስምሪት ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉና **ተዛማጅነት ያላቸው መድብለ ዘርፋዊ ጉዳዮች** (Cross-cutting Issues) ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂን የመቅረፁ ሂደትም እነዚህን አራት የስራ ስምሪት ገፅታዎች ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ የፖሊሲውና ስትራቴጂው የትኩረት

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

አቅጣጫዎቹም በአራት ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ሲሆኑ እነሱም የስራ ዕድል ፈጠራ፣ የሰው ኃይል ምርታማነትን ማሳደግ፣ የሥራ ገበያ ተቋማትን ማሻሻልና የሰው ኃይል ገበያ መድብለ ዘርፋዊ ጉዳዮችንና ተያያዥ ገፅታዎችን ያጠቃልላሉ፡፡ የፖሊሲው ገፅታዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

የሚከተሉት የፖሊሲ ዕርምጃ የትኩረት አቅጣጫዎች የኢኮኖሚውን የሠራተኛ ፍላጎት የሚመለከቱ ተብለው የተለዩ ናቸው፡፡

ሀ. የግሉን ዘርፍ ልማት በማፋጠን የስራ ዕድል መፍጠር፣
ለ. ብቁና ውጤታማ ፐብሊክ ሴክተር (መንግስታዊ) ስራ ስምሪት መፍጠር፣

የሚከተለው የፖሊሲ ዕርምጃ የትኩረት አቅጣጫ የሠራተኛ አቅርቦትን የሚመለከት ተብሎ የተለየ ነው፡፡

ሀ. የሰው ኃይሉን ምርታማነት ማሳደግና ማሻሻል፣

የሚከተለው የፖሊሲ ዕርምጃ የትኩረት አቅጣጫ የሥራ ገበያ ተቋማትን የሚመለከት ተብሎ የተለየ ነው፡፡

ሀ. የሰው ኃይል አስተዳደርን ማሳደግና የስራ ገበያ ተቋማትን ማጠናከር፣

የሚከተሉት መድብለ ዘርፋዊ የፖሊሲ ዕርምጃ የትኩረት አቅጣጫዎች ደግሞ ከኢኮኖሚው የሠራተኛ ፍላጎትና አቅርቦት ጎኖች ጋር በተለያየ መልኩ ተዛማጅነት አላቸው ተብሎ የተቀመጡ ናቸው፡፡

ሀ. የህዝብ ቁጥር ዕድገት ላይ ለውጥ ማምጣት፣

ለ. ግሎባላይዜሽን የሚያስከትለውን የስራ ስምሪት ፈተና መቋቋም፣

ሐ. የተዘዋዋሪ ሠራተኞችን መብት መጠበቅ፣

መ. ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን መከታተል፣

ሠ. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የሥራ አካባቢ ሁኔታን ማየት፣

ረ. የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነትን ማረጋገጥና ወጣቱን በስራ ስምሪት ፈጠራ ውስጥ ማካተት፣

ሰ. ህፃናትን ከጉልበት ብዝበዛ መከላከል፣

ሸ. የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃን ማሳደግ ናቸው፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

### 2.3.2 የስራ ዕድል ፈጠራ (የኢኮኖሚው የሰው ኃይል ፍላጎት)

ውጤታማ የድህነት ቅነሳ መንገድ ምርታማና ጥሩ ገቢ የሚያስገኝ የሥራ ዕድል መፍጠር ነው፡፡ ሰፊ የሥራ ስምሪት ፈጠራ ስትራቴጂ በግሉ ዘርፍ እና በመንግስት ተቋማት የሚደረግ ሥራ ፈጠራንና በከተማና ከተማ ቀመስ በሆኑ አካባቢዎች የሚደረግ ኢንተርፕረነርሽፕ ማበረታታትን ያካትታል፡፡

#### 2.3.2.1 የግሉን ዘርፍ ልማት በማፋጠን የስራ ዕድልን መፍጠር

በቅርብ ዓመታት ከግሉ ዘርፍ የኢንቨስትመንት እንቅስቀሴ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር በኩል አበረታች ጅማሮዎች ይታያሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በሀገሪቱ ውስት በፍጥነት በማደግ ላይ ያለው የአበባ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ይህም የግሉን ዘርፍ ልማት በማፋጠን በሀገሪቱ ውስጥ አዳዲስ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠርና ለማስፋፋት እንደ ዋነኛ መንደርደሪያ ሊያገለግል እንደሚችል አብይ ማስረጃ ነው፡፡ በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድም የግሉ ዘርፍ በስራ ስምሪት ፈጠራ የሚኖረው አስተዋፅኦ በሚገባ ተካትቷል፡፡

የግሉን ዘርፍ ልማት በማፋጠን የስራ ዕድል ለመፍጠር የሚከተሉት የፖሊሲ ዕርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

##### i) አመቺ የሆነ የንግድና የኢንቨስትመንት ሁኔታን መፍጠር

በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው የግሉ ዘርፍ የሚጠበቅበትን የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነትና ሞተር የመሆን እንዲሁም የስራ ስምሪትና ገቢ ምንጭ የመፍጠር ሚና በአግባቡ እንዲወጣ አመቺ የንግድና ኢንቨስትመንት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም መሳካት ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱት የፖሊሲና የአስተዳደር ጉዳዮች መካከል የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦት፣ የታክስ ስርዓት፣ የንግድ ቁጥጥር ሥርዓት፣ የውል ስምምነትን የማስከበርና የማስፈፀም፣ አለመግባባቶችን የመዳኘት ሂደት (የግጭት አፈታት) የተወሰኑት ናቸው፡፡ መንግስት ባስቀመጠው የግሉን ዘርፍ ልማት የማፋጠን ፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ማበረታታት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን በተለያዩ ዘርፎች አበረታች ለውጦች ቢደረጉም የንግድና ኢንቨስትመንት አካባቢውን እንዲሁም አንዳንድ የቢሮክራሲ መሰናክሎችን ለማስወገድ አሁንም ተጨማሪ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የንግድ ቦታ አቅርቦትን ማሻሻል፣ የታክስ የአሰራር ሥርዓቱን ተወዳዳሪነትን ለማረጋጋጥ በሚያስችል መልኩ ቀላል ማድረግና መጠቀም፣ የብድር አቅርቦትን ማሻሻል እና የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን ማሳደግ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ያለውን ህጋዊና አስተዳደራዊ ማዕቀፍም ማሳደግና ማሻሻል የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንት በማፋጠን ውጤታማ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ii) **የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ማስፈን**

የማክሮ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በስራ ስምሪት ፈጠራ ላይ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ የፊስካል፣ የገንዘብና የምንዛሪ ፖሊሲዎች በመደበኛው የግል ዘርፍም ሆነ መደበኛ ባልሆነው የግል ዘርፍ ውስጥ የስራ ዕድል ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ መቃኘት አለባቸው፡፡ በመሆኑም መንግስት የተመጣጠነ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲ በመከተል የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ የማስፈንና ለግል ኢንቨስትመንትና ለስራ ስምሪት ፈጠራ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡

የፊስካል ፖሊሲ ለሀገርና ለውጭ ባለሀብቶች በመሰጠት ላይ ካለው ማበረታቻ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ በመሆኑም መንግስት የታክስ ገቢን ለማስፋት እና ለግል ዘርፉ በሚሰጠው ማበረታቻ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ለማበረታታት በሚያደርገው ጥረት መካከል ተገቢ መመጣጠን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ማድረግ ከታክስ የሚገኝ ገቢ ሕዝባዊ አገልግሎቶችን ማለትም እንደ መሠረተ ልማትና ሌሎች አገልግሎቶችን እያደገ ለሚሄደው የግልና የመንግስት ዘርፍ በማቅረብ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ ለስራ ስምሪት ፈጠራና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት ካለው ሚና አንፃር እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

የገንዘብና ምንዛሪ ፖሊሲዎችም በዋጋና በዋጋ ግሽበት እንዲሁም በኢኮኖሚ ትንበያና መረጋጋት ላይ ባላቸው ትልቅ ተፅዕኖ በኢንቨስትመንትና የወደፊት ዕቅድ ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለኢኮኖሚው መስፋፋት አጋዥ የሆነ የገንዘብ ፖሊሲ ኢንቨስትመንትና ብሎም የስራ ዕድል ፈጠራን ያበረታታል፡፡ በተመሳሳይም የምንዛሪ መጠን ፖሊሲ የተረጋጋና ሊተነበይ የሚችል መሆኑ የወጪና ገቢ ንግድ ስራንና በዚህ ዙሪያ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን ሊጠቅም ይችላል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የንግድና ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች በአመቺ ተቋማዊና ቁጥጥር ስርዓቶች በመታገዝ የግሉን ዘርፍ እንቅስቃሴ በማበረታታት ተፈላጊ የስራ ዕድል ውጤቶችን ለማስገኘት ያስችላሉ፡፡

iii) **ለግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚያገለግሉ ልዩ የማበረታቻ መንገዶችን በመቅረፅ ወጥ በሆነና በተቀናጀ መልኩ መተግበር**

በአበባ ኢንዱስትሪው የታየው ከፍተኛ የሆነ ዕድገት በዋነኛነት ለዘርፉ በተሰጡት ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች በመታገዝ የመጣ ነው፡፡ ይህን መሰል ማበረታቻዎች ወደ ሌሎች ጠንካራ ተደጋጋፊነት ወደአላቸው እንደ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም የመሳሰሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ማስፋት በሚፈጥሩት የምርት ሰንሰለት (backward and forward linkages) ለሚያበረክቱት ቀጥተኛ ያልሆነ የስራ ፈጠራ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በተሞክሮ የታየና ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠሪያ መንገዶች ከሆኑት ውስጥ አንዱ ለግብርና ምርትና የሰው ኃይልን በስፋት ለሚጠቀሙ እንደ አግሮ-ፕሮሰሲንግ እንዲሁም ለውጭ ገበያ ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ልዩ ማበረታቻዎችን መስጠት ነው፡፡ እነዚህም ልዩ ማበረታቻዎች

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በዝቅተኛ ወለድ የብድር አገልግሎት መስጠት፣ ተስማሚ የመሬት ሊዝ ዋጋ መጠቀም፣ የታክስ ማበረታቻ (ዝቅተኛ የታክስ መጠን) እና ውጤታማ የስልጠና አገልግሎት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች መስጠትን ያጠቃልላሉ፡፡ በተጨማሪም ለኢንቨስትመንት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎችን መለየት በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ ያስችላል፡፡ በስራ ስምሪት ፈጠራ ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

### iv) ለንግድ ማስፋፍያ አገልግሎት ልዩ ድጋፍ መስጠት

መንግስት የንግድ ማሳደጊያ አገልግሎቶችን በተለይም ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና መደበኛ ላልሆነው ዘርፍ አንቀሳቃሾች በመስጠት የግሉ ዘርፍ ልማትና ስራ ዕድል ፈጠራ ማገዝ ይኖርበታል፡፡ ሕዝባዊ ተቋማት፣ የግሉን ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ውጤታማና የተቀናጀ የንግድ ልማት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ መንግስት ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም እንደዚህ ዓይነት ድጋፎች ወደ ገጠር የሀገሪቱ ክፍል በተለይም በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ ክልሎችና አካባቢዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት እንዲስፋፉ ድጋፍ መሰጠት አለበት፡፡ ለዚህም መንግስት በፌደራልና በክልል ደረጃ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲዎችን በማቋቋም በስልጠና፣ በገንዘብና በመስሪያ ቦታ በኩል አስፈላጊውን ድጋፍ በማቅረብ ዘርፉን በመደገፍ ላይ ይገኛል፡፡ በግሉ ዘርፍና በመንግስታዊ አካላት የሚሰጠው የንግድ ልማት አገልግሎት ውስን ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ልማት ማስፋፍያ አገልገሎቶች በስፋት ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲዳረሱ መደረግ አለበት፡፡

### v) የመሠረተ-ልማት አውታሮችን በይበልጥ ማስፋፋት

ለግሉ ዘርፍ ልማት ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ የልማት አውታሮች ውስጥ ጥራትና ብዛት ያላቸው መንገድ፣ ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና የኃይል አቅርቦት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የተጀመረውን የመንገድ ግንባታ እንዲሁም የመብራትና ስልክ አገልግሎት ልማት አጠናክሮ መቀጠል ለግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋትና አጠቃላይ ዕድገት መምጣት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ የትራንስፖርት እና የኃይል አቅርቦት አገልግሎት ወጪዎችን መቀነስ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎትን ማሻሻል ዓይነተኛ የሆኑ የሀገሪቱን የእርሻ ምርቶችና ድርጅቶች የገበያ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚረዱ ስትራቴጂዎች ናቸው፡፡ ለስራ ስምሪት ዕድል መፈጠርም በር ይከፍታሉ፡፡

### vi) በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ሙስናን መዋጋትና መግታት

ሙስና ለአንዳንድ የንግድ እንቅስቃሴዎች ጤናማ ያልሆኑ ብልፅግናዎችና ጥቅሞች ሲያስገኝ በምትኩ ደግሞ ሌሎች የመስፋፋት ዕድል ያላቸውን በርካታ የንግድ እንቅስቃሴዎች እንዲወድሙ ያደርጋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና እንደሌሎች የአፍሪካ አገራት የከፋ ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ ብዙም የሚያዝናና እንዳልሆነና አንዳንድ አሳሳቢ የሙስና ችግር ምልክቶች እንደሚታዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በእርግጥም ሙስና በመሬት ሽያጭና ኪራይ፣

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በታክስ አሰባሰብ፣ እንዲሁም በመንግስት ጨረታና ጉምሩክ ዙሪያ አሳሳቢ ችግር እየሆነ መምጣቱን የሚሳዩ መረጃዎች አሉ።

ሙስናን መሰረት ያደረጉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ከመግታት በተጨማሪ መንግስት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር መልካም የንግድ ስነ-ምግባርና ባህል ለመፍጠር የሚያስችሉ ዕርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል። ይህም ተቀባይነት ያለው የንግድ አሰራር ደረጃ እና ውጤታማ የንግድ እንቅስቃሴ አመራር እንዲኖር ያስችላል። ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲባል በአንዳንድ የመንግስት አካላት እና የግሉ ዘርፍ ወኪሎች መካከል ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም የሚፈጠሩ የጥቅም ግንኙነቶች መወገድ አለባቸው።

vii) ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ

ግሎባላይዜሽንና ነፃ የንግድ ስርዓት በአሁኑ ወቅት በዓለም ውስጥ በማደግ ላይ ያሉ ጥምር የገበያ ኃይሎች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ ኢኮኖሚ ከአካባቢያዊና ከዓለም ገበያ ጋር ለማስተሳሰርና ተወዳዳሪ ለማድረግ ጥረት መደረግ አለበት። የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማምጣት፣ የሰው ኃይል ምርታማነትን በማሳደግ፣ ገበያን፣ የመረጃ ስርጭትን እንዲሁም ተቋማዊ አደረጃጀትን፣ አመራርንና አሰራርን በማሻሻል ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ይቻላል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ በዝቅተኛ ምርታማነት እና በአነስተኛ የፈጠራ ችሎታ ችግሮች የታጠረ ነው። በተለይም በአለም አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ ተወዳዳሪነት መኖር የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ውጭ ገበያ የመመልከትና የማምረት ሂደት ይገድባል። በመሆኑም የግል ዘርፍ ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በአፋጣኝ ማሳደግ ያስፈልጋል።

## 2.3.2.2 የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር የግሉን ዘርፍ ልማት የማፋጠን ስትራቴጂ

### 2.3.2.2.1 በመደበኛው ዘርፍ ውጤታማ የስራ ስምሪት ፈጠራን ማዳበርና ማስፋፋት

ከዘመናዊ አምራችና አገልግሎት ኢንዱስትሪ ዘርፍ ጋር ከፍተኛ ተደጋጋፊነትና ትስስር ያለው የግብርና ዘርፍ ሳይመሰርቱ የድህነት ችግርን መፍታት የቻሉ አገሮች የሉም። እንዲሁ በረጅም ጊዜ በኢኮኖሚው ውስጥ የኢንዱስትሪውንና የአገልግሎት ዘርፉን ድርሻ በማሳደግ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት መቻል ተመራጭ ነው። በዋነኛነት መታየት ያለበት መደበኛው የግል ዘርፍ እያደገ የሚሄደውን የሰው ኃይል ሊያስተናግድ የሚችል የስራ ዕድል እንዴት መፍጠር እንደሚችል ሲሆን መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ በኩል ያለው ፈተና ደግሞ በዘርፉ ውስጥ ለተሰማራው ሰራተኛ እንዴት ገቢን ማሳደግ እንደሚቻል ነው።[6] ከዚህ በታች ያሉትን

---

[6] የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የአፍሪካ ኢኮኖሚ ሪፖርት (1997 ዓ.ም)፣ በአፍሪካ የስራ አጥነትና ድህነት የሚያስከትላቸውን ፈተናዎች መቋቋም፣አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ስትራቴጂዎች መከተል በመደበኛና መደበኛ ባልሆነው የግል ዘርፍ ውጤታማ የስራ ስምሪት ለመፍጠር ወሳኝ ነው፡፡

### i) የሰው ኃይልን በሰፊው በሚጠቀም ኢንዱስትሪ ላይ ለሚደረጉ የግል ኢንቨስትመንቶች ተወዳዳሪነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ልዩ ማበረታቻዎች መስጠት

ፈጣን የአምራች ኢንዱስትሪዎች ዕድገት መኖር በኢኮኖሚ ውስጥ የሚፈጠሩ መዋቅራዊ ለውጦችን ለማምጣት፣ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠርና በኢኮኖሚው ውስጥ ተደጋጋፊነትንና ትስስርን በስፋት ለማሳደግ ይረዳል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ መሰረት ጠባብና ደካማ ነው፡፡ ወደ ዳበረ ኢኮኖሚ ለመሸጋገርና መደበኛ የስራ ስምሪት ለመፍጠር ካስፈለገ ይህ ሁኔታ መለወጥ ይኖርበታል፡፡

የሰውን ጉልበት በሰፊው የሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎችን ማለትም የምግብና መጠጥ፣ ጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት፣ የቆዳ እና የቆዳ ዉጤቶች፣ ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች እንዲሁም ሌሎች ብረት ነክ ያልሆኑ ማዕድናት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን የመወዳደር አቅም በመገንባት አዲስ የስራ ዕድል መፍጠር ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የእነዚህን ኢንዱስትሪዎች ምርታማነት በማሳደግ የውድድር አቅምን መገንባት ካፒታልን በሰፊው የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ተፅዕኖና በግሎባላይዘሽን ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቋቋም ያስችላል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩ ንዑስ ዘርፎች በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ (PASDEP) ሰነድ ውስጥ ቀጥተኛ የመንግስት ድጋፍ ከሚደረግላቸው ዘርፎች መካከል የሚጠቀሱ ሲሆኑ በዘርፉ ተጨማሪ የተመቻቸ የስራ ዕድል ለመፍጠር ሌሎች አበረታች እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

- በክልሎች የኢንዱስትሪ ዞኖችን በመለየት የሰው ጉልበት በሰፊው የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ለሚያቋቁሙ የግል ባለሀብቶች መሬት ግልፅ በሆነ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማስተላፍ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤

- የመሬት ዋጋ ተመጣጣኝ መሆን የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎችን የመወዳደር አቅም በማሳደግ ሰፊ የስራ ዕድል እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ በቅርቡ የአለም ባንክ የኢትዮጵያን የንግድ ሁኔታ በዳሰሰበት “ Ethiopian Business Climate ” በተሰኘው ጥናት ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት አቅርቦት ችግር በአንጻራዊነት ከፍተኛ ደረጃ መያዙን አመልክቷል (World Bank 2007b)፣

- ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና ዲዛይኖችን በመጠቀም በሀገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ በጥናትና ምርምር ተቋማት (የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት) እንዲሁም ከሀገር ውስጥና ከአለም አቀፍ ቴክኖሎጂ አምራቾችና አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ በማድረግ የግሉን ዘርፍ የውድድር አቅም ማጎልበት፣

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

- ከዓለም አቀፍ ቴክኖሎጂ አምራቾችና አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ በማድረግ የግሉን ዘርፍ የውድድር አቅም ማጎልበት፣
- በፖሊሲ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲሁም በዘርፉ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለማስወገድ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጋር ምክክር የሚያደርግበት የጋራ የምክክር መድረክ አጠናክሮ መቀጠል፣

ii) **የሰው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የግል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ማበረታታት**

በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተፈጠረውን ሰፊ የስራ ዕድል ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማሳደግ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራቴጂዎች መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

- በሀገሪቱ በተለያየ የግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ የውጭ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች በአብዛኛው ባለሙያዎችን ከሀገራቸው በማምጣት የሚያሰሩ ሲሆን ሀገር በቀል ባለሙያዎችን ሲያሳትፉ አይታይም፡፡ ለዚህም የቻይና ኮንስትራክሽን ድርጅቶች ዋና ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለሆነም በሀገራችን በግንባታ ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚተገበር የሥራ ስምሪት መመሪያ (Employment Guideline) ማዘጋጀት፤
- ህብረተሰቡን በቀጥታ ተጠቃሚ የሚያደርጉ አነስተኛ የኮንስትራክሽን ተቋሞች ለማደራጀትና ነባሮቹን ለማጠናከር በመንግስት በኩል የድጋፍ ፕሮግራም ተቀርጾ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል ፡፡ በተለይም ስራ አጥ ወጣቶችና ህብረተሰቡን በአባልነት ያቀፈ አነስተኛ የኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበራት በማደራጀት በአነስተኛ መንገዶች ግንባታ (መጋቢ መንገዶች)፣ በመንገዶች ጥገና፣ በአነስተኛ መስኖ ግንባታ፣ በመጠጥ ውሀ መስመር ዝርጋታ፣ የመኖሪያ መንደሮች እና መኖሪያ ያልሆኑ ቦታዎችን በማስዋብ እንዲሁም በግንባታ ዕቃዎች አቅርቦት እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ አነስተኛ የግንባታ ስራ ተቋራጮችን በማህበራት እንዲደራጁ ማበረታታትና የአቅም ግንባታ ስልጠና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ አቅማቸውን ማጎልበት፤
- የሰው ጉልበት በሰፊው የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ያጋጠማቸውን ችግር በመለየት የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሰፊ የዳሰሳ ጥናቶች በየጊዜው ማካሄድ፤

iii) **ቱሪዝምን መሠረት ያደረጉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት**

በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ሰነድ ውስጥ እንደተመለከተው የቱሪዝም ዘርፍ አዲስ የስራ ዕድል በመፍጠር ህብረተሰቡ እና ወጣቶችን በቀጥታ በማሳተፍና ተጠቃሚ በማድረግ የሀገሪቱን

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን ከፍተኛ አቅም ያለው ዘርፍ ነው፡፡ የዘርፉ ሀገራዊ የረጅም ጊዜ ራዕይ ኢትዮጵያን በ2020 ከአፍሪካ 10 ምርጥ የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ ማድረግ ነው፡፡

የሀገሪቱ ታሪካዊ ቅርሶች፣ የዱር እንስሳትና የደን ሀብት፣ ግሩም የተፈጥሮ ውበት እና ሌሎችም ሀብቶች በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ገቢ ለማሳደግና አዲስ የስራ ዕድሎችንም ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የቱሪዝም ዘርፍን እምቅ አቅም አውጥቶ ለመጠቀም የሚከተሉት ስትራተጂዎች ተቀምጠዋል፡-

- በቱሪስት መዳረሻዎች አገልግሎት የሚሰጡ አብዛኞቹ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና ለዓይን የማይስቡ ናቸው፡፡ ስለሆነም በዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎችንና አስጎብኚ ድርጅቶችን አቅም ለማጎልበት የገንዘብ እና የስልጠና ድጋፍ ፕሮግራም ቀርጾ በክልሎችና ከተማ መስተዳደሮች በኩል መተግበር፤ በድጋፍ ፕሮግራሙ የሆቴል ስራ አመራር፣ የምግብ ዝግጅት እና መስተንግዶ ት/ቤቶችን በማስፋፋት የዘርፉን የሰው ኃይል ብቃት ማሳደግ፤

- ቱሪዝምን በማስተዋወቅ ላይ በተሰማሩ ባለድርሻ አካላት መካከል ትስስር በመፍጠር እና አለም አቀፍ ሚዲያዎችን በመጠቀም ሀገሪቱ ያሏትን የቱሪስት መስህቦች ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ማስተዋወቅ፤

- ሀገር በቀል አስጎብኚ ድርጅቶች ከአቻ የውጭ ሀገር ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማበረታታት፣ ድጋፍ ማድረግ፤

- በኢኮ-ቱሪዝም ለመሰማራት ፍላጎት ባላቸው የግል ባለሀብቶች እና በህብረተሰቡ መካከል አጋርነት ለመፍጠር የሚያስችሉ ፖሊሲ እና መመሪያዎችን ማውጣት፤

### iv) የሰው ጉልበት በሰፊው በመጠቀም የተመረቱ ምርቶችን ኤክስፖርት ማሳደግ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአብዛኛው ለቤት ውስጥ ፍጆታ በሚያመርት የግብርናው ዘርፍ የተያዘ በመሆኑ በኢኮኖሚው ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ያለውን የሰው ኃይል ሊያስተናግድ የሚችል የስራ ዕድል መፍጠር አልተቻለም፡፡ ስለሆነም የንግዱን ዘርፍ (Commercialization) በማስፋፋት በገበያ ላይ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የግብርና ምርቶች እንዲመረቱ መንግስት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ርካሽ የሰው ጉልበት በበቂ ሁኔታ መኖር፣ የግብርና እና የማዕድን ጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልካቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች ጋር ሲነፃፀር አንጻራዊ ጥቅም (Comparative Advantage) በማስገኘት የተሻለ በመሆኑ በዘርፉ ለማደግ ሰፊ ዕድል እንዳለ ያመላክታል፡፡

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በሌላ በኩል በሀገሪቱ የመሠረተ ልማት ዘርፍ ብዙ መሻሻሎች ቢታዩም ለረጅም ጊዜ የዘርፉ ዕድገት እጅግ አዝጋሚ ሆነ የቆየ መሆኑ እንዲሁም ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሀገር መሆኗ በወጭ ንግዱ ዘርፍ በአለም አቀፍ ገበያ በበቂ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዳትሆን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይሁንና የወጭ ንግድን ለማሳደግ ምቹ ፖሊሲና ስትራተጂ ቀርጾ ተግባራዊ በማድረግ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃ በማሳደግና የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕድገትን በማፋጠን የውድድር አቅምን ማጎልበት ይቻላል፡፡

በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ሰነድ ውስጥ ጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት፣ ቆዳና የቆዳ ዉጤቶች በወጭ ንግዱ ዘርፍ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ንዑስ ዘርፎች በመባል ተለይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የመንግስት ድጋፍ ፕሮግራም በእነዚህ ውስን ዘርፎች ላይ ብቻ ሳያተኩር ሌሎችንም አቅም ያላቸውን ዘርፎች በመለየት ማቀፍ አለበት፡፡ በወጭ ንግድ የተሰማሩ ባለሀብቶች አስፈላጊውን አገልግሎት ማለትም የኃይል አቅርቦት፣ የውሀ፣ የመንገድና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያገኙ ይገባል፡፡ የመሠረተ ልማት መስፋፋት የኢንዱስትሪዎችን በሀገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ የመወዳደር አቅም ከማጎልበቱም በላይ አዲስ ፈጠራ በማከል የተለያዩ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን ለገበያ እንዲያቀርቡ ይረዳል፡፡

የዘርፉን ዕድገት ለማፋጠን ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራተጂዎች ተቀምጠዋል፤

- የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውጭ ንግድን ለማበረታታት የተለያዩ እርምጃዎችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት፣ በቆዳ እና የቆዳ ዉጤቶች ንግድ ላይ ሰፊ ለውጥ ያልተመዘገበ ሲሆን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በዘርፉ ተግባራዊ የተደረጉ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎችን በመፈተሽ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፣

- የወጭ ንግድን ለማበረታታት የሚተገበሩ ፓኬጆች ቀረጻ ላይ እንዲሁም በአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ወቅት የላኪዎች ማህበራት በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት፣ አቅማቸውን ማጎልበት፤

- በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ የሚደረጉ የንግድ ልውውጦችን (e-Commerce) ለማበረታታትና ለማሳደግ የተቋሞችን መዋቅር ማሻሻል፣ የተቋማት ብቃትን ማሳደግና የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፤

### v) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማንቀሳቀስ በልማት ላይ እንዲሳተፉ ማበረታታትና መደገፍ

የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሁኔታ እና ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ ስትራተጂዎችን በመተግበር በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ወደ ሀገራቸው በመምጣት በልማት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል፡፡ በውጭ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በማንቀሳቀስ በሀገሪቱ ልማት ላይ እንዲሳተፉ የሚያግዙ ስትራተጂዎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፤

- በግንባታ መሬት አቅርቦት፣ በመሠረተ-ልማት ግንባታ፣ በፈቃድ አሰጣጥ ቅልጥፍና፣ በታክስ ዕፎይታ አፈፃፀም ላይ ማበረታቻዎችን ማድረግ፣ ነባሮቹን አጠናክሮ መቀጠል፤
- በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች የሚሰጡ የኢንዱስትሪ ዞኖችን በመለየት የመሬት አቅርቦትን ችግር መቅረፍ፤
- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት ሀገር ለኢትዮጵያ ምርቶች ገበያ እንዲያፈላልጉ በማበረታታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከሌሎች ሀገራት ኢኮኖሚ ጋር ትስስር እንዲፈጥር ማድረግ፤

#### 2.3.2.2.2 በራስ ሥራ የሚሰማሩትን ማበረታታትና መደበኛ ያልሆኑ ዘርፎችን መደገፍ

በከተሞች አካባቢ የሚገኘው አብዛኛው ህዝብ በራስ ሥራ (Self-employment) መደበኛ ባልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ በዋነኝነት ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን በመስጠትና በሀገር ውስጥ ገበያ የሚሸጡ ሸቀጦችን በማምረት ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ "የመጨረሻ አማራጭ ቀጣሪ" (Employer of the last resort) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ያልሰለጠኑ (Unskilled) ወጣቶች፣ ሴቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በብዛት የተሰማሩበት ዘርፍ ነው፡፡ በጣም ዝቅተኛ ትርፍ በሚያስገኙና ከአቅም በታች በሆኑ ጥቃቅን ስራዎች ላይ መሰማራት የዘርፉ ዋነኛ ችግር ነው፡፡ መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ እና የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን ምርታማነት ማሳደግ የከተሞችን የድህነት ሁኔታ ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በአሁኑ ወቅት መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ ሰፊ የሰው ኃይል በመያዝ በተለይም ሴቶችና አቅመ ደካሞች የተሰማሩበት በመሆኑ ዘርፉን በመደገፍ ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ የሚሰጠውም ድጋፍ በዘላቂነት በዘርፉ እንዲቆዩ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ውስጥ ወደ መደበኛ ዘርፍ እንዲሸጋገሩ የሚያግዝ መሆን ይኖርበታል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና (TVET) ማስፋፋት የአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት ልማት (MSEs) ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አነስተኛ የገንዘብ ተቋማትን (MFIs) ማደራጀትና መደበኛ ያልሆኑ ዘርፎችን መደገፍ በአምስት ዓመቱ ልማት ዕቅድ ውስጥ ከተቀመጡት የልማት ማሳኪያ መሣሪያዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

#### 2.3.2.2.3 የኢንተርፕረነርሺፕ ትምህርትና ስልጠና አስፈላጊነትን በማሳመን ለሁሉም ማዳረስ

የኢንተርፕረነርሺፕ ዕውቀትና ክህሎት ሰዎች በተሰማሩበት የንግድ እንቅስቃሴ ስኬታማ እንዲሆኑ ከመርዳቱም በላይ የሰዎችን ዕይታ በማስፋት አዲስ የንግድ በሮችን በመፈለግ የስራ ዕድል ፈጠራን ያሰፋል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የኢንተርፐረነርሺፕ ዕውቀት ለንግድ እንቅስቃሴ ስኬታማነትና ዜጎች ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ በመርዳት የስራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ የሚረዳ በመሆኑ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ተቆጥሮ በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከታች ጀምሮ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

### 2.3.2.3 የመንግሥት ሴክተር ሥራ ስምሪትን (Public sector employment) ውጤታማነት እና ብቃት ማሳደግ

በከተሞች አካባቢ በመደበኛ ዘርፍ ከተሰማሩት ሠራተኞች መካከል በመንግስት ተቋማት የሚደረግ ቅጥር ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛል፡፡ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት የመደበኛ ዘርፍ ሠራተኞች በመንግስት ተቋማት ውስጥ የተቀጠሩ ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ 68 በመቶ የሚሆኑት ከፍተኛ ትምህርት ያጠናቀቁ ናቸው፡፡

የመንግስት ተቋማት ለግሉ ዘርፍ በሚሰጡት ድጋፍ እና አገልግሎት ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም የመንግስት ሠራተኞች የስራ ብቃትና ውጤታማነት ለኢኮኖሚው ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በመንግስት ተቋማት የሚደረግ የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴ የግል ተቋማት ሊያከናውኑት በማይፈልጉትና በማደግ ላይ ያሉ ክልሎችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማሳደግ አዲስ የሥራ ዕድል በመፍጠር ላይ ሊያዘነብል ይችላል፡፡

በመንግስት ተቋማት የሚፈጠሩ አዳዲስ የስራ ዕድሎች ከፍተቶችን በመሙላትና በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸውን ተቋማት በማስፋፋት መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጡ ማህበራዊ አገልግሎቶችን፣ የህግ አገልግሎቶችን ያጠቃልላሉ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ አገልግሎቶች በመንግስታዊ ዘርፍ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ያግዛሉ፡፡

#### 2.3.2.3.1 የመንግስት ሴክተር የሥራ ስምሪት ብቃትና ዉጤታማነት ለማሳደግ የሚረዱ ስትራተጂዎች

በመሠረተ-ልማት ግንባታ ላይ በመረባረብ፣ የሰው ኃይልን መሰረት ያደረገ በህዝብ ተሳትፎ የሚከናወን (Public work) ፕሮግራም በመተግበርና ከተሞችን የካፒታልና የዕውቀት ተኮር ምርቶችና አገልግሎቶች አቅራቢ ማዕከል በማድረግ ዉጤታማ ድህነት ተኮር የመንግስት ሴክተር ሥራ ስምሪት መፍጠር ይቻላል፡፡

ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የመሠረተ ልማት ግንባታ በገጠር የመሠረተ ልማት አቅርቦትን ለማሻሻል ጠቃሚ ነው፡፡ በመንገድ፣ በቴሌኮም፣ በኢነርጂ እና መስኖ እንዲሁም በማህበራዊ ዘርፍ በትምህርትና በጤና ላይ የሚደረግ የመንግስት ኢንቨስትመንት በሰው ኃይል ልማት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ እነዚህ ኢንቨስትመንቶች አዲስ የስራ ዕድል ከመፍጠራቸው በተጨማሪ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ልማት ያፋጥናሉ፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ስለሆነም ዉጤታማ እና ብቃት ያለው የመንግስት ሴክተር የሥራ ስምሪት ለመፍጠር የሚያስችሉ ስትራተጂዎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

### i) ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ማካሄድ

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ መዘጋጃ ቤቶች፣ የከተማ መስተዳደሮች፣ የውሀ ሀብት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ሌሎችም በእያንዳንዱ በጀት ዓመት ለሚያካሂዱት የግንባታ ስራ መንግስት ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ይመድባል፡፡ እነዚህ ዘርፎች በግንባታ ወቅት ጉልበትን በሰፊው እንዲጠቀሙ የማበረታቻ ፓኬጆችን ቀርጾ በመተግበር በየዘርፉ የተፈጠረውን አዲስ የስራ ዕድል መከታተል ያስፈልጋል፡፡

### ii) በትግበራ ላይ የሚገኙ የመንግስት ፕሮግራሞች ዉጤታማነትና አግባብነት ማሻሻል

የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አካል በመሆን በመተግበር ላይ የሚገኘው የምርታማ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም የገጠሩን ህብረተሰብ በመንገዶች ግንባታና በሌሎች የመሠረተ-ልማት እንቅስቃሴዎች ላይ በማሳተፉ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ፕሮግራም የሚከፈለው የደመወዝ መጠን አነስተኛ በመሆኑ በሚገኘው የሥራ ውጤት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲፈጥር ይታያል፡፡

በመንግስት የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን ችግር በመቅረፍ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚከተሉት ስትራተጂዎች ተቀምጠዋል፡፡

- በመተግበር ላይ የሚገኙ ህጎችና ደንቦችን እንዲሁም የክፍያን ሁኔታ በማሻሻል በምርታማ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ለሚካሄዱ የልማት ሥራዎች የጥራት ደረጃ መወሰን፤
- በህዝብ ጉልበት በሚካሄዱ የመንግስት ፕሮግራሞች አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ወቅት ህብረተሰቡን ማሳተፍ፤
- በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተለይም በትምህርትና ጤና ዘርፎች ውስጥ ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠር፤

### iii) የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ማሻሻል በተለይም በትምህርትና በጤና ዘርፍ

በመስፋፋት ላይ የሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ክሊኒኮች እና ሆስፒታሎች ከፍተኛ የስራ ዕድሎችን ፈጥረዋል፡፡ ይሁንና የዚህ አገልግሎት መስፋፋት በተለይ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ በሚጠይቁ የሥራ መደቦች ላይ የሰው ኃይል ዕጥረት እየገጠመው የውጭ ሀገር ዜጎች በዩኒቨርሲቲዎችና በኮሌጆች ውስጥ ተቀጥረው እንዲያገለግሉ እየተደረገ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በአዳዲስ የመንግስት የትምህርትና የጤና ተቋማት የትምህርትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አልፎ አልፎ ጥራት መቀነስ አዝማሚያ ይታያል፡፡

ስለሆነም በዘርፉ የሚታየውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት (በዓይነትም ሆነ በጥራት) ለማሟላት የሚከተሉት ስትራተጂዎች ተቀይሰዋዋል፡፡

- ዝቅተኛ የሆነ የትምህርትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት በሰው ኃይል ልማት እና በሀገሪቱ የመወዳደር አቅም ላይ ከፍተኛ ጫና እንደሚፈጥር በመገንዘብ የትምህርትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ከመንግስታዊ ተቆጣጣሪ ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያቀፈ የጋራ የምክክር መድረክ ማቋቋም፣

- በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰሩ ሠራተኞች በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ለማድረግና እንዳይለቁ ለመከላከልና ተጨማሪ ባለሙያዎችን ለመሳብ የሚያስችል የተለያዩ ስልቶችን መቀየስ፣ ምቹ የስራ ሁኔታ መፍጠር፣ የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣

- በተመረጡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የሁለተኛ ዲግሪ ስልጠና በማጠናከርና በማስፋፋት የኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎችን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ማሟላት፡፡

### 2.3.3 የሰው ኃይል ምርታማነትን ማሻሻል (የሰው ኃይል አቅርቦትን ማሻሻል)

#### 2.3.3.1 የግብርና ዘርፍ የሰው ኃይል ምርታማነትን ማሳደግ

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የግብርናው ዘርፍ ጥሩ አፈጻጸም የታየበት እና የሥራአጥ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም የገጠሩ የድህነት ሁኔታ ግን ከፍተኛ ነው፡፡ የገጠሩን ድህነት ለመቀነስ አገሪቱ የምትከተለው የፖሊሲ አቅጣጫ አዲስ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ከማተኮር ይልቅ የገጠሩን ህብረተሰብ ገቢ በማሳደግና ምርታማነትን በማሻሻል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በአጠቃላይ የግብርናን ምርታማነት ለማሳደግ የተያዘው አቅጣጫ ተያያዥነት ባላቸው የተለያዩ ጉዳዮች ማለትም ቴክኖሎጂያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መሠረተ-ልማትና በተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል እንዲሁም በመሬት አስተዳደር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የፖሊሲ እርምጃዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

#### i) የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ውጤታማነት እና የቴክኖሎጂ እድገትን ማረጋገጥ

በአገር አቀፍ ደረጃ በማዳበሪያ አቅርቦት እና አጠቃቀም ዙሪያ ብዙ መሻሻሎች ቢታዩም የመጠቀም ፍላጎት ላይ ክፍተቶች አሉ፡፡ በተለይም የምርጥ ዘር አጠቃቀም በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የምርጥ ዘር አጠቃቀም ተግባራዊ ሳይደረግ ማዳበሪያን ብቻ መጠቀም

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ላይ ብዙ ለውጥ አያመጣም፡፡ መንግስት የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ እየወሰደ ያለውን እርምጃ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ የቴክኖሎጂ ለውጥ (አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ) የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሻሻል (በእጃችን ያሉትን ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ መጠቀም) የቴክኖሎጂ ዕድገት (አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን በሙሉ አሟጦ መጠቀም) ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ ናቸው፡፡

ገበሬዎች የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማስቻል የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና በአብዛኛው ዝናብ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስርዓቱ በመስኖ ልማት መደገፍ ይኖርበታል፡፡ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የግብርና ምርታማነትን የማሻሻል እርምጃዎች ከእንስሳት ግጦሽ፣ መኖ፣ ውሀ እና ከእንስሳት ጤና እንክብካቤ ጋር በመያያዝ መከናወን ይኖርበታል፡፡

### ii) የኢኮኖሚ ዘርፍ ማበረታቻዎችን ማሻሻል

በመንግስት በኩል የሚደረጉ የግብርና ማበረታቻዎች በአብዛኛው ምርታማነትን ለማሳደግ የሚተገበሩ እንጂ የኢኮኖሚ ማበረታቻዎች አይደሉም፡፡ ስለሆነም የምርት ዕድገት በተሻሻለበት ዘመን (ለምሳሌ በጥሩ የምርት ዘመን እንደሚታየው) በተቃራኒው የምርት ዋጋ ስለሚቀንስ የገበሬዎች ለገበያ የማምረት ፍላጎት ይወርዳል፡፡

ስለሆነም መንግስት የግብርና ግብዓት እና የግብርና ምርት ግብይት ስርዓት ይበልጥ በማሳደግ ገበሬዎች የውድድር ገበያ ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ዋናው የትኩረት አቅጣጫ የግብርና ምርት ለቤት ውስጥ ፍጆታ ከመጠቀም አልፎ ለገበያ እንዲውል ማበረታታት እና የግብርና ምርት ከሀገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ ገበያ ጋር ማስተዋወቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

የምርት ትስስር ልማት እና ጊዜያዊ የግብርና ቅጥር (Contract) ዘዴን በመጠቀም ገበሬዎች ከገበያ፣ ከግብርና ምርት ተጠቃሚዎችና (Processors) ከላኪዎች (Exporters) ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### iii) የመሠረተ ልማት እና የተቋማት ልማት

መንግስት በመሰረተ ልማት ግንባታ እና የገበያ ተቋማትን በማስፋፋት ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የጥራትና ደረጃ፣ የህግ፣ የመረጃ፣ የፋይናንስ እና ለአደጋ ተጋላጭነትን የሚቆጣጠሩ ተቋማትን በማጠናከር እና ከአምራች እስከ ተጠቃሚ ድረስ ለማድረስ የሚወስደውን ጊዜ እና ወጪ በመቀነስ ላይ አተኩሮ መስራት ይኖርበታል፡፡ ለግብርና ንግድ ተቋማት እና ለገበሬዎች ድርጅቶች ለምሳሌ ለህብረት ሥራ ማህበራት ልዩ ትኩረት በማድረግ ገበሬዎችን ከገበያ ጋር ማስተሳሰር እና በግብርና ጥሬ ዕቃ ላይ እሴት በመጨመር የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ እንዲገቡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በአምስት ዓመቱ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ሰነድ ውስጥ የግብርና ግብይት ሥርዓትን ማሳደግ አስፈላጊነት የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ በመተግበር ላይ ያለው የግብርና ምርት ግብይት ሥርዓት ይበልጥ ተጠናክሮ ሌሎች አቅም ያላቸው ምርቶችን ሁሉ በማካተት መከናወን ይኖርበታል፡፡

ያሉትን የማበረታቻ ፓኬጆች በማጠናከር ሁሉም ባለድርሻ አካላት በሂደቱ ውስጥ መሳተፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም አካላት ገበሬዎችን፣ የግብርና ግብዓት አቅራቢዎችን፣ የግብርና ግብዓት ተጠቃሚዎችንና ላኪዎችን (Exporters) ያጠቃልላሉ፡፡

### iv) የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ

የገጠሩ ህብረተሰብ የእርሻ መሬት ይዞታ ባለቤትነት መረጋገጥ የመሬቱን ለምነት በመጠበቅ እንዲያመርት ከማበረታታቱም በተጨማሪ የእርሻ ምርታማነት እንዲጨምር ይረዳል፡፡ በመንግስት በመተግበር ላይ የሚገኘው የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ ፕሮግራም የመሬት ባለቤትነትን በማረጋገጥ የእርሻ መሬት ለምነትን እና ምርታማነትን ለመጠበቅ የሚረዱ የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንቶች ማለትም የእርከን ግንባታ፣ የመስኖ እና የደን ልማት ላይ ሊኖረው የሚችለው ፋይዳ መዳሰስ አለበት፡፡

የሀብት ባለቤትነት መብት እንዲሁም የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መረጋገጥ ገበሬዎች በእርሻ መሬት አስተዳደር እንዲሁም የመሬትን ለምነት ለመጠበቅና ምርታማነት ለማሳደግ በሚያድርጉት ውሳኔ ላይ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመንግስት በመከናወን ላይ የሚገኘው የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ ፕሮግራም በእርሻ መሬቶች ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶችን ያበረታታል ተብሎ ይገመታል፡፡

### v) ከግብርናና ከግብርና ውጪ በተጓዳኝ ያሉ ስራዎችን ማበረታታት

የገጠሩ ህብረተሰብ ከግብርና በተጓዳኝ ከግብርና ውጪ በሆኑ ተጓዳኝ ስራዎች ላይ እንዲሰማራ ለማድረግ አምስት ዓይነት ሀብቶች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህም የሰው ሀብት (ዕውቀትና ክህሎት)፣ ማህበራዊ ሀብት (ግንኙነትና ትውውቅ)፣ የመሰረተ ልማት (ትራንስፖርትና መገናኛ)፣ ገንዘብ (ቁጠባና ብድር) እና የተፈጥሮ ሀብት (መሬት፣ ደን፣ ማዕድናት፣ የአሳ ሀብት እና የመሳሰሉት) ናቸው፡፡ የገጠሩን ህብረተሰብ ከእርሻ በተጓዳኝ በሚካሄዱ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፍ የገጠር አነስተኛ የብድር ተቋማትን ማስፋፋት፣ በንግድ ዙሪያ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት እና የገጠር የመሰረተ ልማትን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

ደሀውን ህብረተሰብ ግብርና ነክ ባልሆኑ ስራዎች ላይ በማሰማራት በሚፈጠረው የስራ ዕድል ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኝ ለማድረግ ቢያንስ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የገንዘብ እና የሰው ሀብት ልማት ለማሻሻል የሚያስችሉ ዕርምጃዎችን መወሰድ ያስፈልጋል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

አነስተኛ የገጠር የገበያ መንደሮችን በማሳደግ የገጠርና የከተማ ትስስርን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ የገጠር የገበያ መንደሮች የገጠሩን ኢኮኖሚ እና የሰው ኃይል ግብርና ነክ ካልሆኑ ስራዎች እንዲሁም ከተሞች ጋር ለማገናኘት ማዕከል በመሆን ያገለግላሉ፡፡

### 2.3.3.1.1 በግብርና ዘርፍ የተሰማራውን የሰው ሀብት ምርታማነት ለማሳደግ የተቀየሱ ስልቶች

በግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች የተሰማራውን የሰው ኃይል ምርታማነት ለማሳደግ በመተግበር ላይ የሚገኙ ስልቶች መፈተሽ እንዲሁም አዳዲስ ስልቶችን መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ የገጠሩን ህብረተሰብ ድህነት ሊያስወግዱ የሚችሉ ሁለት መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛው መንገድ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ማሸጋገር ሲሆን ይህ ሽግግር የግብርና ምርት ዓይነትን በማሳደግ፣ ማለትም የአዝዕርት ዓይነቶችን ማብዛት፣ በገበያው ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ ምርቶችን በማምረት እና የግብርና ግብዓቶችን በአግባቡ መጠቀምን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ይህ መንገድ እጅግ ምርታማ በሆኑ የግል የንግድ እርሻዎች ላይ በመቀጠር በሚያገኙት የተሻለ ደመወዝ ከድህነት የሚወጡ ሰዎችን ያካትታል፡፡ በዚህ ደረጃ የግብርና የሰው ኃይል ወደ ከፍተኛ ምርታማ ዘርፍ ይሸጋገራል (ለምሳሌ፡- በግብርናው ዘርፍ ከዝቅተኛ ምርታማ እና ለቤት ውስጥ ፍጆታ ብቻ ከማምረት ወደ እጅግ ምርታማ የንግድ ዘርፍ፣ ከዝቅተኛ ምርታማ ግብርና ነክ ያልሆኑ ዘርፎች ወደ መደበኛ እና ምርታማ ግብርና ነክ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች መለወጥ ወ.ዘ.ተ ወይም ቀደም ሲል የማያመርቱ የምርት መገልገያዎችን ወደ አምራችነት በማሸጋገር ይከናወናል)፡፡

ቀጣይና ድህነት ተኮር የምርት እና የምርታማነት ዕድገት የአነስተኛ ገበሬዎችን አመራረት ዘይቤ የእርሻ እና እንስሳት እርባታ፣ የሰብል ምርት እና የደን ልማትን በማጣመር ፣እንዲሁም ለቤት ውስጥ ፍጆታ እና ለንግድ ማምረት፣ መስኖ እና የአሳ እርባታ፣ የአካባቢ እና አዲስ የአዝዕርት ዝርያዎችን በማጣመር ማምረትን ያካትታል፡፡ ይህም በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ክልሎች አንጻራዊ ጥቅምና የመወዳደር አቅም ላይ በመመስረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

ከግብርና ውጪ ያለውን ሥራ ምርታማነት እና ትርፋማነት ማሳደግ ወይም ጥሩ ክፍያ በሚፈጽሙ መደበኛ ዘርፎች ውስጥ መሰማራት ከድህነት ለመውጣት ሁለተኛው መንገድ ነው፡፡

በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ሰነድ ውስጥ የተዘረዘሩትን ግቦች የሥራ ዕድል የመፍጠርና የሰው ኃይል ምርታማነትን የማሳደግ ግቦች ለማሳካት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራተጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

**i) በከፍተኛ ደረጃ ምርታማ የሆኑ የዘር ዓይነቶችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በማባዛት ለማሰራጨት የሚያስችል ልዩ ዘዴ መቀየስና መተግበር፣**

በመንግስት በመካሄድ ላይ የሚገኘው ምርጥ ዘርን ማባዛትና ማሰራጨት ውጤታማ ባለመሆኑ ተወዳዳሪና ቀጣይነት ያለው የስርጭት አቅም እና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሰው ኃይል ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ እና የግብርናን ምርት ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ii) የመስኖ እና የግብርና ወጪ ለመቀነስ የድጋፍ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ

የማዳበሪያ እና የምርጥ ዘር ድጎማ በ1990ዎቹ ከተነሳ ወዲህ የግብርና ግብዓት ዋጋ በመጨመሩ በአጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆነው የአገሪቱኤአስራረስ ዘዴ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ለማምረት የሚያስችል ሲሆን፣ መስኖን በመጠቀም በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ ለማምረት ይቻላል። የግብርና ግብዓት ድጎማ እና በመስኖ ልማት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን ጨምሮ በመንግስት የሚካሄድ ድጋፍ የግብርናን ግብዓት አጠቃቀም ከማሻሻሉም በተጨማሪ በግብርና ዘርፍ ትርፋማነት እና ግብርናን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

iii) በግብርና ኤክስቴንሽን ፣ በምክርና ስልጠና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ ስርዓት መዘርጋት

የመንግስት ተቋማትን ብቻ በመጠቀም በሚከናወን ልማዳዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት የተጠበቀው ያህል ውጤት ሊመዘገብ አልቻለም። ስለሆነም የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የምክርና የስልጠና አገልግሎት አሰጣጥ በመንግስት፣ በግል ተቋማትና በሲቪል ማህበራት መካከል የውድድር መንፈስን በመፍጠር ባልተማከለ አሰራር መከናወን ይኖርበታል።

iv) የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ ስርአት በእርሻ መሬት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ መሆኑን ማረጋገጥ

የሀብት ባለቤትነት መብት ማረጋገጫ ስርዓት የመሬትን ለምነት ለማሻሻል የሚደረጉ የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንቶችን ማለትም የመስኖ ልማት፣ የዛፍ ተከላ እና ሌሎች ኢንቨስትመንቶችን የሚያበረታታ መሆኑን ማረጋገጥ።

v) አነስተኛ ገበሬዎችን ከጥቃት የሚከላከሉ፣ ህጋዊ መብታቸውን የሚያስጠብቁ፣ ድጋፍ የሚሰጡ የገበሬዎች ተቋማትን ለማቋቋም ፈጣን ዕርምጃ መውሰድ፣

ጠንካራ እና ፍላጎት ያላቸው የገበሬዎች ማህበራት አለመኖር ግብርና እና የገጠር ልማትን አስመልክቶ በሚወጡ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ቀረጻ ወቅት የሚኖረውን የገበሬዎች ተሳትፎ ውስን ያደርገዋል። ውጤታማ የገበሬዎችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንዲሁም በገጠሩ አካባቢ ባለሀብቶች እንዲፈጠሩ ለማድረግ አሳታፊ ተቋማትን ለምሳሌ፡- ብሔራዊ የገበሬዎች ማህበርና የተለያዩ የግብርና ምርቶች አምራች ገበሬዎች ማህበራትን ማቋቋም ያስፈልጋል። የግብዓት ድጋፍን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማድረግ እንዲሁም የቁጥጥር ፖሊሲዎችን ማጠናከር በቀጣይ የግብርና ልማትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው።

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

vi) አገር በቀል ዕውቀትና ክህሎቶች ጥቅም ላይ እንዲወሉ ማበረታታት

የገበሬዎችን የተረጋገጠ የቆየ ልምድና አገር-በቀል የግብርና ዕውቀቶችን በማበረታታት ምርታማነትን ማሳደግ፣

vii) ገበያ-ተኮር ምርትን በማበረታታት ምርታማ የስራ ስምሪት እንዲስፋፋ ማገዝ

በተለምዶ የሚታወቁና የማይታወቁ ገቢ የሚያስገኙ ምርቶችን ምርታማነትና ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ አብዛኞቹ ገበሬዎች ለምግብ ፍጆታ ከማምረት ለንግድ ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለሀገር ውስጥ እና ለአለም አቀፍ ገበያ የሚቀርቡ የፍራፍሬ ምርቶች ልማት አዲስ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ከማስቻሉም በላይ ገቢው በብዙ ዕጥፍ እንዲጨምር አስችሏል፡፡

በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ሰነድ ውስጥ የተቀመጠው የንግድ ግብርናን የማስፋፋት ዓላማ አዲስ የሥራ ዕድልና ምቹ የሥራ ሁኔታን በመፍጠር እንዲሳካ ለማድረግ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

- የኮንትራት ግብርና ለማስፋፋት የህግ፣ የቁጥጥርና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ አነስተኛ ገበሬዎች ለንግድ ዓላማ ከሚያመርቱ ገበሬዎችና አቀነባባሪዎች ጋር በጥምረት በመስራት የቴክኖሎጂ፣ የገበያ እና የገንዘብ እጥረት ችግሮቻቸውን ለማስወገድ እድል አላቸው፡፡ የኮንትራት ግብርናን ለማጎልበት የህግ እና የቁጥጥር ስርዓት ማዕቀፍ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

- በተመረጡ ቦታዎች አነስተኛ ገበሬዎች ለንግድ እንዲያመርቱ ልዩ እገዛ ማድረግ፡- አነስተኛ ገበሬዎች ለውጭ ሀገርና ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎች እንዲሁም ለገበያ የሚውሉ ምርቶችን እንዲያመርቱ ድጋፍ ማድረግ፡፡ ይህም የተሻሻለ እና አስተማማኝ የመሬት፣ የውሀ አቅርቦት እንዲሁም የማምረቻ መሳሪያዎችና የምርጥ ዘር አጠቃቀም ክህሎት፣ የገንዘብና የገበያ ተደራሽነት ድጋፍ በማድረግ ሊከናወን ይችላል፡፡

viii) በዶሮ እና በእንስሳት ዕርባታ ምርታማ የስራ መስክ መፍጠር

ግብርና በሚካሄድባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች የሚታየውን የህዝብ ቁጥር መጨመር ከግምት ውስጥ በማስገባት ያለው የሰው ኃይል በዶሮና በቤት እንስሳት ዕርባታ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ገቢንና ምርታማነትን ለማሳደግ ተገቢ የሆነ ዕርምጃ ነው፡፡ የወተት ላም እርባታ፣ እንስሳትን ማድለብ እና የዶሮ እርባታ ለብዙ ወጣቶች ወደ ግብርናው መስክ እንዲገቡና ምርታማ እንዲሆኑ ከፍተኛ ዕድል ፈጥሯል፡፡

በሀገሪቱ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ውስጥ በእንሰሳት እርባታ መስክ ከፍተኛ የስራ ዕድል እንዲሁም ምቹ የስራ ሁኔታ ለመፍጠር የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

➢ የእንስሳት ህክምና አገልግሎትን ለማዳረስ በመንግስት እየተደረገ ያለውን ጥረት የሚያግዙ የግል የእንስሳት ህክምና ተቋማት እንዲስፋፉ ማበረታታት፣ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፣

➢ ለግል የእንስሳት ሕክምና አገልግሎት ሰጪዎች አመቺ ሁኔታን በመፍጠር እና ውጤታማ የመንግስትና የግል ሽርክና (Public-Private-Partnership) አሰራር በማራመድ የእሰሳት ሕክምና አገልግሎትን ቀልጣፋ ማድረግ፣

➢ ደህንነቱ የተጠበቀና ጥራት ያለው የእንስሳት ምርትና ግብይት እንዲኖር ውጤታማ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት መዘርጋት፣ በእንስሳት በሽታ ምክንያት የኢትዮጵያ የእንስሳት ተዋጽኦ አምራቾች ወደ አለማቀፍ ገበያ የመግባት ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ በመሆኑም የመንግስት የላብራቶሪ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን አቅም በመገንባት ውጤታማ የቁጥጥርና የክትትል አገልግሎት መስጠት ያስፈልጋል፣

➢ የእንስሳት አርቢዎችን መብት ለማስከበር የወተት ከብት፣ የበሬ ፣ የበግ፣ የፍየል፣ የዶሮ እና የዓሣማ ሥጋ አምራቾች ማህበር እንዲቋቋም ዕርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ የእንስሳት ህክምና ሽፋንን ማሻሻል፣ የግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የእንስሳት መኖ አቅርቦት፣አስተማማኝ የውሀ አቅርቦት፣ ጥሩ መንገዶች፣ የእንስሳት እርባታ ቴክኖሎጂ እንዲሁም የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎት ያለ አምራቾች ቀጥተኛ ተሳትፎ ዕውን ሊሆኑ አይችሉም፡፡

### ix) የአርብቶ አደሩን ሕብረተሰብ ምርታማነት ማሳደግ

በኢትዮጵያ ውስጥ ለገጠር ሕዝብ የአኗኗር ዘይቤ መሰረት ከሆኑት ውስጥ አንዱና ዋነኛው የአርብቶ አደሩ ዘርፍ ሲሆን ይህም ዘርፍ ለእንስሳት ሀብት ልማት ትልቅ ድርሻ በማበርከት ላይ ያለ ነው፡፡ የእንስሳት ልማት ዘርፉን ምርታማነት ማሳደግ በተለይም የአርብቶ አደሩን ሕብረተሰብ ኑሮ በመለወጥ እንዲሁም አጠቃላይ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግ በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በአገር አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ገበያ እያደገ የመጣውን የእንስሳት ምርት ፍላጎት ተከትሎ የዘርፉን ምርታማነትና ገበያ ትስስር ማሻሻል የአርብቶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን ሕብረተሰብ ኑሮ ለመለወጥ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ለዚህም የግጦሽ መሬትን ማሻሻል፣በቂ የውሀ መጠጫ ቦታዎች አቅርቦት፣የእንስሳት ህክምናን ማሻሻል፣ እንደ መንገድ፣የውሀ ገንዳዎች፣ስልክና መብራት የመሳሰሉትን የመሰረተ ልማት አውታሮችን መዘርጋትና ለተሻለ ገበያ ዕድል የምርት ትስስር ዕድገት (value-chain) መፍጠር የአርብቶ አደሩን ሕብረተሰብ ኑሮ ለመለወጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የምርት ትስስር ሂደትን መሰረት ያደረገ የገበያ ግንኙነት እንዲዳብር በማበረታታት በአርብቶ አደሩ ዘንድ ገበያ ተኮር የሆነ የአመራረት ሂደት የተከተለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ በተጨማሪም የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ማጠናከርና በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ከአኗኗር ዘይቤያቸው ጋር በተጣጣመ መልኩ ማህበራዊ አገልግሎቶች ማለትም

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ትምህርት፣ስልጠና እንዲሁም የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ፣ዕውቀትና ችሎታን ለማዳበር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

### x) በከተሞችና በከተሞች አቅራቢያ የሚከናወኑ የግብርና እንቅስቃሴዎችን መደገፍ

በከተሞች እንዲሁም በከተሞች አቅራቢያ የተሻለ መረጃ እና የገበያ አቅርቦት በመኖሩ የከተማ ግብርና ለከተማ እና በከተሞች አቅራቢያ ለሚኖሩ ወጣቶች ጥሩ የገቢ ማስገኛ መንገድ ሆኗል፡፡ የከተማ ግብርና ከብቶችን በማድለብ፣ በወተት ልማት፣ በዶሮ እርባታ እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዙሪያ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል፡፡ አነስተኛ መጠን ያለው መሬት በመጠቀም በገበያ የሚፈለጉ ምርቶችን ማምረት ይቻላል፡፡ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በአንጻራዊ መልኩ ሲታይ ጥቂት ገንዘብ የሚፈልግ ሲሆን የከተሞችን ገበያ ለመቆጣጠር አቅም አለው፡፡ ይህንን እንቅስቃሴ ለመደገፍ የተቀናጀ ከተማ መስተዳድር ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

በዘርፉ የስራ ዕድል ፈጠራን ለማበረታታት የሚከተሉት ስትራተጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

- ለከተሞች ወይም በከተሞች አቅራቢያ ለሚካሄዱ የግብርና አገልግሎቶች የሚውሉ መሬቶችን መለየት፣
- በከተሞች እንዲሁም በከተሞች አቅራቢያ የሚመረቱ የግብርና ምርቶችን ጤንነት እና ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት የድጋፍ እርምጃ መውሰድ፣
- በከተሞች እና በየአቅራቢያቸው በግብርና ስራ የተሰማሩ ገበሬዎች ህብረት እንዲቋቋም አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፡፡

### xi) የግብርና ምርቶች ላይ ዕሴት በመጨመር ለገበያ እንዲቀርቡ ማበረታታት

በኢትዮጵያ በአብዛኛው በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ የማቅረብ ሂደት በጣም አጭር ከመሆኑም በላይ በሂደቱ ጥቂት ወይም ምንም ዕሴት ሲጨመር አይታይም፡፡ እንዲሁም የምርት ስርጭት መረቡ በጣም ረጅም፣ የተበጣጠሰ የገበያ ሥርዓት የሚከተልና ጥቂት ዕሴት በመጨመር የሚከናወን በመሆኑ ደካማ የሥራ ዕድል ፈጠራ የሚታይበት ነው፡፡ ዘርፉን የማስተባበር ችግር ከከፍተኛ የትራንስፖርት እና የሽቀጥ ልውውጥ ወጪ ጋር ተያይዞ በግብርና ግብዓት አቅራቢዎች፣ በነጋዴዎች፣ በገንዘብ አበዳሪዎች፣ በገበሬዎች እንዲሁም በትራንስፖርት አቅራቢዎች መካከል ተያያዥነት ያለው ኢንቨስትመንት እንዲካሄድ አያበረታታም ፡፡

ከግብርና ግብዓት አቅራቢዎች እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ እሴትን በመጨመር የማቅረብ ስርዓት አዲስ የስራ ዕድል እንዲሁም ምርታማ የስራ መስክ ለመፍጠር ያስችላል፡፡

በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ውጤታማ የስራ መስክ ለመፍጠር ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

- የሀገር ውስጥ የግል ኢንቨስትመንትን የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ጨምሮ በመስኩ የሚያበረታቱ ፓኬጆች መቅረጽና መተግበር፡፡ የማበረታቻ ፓኬጁ ዓላማ የግብርና ምርት የሚያቀነባብሩ የግል ኢንቨስትመንቶችን እና የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ የገንዘብ፣ የቴክኖሎጂ እንዲሁም የምክር አገልግሎት አቅርቦትን ለማበረታታት ነው፡፡
- በአቀነባባሪዎች ተፈላጊ የሆኑና ተቀባይነት ያላቸው የጥሬ ዕቃዎች የጥራት ደረጃዎችን ማዘጋጀት፡፡ ይህም በምርት አሰባበሰብ፣ በዘር አመራረጥና በዘር ማባዛት ዙሪያ ለሚካሄዱ የጥናትና ምርምር ስራዎች ትከረት መስጠትና ሀብት መመደብን ያካትታል፡፡
- የግብርና ንግድን ለማስፋፋት የቴክኒክና የገንዘብ አቅርቦት ድጋፍ ማድረግ፡፡ የግብርና ምርት አቀነባባሪዎች፣ የላኪዎችና ነጋዴዎች ማህበራት በምርት አቅርቦት መረብ ውስጥ በግብርና ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ እንዲቀርብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል አቅም በመፍጠር ድጋፍ ማድረግ፡፡

### xii) ከግብርና ውጪ ሥራ ስምሪትን የሚያፋጥኑ ዕርምጃዎችን መውሰድ

በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ በገጠር ከግብርና ውጪ የሚከናወን የስራ እንቅስቃሴ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ አማራጭ መንገድ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ከግብርና ውጪ የሚከናወን እንቅስቃሴ በገቢ ላይ መዋዠቅ ሲከሰት፣ በዕዳ ጫና እና በግብርና ስራ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች በመቋቋም ከድህነት ለመውጣት ከማገዙም በተጨማሪ የእርሻ መሬት ለሌላቸው ቤተሰቦች የገቢ ምንጭ ነው፡፡ ከግብርና ውጪ ያለው ዘርፍ ድሀ የህብረተሰብ ክፍሎችን በሥራ ገበያ በማቀፍ ዋነኛ የሥራ መስክ መሆን ይኖርበታል፡፡ የገጠር ሴቶች እና ወጣቶች ከግብርና ውጪ በሚከናወን የስራ መስክ ተሳትፎአቸው እንዲያድግ መበረታታት ያለበት ሲሆን፣ ይህም ገቢያቸው እንዲያድግ ያግዛል፡፡

እነዚህ ፕሮግራሞች ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት ከመቀነስም በተጨማሪ ከመሬት መበጣጠስ ጋር ተያይዞ የሚከሰት ችግርን እና ዝቅተኛ የግብርና ምርታማነትን በገጠሩ አካባቢ ለማሻሻል ይረዳሉ፡፡ የግብርናው ተረፈ ምርት ማደግ ከግብርና ውጪ ያሉ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ እንቅስቃሴዎችን (upstream & downstream activities) ያበረታታል፡፡

ከግብርና ውጪ ያሉ የገጠር የስራ እንቅስቃሴዎችን ለማስፋፋት የሸማኔዎች፣ የነጋዴዎች፣ የብረታ ብረት ሰራተኞች እና የአቀነባባሪዎች ማህበራት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡

### 2.3.3.2 ከግብርና ውጪ የግል ዘርፍ እና መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ ምርታማነት ማሳደግ

ከግብርናና ከፐብሊክ ሴክተር ጎን ለጎን ከግብርና ውጪ ያሉ የግል ዘርፍ እና መደበኛ ያልሆነው ሴክተር ለብዙ ኢትዮጵያውያን የስራ ዕድል አስገኝተዋል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአማካይ 71 በመቶ የከተማ ሰራተኞች መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማሩ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ናቸው፡፡ ስለሆነም ከግብርና ውጪ የግል እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ ምርታማነትን በማሳደግ በዘርፉ የተሰማራውን የሰው ኃይል ገቢ በማሻሻል ሠራተኛ የሆኑ ድሆችን (Working poor) ችግር ለመፍታት ይቻላል፡፡

ከግብርና ውጪ ባሉ እንደ ኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ ያለው አምራች ኃይል የክህሎትና ዕውቀት ደረጃ ካደገ ምርታማ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር የሚቻል ከመሆኑም በላይ ምርታማነትን በማሳደግ በሀገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ የዘርፉን የመወዳደር አቅም ያጎለብታል፡፡

የዘርፉን የሰው ኃይል ምርታማነት ለማሳደግ መደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ከአገሪቱ የእውቀትና የክህሎት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን እና የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎችን ቁጥር በብዙ ዕጥፍ አሳድጎታል፡፡ ይህ የተማሪዎች ቁጥር ከተፈጠረው የስራ ዕድል ጋር በተለይም መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ጋር ሊመጣጠን ባለመቻሉ እንዲሁም በትምህርት ጥራት ላይ ከተከሰተው ችግር እና ከሥራ ገበያ ፍላጎት አለመጣጣም ጋር ተያይዞ ችግሩን የጎላ አድርጎታል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ችግር ለመቅረፍ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡

- ተከታታይ የሥራ ገበያ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች የስልጠና መርሀ-ግብር በገበያው የሚፈለገውን የእውቀት ዓይነትና የጥራት ደረጃ ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲን (Higher Education Relevance and Quality Agency-HERQA) በማጠናከር በከፍተኛ የትምህርት ዘርፍ የሚፈለገው የጥራት ደረጃ እንዲያረጋግጥ ማድረግ፤
- መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ አቅም በመገንባት እና በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በማስገባት ከመደበኛው የግል ዘርፍ ጋር ማቀናጀት፡፡

አበረታች የፖሊሲ እርምጃዎችን በመተግበር እንዲሁም አቅርቦትን፣ እውቀትን፣ እና ቴክኖሎጂን በማሻሻል መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች ምርታማነት እና የመወዳደር አቅም በማሳደግ በኑሮ ሁኔታ ላይ በጎ ተፅዕና ማምጣት ይቻላል፡፡ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ ሰራተኞችን ምርታማነት ለማሻሻል የመሠረታዊ ሀብቶች አቅርቦት ማለትም መሬት፣ ገንዘብ፣ ገበያ፣ መሠረተ-ልማት እንዲሁም በአመራረት ዘይቤ፣ በገበያ እና በንግድ ዙሪያ የስልጠና አገልግሎት ማቅረብና ማህበራዊ ዋስትናን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ ከመደበኛ ዘርፍ ጋር እንዲሁም ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ ሸቀጦች ጋር መወዳደር እንዲችል በቴክኖሎጂ አቅርቦትና በዘመናዊነት ዙሪያ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ዕውቀት-ተኮር ቴክኖሎጂ፣ ዘመናዊ ስራ አመራር እና የመረጃ አጠቃቀም የአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማትን ወይም መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ምርት እና አገልግሎት ተወዳዳሪነት በማሻሻል ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የመሠረታዊ ሀብት አቅርቦት እና ተቋማዊ ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ መንግስት መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ፣ ለተሻሻሉ የኢንዱስትሪ አመራረት ዘዴዎች በአጠቃላይ ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ እንዲሆኑ መደገፍ ይኖርበታል፡፡

የመንግስት ተቋማት ለምሳሌ የፌደራል አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት ልማት ኤጀንሲ እና ተጓዳኝ የክልል ተቋሞችን አቅም በማጠናከር በቴክኖሎጂ ምንጮች ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ በማከናወን እንዲሁም ሰርቶ ማሳያዎችን በመጠቀም ቴክኖሎጂዎችን የመገምገምና የመፈተሽ አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 2.3.3.2.1 ከግብርና ውጪ እና መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ የተቀየሱ ስትራተጂዎች

የዚህ ስትራቴጂ ዋነኛ ዓላማ ከመንግስት ተቋማት ውጭ በሀገሪቱ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ መካካል የተፈጠረውን ችግር ማስወገድ ነው፡፡ ይህም መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ከግብርና ውጪ ዘመናዊ ዘርፍ ጋር በማቀናጀት ይከናወናል፡፡ ስለሆነም መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተቀመጡ የምርታማነት ችግሮችን መቅረፍ በተዘዋዋሪ ከግብርና ውጪ ያለ ዘርፍ የሰው ኃይል ምርታማነት ክፍተትን ለመሙላት ያስችላል፡፡

መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ለመደገፍ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስትራተጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

#### i) መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ የሥራ ቅልጥፍና ለማሻሻል ግልጽ መመሪያ ማውጣት

መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ በብዛት መገኘት በመደበኛው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚሳድር ቢሆንም መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ግልጽ በሆነ የአሰራር መመሪያ መደገፍ አለባቸው፡፡ የመመሪያው መኖር ስጋቶችን በማስወገድና መተማንን በመፍጠር በነጻነት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡ ይህም በዘርፉ ለተሰማሩት የሥራና የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን በመፍጠር ረገድ ጠቀሜታ አለው፡፡

#### ii) ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ

መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማራው አብዛኛው የሰው ኃይል ያለው ሙያዊ ክህሎት ወይም በሥራ ገበያ ያለው ተፈላጊነት ውስን በመሆኑ መንግስት የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀትና ሌሎች የቢዝነስ ድጋፎችን በማድረግ የዘርፉን ዕድገት ማፋጠን አለበት፡፡ የሚዘጋጁ ስልጠናዎችም በመሠረታዊ የአመራረት ክህሎት፣ በማርኬትንግ፣ እንዲሁም የፋይናንስ ሀብትን ጨምሮ በንብረት አመራር ላይ ማተኮር አለባቸው፡፡ ከግሎባላይዘሽን እና በመረጃና ኮሙኒኬሽን

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

መስፋፋት ጋር ተያይዞ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠ የመጣውን የኢኮኖሚ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚሰጡ ስልጠናዎች የኮምፒዩተርን ዕውቀት፣ የኢንተርኔት አጠቃቀምንና በኤሌትሮኒክ የተደገፈ የንግድ ልውውጥን (e-commerce) ያካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

iii) የመስሪያ ቦታ አቅርቦት

የመስሪያ ቦታ አቅርቦት ችግር፣ የመስሪያ ቦታን ለመረከብ የሚፈጀው ጊዜ እና ለመስሪያ ቦታ የሚከፈለው ገንዘብና ሌሎች የማረካከቢያ ወጪዎች መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነው የግሉ ዘርፍ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ካሳደሩ ችግሮች ተርታ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የህንጻዎች ኪራይና የሊዝ ዋጋ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎችና የጥቃቅን መደበኛ ንግድ ባለሀብቶች  የመስሪያ ቦታን በጨረታ የማግኘት ዕድል እጅግ ጠባብ ነው፡፡ ለመስሪያ የሚውል ቦታ ጨረታ አልፎ አልፎ የሚካሄድ ከመሆኑም በላይ እጅግ ውድ ነው፡፡ ስለሆነም መንግስት የመሬትና የመስሪያ ቦታዎች አቅርቦትን (በተመጣጣኝ ዋጋ) ለማሻሻል የሚያስችል ተገቢ የፖሊሲ ዕርምጃ  መውሰድ ይኖርበታል፡፡

iv) የፋይናንስ አቅርቦት

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ ፈቃድ ያላቸው 25 አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የገንዘብ ተቋማት አነስተኛና የሽፋን ደረጃቸውም ውሱን ነው፡፡ አነስተኛና በማደግ ላይ የሚገኙ የንግድ ተቋማት ከአነስተኛ የገንዘብ ተቋማት አቅም በላይ ከፍተኛ ገንዘብና የረጅም ጊዜ ብድር ይፈልጋሉ፡፡ መደበኛ የገንዘብ ተቋማት (ንግድ ባንኮች) መደበኛ ላልሆኑ ዘርፎች በሚሰጠው ብድር አዋጪነት ላይ እምነት ስለሌላቸውና አስተዳደራዊ ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ (high transaction cost) ገንዘብ ለማበደር ፈቃደኞች አይደሉም፡፡

ስለሆነም መደበኛ ያልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ አዲስ የስራ ዕድል በመፍጠር የድሆችን የገቢ መጠን የሚያሻሽል በመሆኑ አነስተኛ የገንዘብ ተቋማትን በማሳደግ ሽፋናቸውን ማስፋት፣ የተቋማቱን የማበደር አቅምና ብድርን የመሰብሰብ ዘዴ በማሻሻል ዘርፉን መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ አገሮች መደበኛው የባንክ ዘርፍ ከሚያበድረው አጠቃላይ ገንዘብ ውስጥ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች ማለትም ለግብርና፣ ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች እና ለአገልግሎት ዘርፎች የሚሰጥ ብድር እንዲመድቡ የሚያስገድድ ህግ አውጥተዋል (ለምሳሌ በህንድ ከአጠቃላይ ብድር ውስጥ 40 በመቶ ቅድሚያ ለተሰጣቸው ዘርፎች የተመደበ ነው)፡፡

በዚህ ረገድ አዳዲስ አገልግሎቶች ለምሳሌ ለስራ የሚውል ገንዘብ ብድር፣ የውጭ ምንዛሬ አግለግሎት፣የቴክኖሎጂ ልማትና ዘመናዊ ፈንድ አስተዳደር ተግባራዊ መሆን አለባቸው፡፡

v) ማህበራትን ማቋቋም

መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የሚሰጠውን የድጋፍ አገልግሎት ለማቀላጠፍና ውጤታማ ለማድረግ፣ በአባላት መካከል አጋርነትና ቅንጅትን ለመፍጠር፣ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በራሳቸው ለመፍታት እንዲችሉና መብታቸውንም እንዲያስከብሩ ስለሚረዳ መንግስት መደበኛ ባልሆነው

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ዘርፍ የተሰማራው የሰው ኃይል በማኅበር እንዲደራጅ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ አንቀሳቃሾች (Operators) በተለያየ መልኩ መደራጀት ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ድጋፎችንና አገልግሎቶችን በቀላሉ ለመለየትና በተቀላጠፈ መልኩ ለመስጠት ያስችላል፡፡

vi) ምቹ የስራ ሁኔታ መፍጠር

መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ መንግስት ባወጣቸው የአሰሪና ሠራተኛ ህጎች ወይም በሠራተኞች ማህበራት ተገቢው ከለላ ስለማይደረግለት ምቹ የስራ ሁኔታን (Decent work) በመፍጠር ረገድ በዘርፉ የተሰማራው የሰው ኃይል ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም፡፡ ይህም የሆነው የዘርፉን የስራ ሁኔታ ለመቆጣጠርና አስፈላጊውን የሌበር ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ እና በተለየ ሁኔታ በዘርፉ የተሰማሩ ሠራኞችን መብት ለማስከበር የወጣ ህግና መመሪያ ባለመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ አሰሪዎችና ሠራተኞችን መብት ለማስከበር የህግ ማዕቀፍ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህ የሚዘጋጀው የህግ ማዕቀፍ መደበኛ ላልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ ዕውቅና በመስጠት በዘርፉ የተሰማሩ ሠራተኞችን የስራ መብት የሚያስከብርና አስፈላጊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ለምሳሌ የስራ ቦታ አቅርቦት፣ ሰራተኞች ተደራጅተው በተወካዮቻቸው አማካይነት በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ የሚችሉበትን ሁኔታ፣ ወ.ዘ.ተ ማካተት ይኖርበታል፡፡ ስለምቹ የሥራ ሁኔታና ስለመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ለሕብረተሰቡ በማሳወቅ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራኞችን መብት ማስጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

2.3.4 የሥራ ገበያ ተቋማትን ማጠናከር፣ የአሰሪና ሠራተኛ አስተዳደርን ማሻሻል እና የሥራ ገበያ አገልግሎትን ማስፋፋት

የሥራ ገበያ ተቋማት የሚባሉት የመንግስት አካላት ማለትም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የክልል ተጓዳኝ ቢሮዎች፣ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ፍርድ ቤቶች፣ የሠራተኞች እና የአሰሪዎች ማህበራት ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት በመመሪያዎችና ህጎች ላይ በመመርኮዝ የሰራተኞችን መብትና ጥቅም ማለትም በደመወዝ ክፍያ፣ በጥቅማጥቅሞች፣ በደረጃ ዕድገት እና በሌሎችም መብቶች ዙሪያ ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡

ይሁን እንጂ በእነዚህ ተቋማት የሰራተኞችን መብት የማስከበር ተግባር በመንግስት የልማት ድርጅቶችና በጥቂት የግል ተቋማት ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ መደበኛ ባልሆነ እና በአነስተኛ የግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ ሰራተኞች ምንም ዓይነት መብትን የማስከበር ሁኔታ የለም፡፡ መንግስታዊና እና የግል የሥራ ስምሪት አገልግሎቶች እጅግ ደካማ በመሆናቸው መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንኳ (ለምሳሌ ለስራ ፈላጊዎችና ለቀጣሪዎች መረጃ የመስጠት ተግባር) ሲያከናውኑ አይታይም፡፡

በመንግስታዊ እና በግል መደበኛ ዘርፍ የተሰማሩ ሁሉም ሠራተኞች በበለጠ ውጤታማ የሆኑ የሠራተኞች ማህበራትን እንዲያቋቋሙ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የመደበኛ ዘርፍ አሰሪዎች

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ወይም ቀጣሪዎች አሁን ባለው የአሰሪዎች ማህበር ውስጥ እንዲገቡ እና በማህበራዊ የምክክር መድረኮች እንዲሳተፉ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጥበቃ የሚያደርጉ አግባብነት ያላቸው ተቋማት ሊቋቋሙ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተቀጠሩ ሰራተኞችን የሚደግፍ እና በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የውይይት መድረኮች ላይ የሚወክላቸው ማህበር መቋቋም ይኖርበታል፡፡ አሁን ባለው የሠራተኞች ማህበር ውስጥ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ ሰራተኞቸ የሚወከሉበት አግባብ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞችን መብት ለማስከበር የሚረዳ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ረገድ አሁን በመተግበር ላይ የሚገኘውን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አድማስ በማስፋት፣ የሕብረት ድርድርና ስምምነቶችን በማካተት፣ የሥራ ሁኔታ ስታንዳርዶችን ተግባራዊ በማድረግ፣ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ዘርፎች ለተሰማሩ ሰራተኞች በእኩል የሚያገለግሉ ፖሊሲዎችን በመንደፍ እና ለአፈጻጸሙ የሚረዱ ሥርዓቶችንና ተቋማት (Mechanisms & Institutions) በመመስረት ህጉ ሰፊ ሽፋን እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡

በግብርናና ከግብርና ውጪ ባሉ የስራ መስኮች እና መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ የተሰማሩትን ወጣቶች፣ ሴቶችና ድሃ ቤተሰቦችን ዒላማ ያደረገ ቀልጣፋ የሥራ ገበያ መረጃ አገልግሎት ለመስጠት የፌደራል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና የክልል ተንዳኝ ቢሮዎች አቅም ሊጠናከር ይገባል፡፡ ይህም የሙያ ምክር አገልግሎትን፣ የስምሪት ዕገዛን፣ ሙያና ሙያተኛ ማገናኘትን፣ አሰሪና ሠራተኛ ማገናኘትን፣ ለአሰሪና ሠራተኛ ማህበራት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትንና የሥራ ገበያ መረጃዎች ማዘጋጀትና ማሰራጨትን፣ ወ.ዘ.ተ በማካተት የተቀናጀ የስራ ስምሪት አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም የቀጣሪ ድርጅቶችን ፍላጎት ከትምህርትና ስልጠና ስርዓት ጋር በሚያገናኝ የሙያ ስልጠና ፕሮግራም አማካኝነት ሊቀጠር የሚችል የሰው ኃይል የሙያ መሠረት (Skill-base) ሊፈጠር ይገባል፡፡

መንግስት የሥራ ገበያ ተቋማትን በማጠናከርና በማቋቋም ላይ ትኩረት ላደረጉ እንቅስቃሴዎች እንዲሁ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

### 2.3.4.1 የአሰሪና ሠራተኛ አስተዳደር እና የሥራ ገበያ ተቋማትን የማጠናከር ስትራቴጂዎች

በኢትዮጵያ የሥራ ገበያን ለማስተዳደር የተመሠረቱ ተቋማት ገና ብዙም ያላደጉ ናቸው፡፡ የሠራተኞችን መሠረታዊ መብቶች ከማስጠበቅ፣ የሠራተኞችን ደህንነት፣ የመደራጀት ነጻነት፣ እኩልነትና ሰብዓዊ ክብርን ከማረጋገጥ አኳያ ገና ብዙ አልተሰራም፡፡ አሁን ያሉ የአሰሪና ሰራተኛ ሕጎችና ተቋማዊ አገልግሎቶች መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ተፈጻም አይደሉም፡፡ አብዛኞቹ የምቹ የስራ ሁኔታ መገለጫዎች በግሉ ሴክተር በክፍያ በሚሰሩ ሠራተኞች ዘንድ አይታወቁም፡፡ አነስተኛ የመነሻ ደሞዝ (Minimum wage) በአብዛኛው በመደበኛው የሥራ ዘርፍ በተሰማራው ያልሰለጠነ ሠራተኛ ዘንድ ተፈጻሚ አይደለም፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በአሰሪና ሠራተኛ ህጎችና አስተዳደሮች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የመንግስት ተቋማት ከሠራተኛ ማህበራት፣ ከአሰሪዎች ማህበራት፣ከንግድ ማህበራት እና ከወጣቶችና ከሴቶች አካላት ጋር በቅርበት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ አነስተኛ የመነሻ ደሞዝ አሰራር በግሉ ሴክተር ለተሰማሩ ሰራተኞችም እንዲሁ መውጣትና ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

የሚከተሉት ስትራቴጂዎች የሰራተኛውን መብትና ጥቅም በይበልጥ ለማሻሻል ተቀይሰዋል፡፡

i) የሠራተኛ ጥበቃንና ምቹ የሥራ ሁኔታን ማረጋገጥ

አብዛኞቹ የክፍያ ስራዎች ዋስትና የሌላቸውና ጊዜያዊ ሲሆኑ የግል ስራ (Self-employment) ደግሞ ጥሩ ገቢን አያስገኝም፡፡ የሠራተኞችን መሠረታዊ መብትና ፍላጎት ለማስከበርና ሰራተኞችን ካልተገባ አያያዝ ለመጠበቅ በሥራ ገበያ ስርዓት ውስጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ከገደብ ያለፈ ጥበቃ ሠራተኞችን ከሥራ ለማባረር (Firing) ከሚጠይቀው ወጪና በጊዜያዊ ኮንትራቶች ላይ በሚደረገው አላስፈላጊ ዕገዳ የተነሳ የሠራተኛ ቅጥር ፍላጎትን እንደሚቀንስ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

ድሃ-ተኮር ዕድገትን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድሃውን ሰራተኛ (Working poor) ጨምሮ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካተውና መሰረተ ሰፊ ውይይትና ተሳትፎን ተከትለው ከተቀረጹና ከተተገበሩ ስኬታማ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡ የሥራ ገበያ ስርዓት በተፈለገው መልኩ እንዲታዘዝ (Labour market flexibility) እና የስራ ስምሪት ጥበቃ እንዲረጋገጥ ከተደረገ የሥራ ገበያ ስርዓቱ ከለላ ያገኛል፡፡

የሠራተኛን ጥበቃና ምቹ የስራ ሁኔታን ለማረጋገጥ ከሚወሰዱ ስትራቴጂዎች መካከል የሚከተሉት ተቀይሰዋል፡፡

- በየጊዜው አነስተኛ የመነሻ ደሞዝ መጠንን ለመገምገም የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና የዋጋ ግሽበትንና የገበያ ክፍያዎችን (Market wages) በማገናዘብ መጠኑን ማሻሻል፣

- አነስተኛ የመነሻ ደሞዝ አሰራር ሰፊ ሽፋንና የተሻለ አፈፃፀም እና ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያረጋግጥ የተቋም አደረጃጀት መገንባት፣

- የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችን የአሰራር ሁኔታ ለመከታተልና ደህንነቱ የተጠበቀና ተቀባይነት ያለው የጥራት ደረጃ ስራ ላይ ለማዋል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርንና ተጓዳኝ የክልል ቢሮዎችን አቅም መገንባት፣

- ሴቶች በተሻለ ደረጃ የመደበኛው ዘርፍ (በተለይም የመንግስት ዘርፍ) የስራ ስምሪት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የሚያስችል ለሴቶች ቅድሚያ የሚሰጥ አሰራር (Affirmative action) መዘርጋት፣

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ii) ***የሥራ ገበያ አገልግሎትን ማሻሻል***

*በዚህ ረገድ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ተጓዳኝ የክልል ቢሮዎች የሚከተሉትን ስራቴጂዎች መከተል ይኖባቸዋል፡-*

- *የሥራ ሁኔታ ደረጃ፣የሙያ ጤንነትና ደህንነት ወ.ዘ.ተ በተመለከተ መመሪያ በማውጣት የሰው ኃይል ጉዳዮችን በአግባቡ መቆጣጠር፣*

- *የሠራተኛ ማህበራትን መመዝገብ እና ለማህበራቱ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት መስጠት፣*

- *አለመግባባቶችን ውጤታማ በሆነ መልኩ የመፍታት አሰራርን ማስተባበርና ማገዝ፣*

- *በሰው ኃይል፣ በስራ አጥነትና በሥራ ስምሪት ሁኔታ ላይ በየጊዜው የሚካሄዱ ጥናቶችን ማስተባበር፣*
- *የሰው ኃይል፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ማጠናቀርና ማሰራጨት፣*

*የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ተጓኝ የክልል ቢሮዎች አሁን ያለባቸውን ኃላፊነት ከመወጣት ጎን ለጎን ውጤታማ እና ጊዜና ገንዘብን ቆጣቢ የሥራ ገበያ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ለመስጠት እንዲችሉ የሚከተሉትን ስትራቴጂዎች መከተል ይኖባቸዋል፡፡*

- *የአስተዳደር ሚና ሳይሆን የስራ አማካሪ ወይም የስራ ስምሪት አማካሪ ሚናን የሚጫወቱ የስራ ማዕከላትን* (Job centers) *ማቋቋም፡- በኢትዮጵያ በትውውቅ የሚደረጉ የሰራተኛ መረጣና ቅጥር መደበኛ ካልሆኑ አሰራሮች መካከል የተለመዱ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ አሰሪዎች ብቁና ለስራው የሚመጥኑ ሰራተኞችን ሁልጊዜ ማግኘት አይችሉም፡፡ በተመሳሳይም ብቁ ሰራተኞች የሚፈለገው ትውውቅና ግንኙነት* (Network) *ከሌላቸው ተገቢውን ስራ አያገኙም፡፡ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ተጓዳኝ የክልል ቢሮዎች መንግስታዊ የስራ ማዕከላትን ሲያስተዳድሩ የግሉ ዘርፍ ተቋሞች የራሳቸውን የስራ ማዕከላት ሊያስተዳድሩ ይችላሉ፣*

- *የግሉ ዘርፍ የስራ ስምሪት ማዕከላትን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያዎች ብቁ የሆኑ ሠራተኞችን የማቅረብ አቅም ለማጠናከር የድጋፍና የቁጥጥር ስርዓት መገንባት፣*

- *ከከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት (ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች) ጋር ቅንጅት በመፍጠር በጋራ መስራት፤ የዚህ ዓላማ የስልጠና ተቋማት በገበያው ተፈላጊ የሆኑ ሙያዎችን* (Right-skills) *እንደሚያስጨብጡ ማረጋገጥ፣ በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ወይም በጂኦግራፊያዊ፣ በስራና በችሎታ አለመጣጣም የሚከሰተውን ስራአጥ*

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ወደ ሌላ ቦታ በማዘዋወር እንዲሰራ ማስቻልና የስራ አጦችንና የሥራ ገበያ ስርዓትን ቁርኝት ማረጋገጥ ናቸው፣

- አስፈላጊውን የሥራ ገበያ መረጃ ለሕብረተሰቡ ከሚያመነጩ ጥናቶች የጊዜ ሠሌዳ ጋር በተጣጣመ መልኩ በየጊዜው (በዓመት ከተቻለም በመንፈቅ) የሥራ ገበያ አመልካቾችን ማመንጨትና ማሰራጨት፣

- ቀልጣፋ የሥራ ገበያ አገልግሎት መስጠት፡- ቀልጣፋ የሥራ ገበያ አገልግሎቶች የሠራተኛን ሙያዊ ክህሎትና ምርታማነት ለማሻሻል፣ የደሞዝ ድጎማ ለማድረግና የስራ ፍለጋ ቅልጥፍናን ለማሻሻል አስፈላጊ ናቸው፡፡ ይህን በማድረግ የሥራ ገበያ አገልግሎት አሰጣጥ ምርታማ የስራ ስምሪት እንዲኖር ያስችላል፡፡ ነገር ግን ቀልጣፋ የሥራ ገበያ አገልግሎቶች የበጀት ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ እነዚህ ፕሮግራሞች በአጠቃላይ የሰው ኃይልን በሰፊው በመጠቀም የሚመጣ የኢኮኖሚ ዕድገት (Labour-intensive economic growth) ሚናን እንዲተኩ አይጠበቁም፡፡

iii) **መደበኛ ያልሆነው የስራ ዘርፍን ጨምሮ የግል ሰራተኞች ህብረትና ማህበራት እንዲመሰረቱ ድጋፍ መስጠት**

የአርሶ አደሮችንና መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ሰራተኞችን መብትና ፍላጎት ለማስጠበቅ የቆመ ደጋፊ አካል በሌለበት ድህነትን የማስወገድ ዓላማ ግቡን ሊመታ አይችልም፡፡ የአነስተኛ አርሶ አደሮችና መደበኛ ያልሆነው የስራ ዘርፍ ሰራተኞች ያልተደራጁ በመሆናቸው የመደራደር ኃይላቸው ደካማ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ስለሆነም የአገር ውስጥ የንግድ ሚዛን ለገበሬዎች፣ ለግል ስራ ሰራተኞችና መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ላይ ለተሰማሩት ሰራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ጥሩ አይደለም፡፡

እነዚህ አካላት አብዛኛውን የሕዝብ ቁጥር የሚሸፍኑ እንደመሆናቸው ድምጻቸው እንዲሰማ ግብርናንና መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ትኩረት ያደረገ የድጋፍ ፕሮግራም ሊቀረጽ ይገባዋል፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተግባራዊ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

- በአገር አቀፍና በአካባቢ ደረጃ የገበሬ ማህበራት እንዲቋቋሙ ቴክኒካዊ፣ተቋማዊና የፖሊሲ ድጋፍ መስጠት፣

- በከተማና በገጠር መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ማህበራት እንዲቋቋሙ ቴክኒካዊ፣ ተቋማዊና የፖሊሲ ድጋፍ መስጠት፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

### 2.3.5 የመድብለ ዘርፍ ጉዳዮች፡- የፖሊሲ እርምጃ አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

#### 2.3.5.1 የስነ ሕዝብ አወቃቀር ሽግግር (Demographic transition) ማምጣት

ዕድገትን ለማፋጠን፣ የስራ ዕድልን ለመፍጠርና ድህነትን ለመቀነስ የሚደረግ የመዋቅር ለውጥ፤ የህዝብ ዕደገትን በመቀነስ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት ጋር በማጣጣም የነፍስ ወከፍ ገቢ በፍጥነት እንዲጨምር ማስቻልን ይጠይቃል፡፡ ከፍተኛ የሕዝብ ዕድገት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን በማበረታታት በተለይም በከተማ የወጣቶች ስራ አጥነት እንዲጨምር የራሱን አስተዋጽኦ አድርጎል፡፡ ጠንካራ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ተከትሎ የሚመጣ የተሻለ ትምህርት፣ የጤና ሽፋንና ማህበራዊ-የባህል ለውጥ ለውጤታማነታቸው ቁልፍ እንደሆነ የስነ ሕዝብ አወቃቀር (Demographic) ለውጥ በማምጣት ስኬታማ የሆኑ አገራት ተሞክሮ ያመለክታል፡፡

##### 2.3.5.1.1 የስነ ሕዝብ አወቃቀር (Demographic) ለውጥ ስትራቴጂዎች

መንግስት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ከማሻሻል ጎን ለጎን የወሊድ መጠንን ለመቀነስ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ይህም የጋብቻ ህጎችን በማጽደቅና በመተግበር ሴቶች የመጀመሪያ ልጃቸውን የመውለጃ ዕድሜ በተወሰነ ደረጃ ከፍ ማድረግና ሴቶች በጋብቻና በወሊድ ላይ በሚደረግ ውሳኔ የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሴቶችን የትምህርትና የስራ ዕድሎችን ማሳደግ፡፡ በተጨማሪም የወሊድ መቆጣጠሪያ ፍላጎትን በማሟላት ያልተፈለገ እርግዝናን ለመቀነስ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡

#### 2.3.5.2 ግሎባላይዜሽን የሚያስከትላቸውን የስራ ስምሪት ፈታኝ ሁኔታዎች መግታት

ግሎባላይዜሽን የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰትን በመጨመር ለአገር ውስጥ የስራ መስኮች መፈጠር ዕድሎችን ይከፍታል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያለ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በጠንካራ ተወዳዳሪነት የአገር ውስጥ ድርጅቶችን ከስራ ውጭ ካደረገ የሚፈጥረው የስራ ዕድል ምናልባት ከሚያስከትለው የስራ አጥነት ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ መንግስት የተሻሻለ የምርታማነት ዕድገት ለማምጣት፣ የመሰረተ ልማትን የበለጠ በማሻሻልና አመቺ የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎችን የመቅረጽ እርምጃዎችን በመውሰድ ከግሎባላይዜሽን የሚገኘውን ዕድል በአግባቡ ለመጠቀም የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን መደገፍ ይኖርበታል፡፡ ግሎባላይዜሽን ለስራ ፈጠራና ለድህነት ቅነሳ ያለው ጥቅም በውጭ ቀጥተኛው ኢንቨስትመነት ዓይነት፣ ለግብይት በሚቀርቡ ምርቶችና በድርጅቶች የተወዳዳሪነት አቅም ላይ በእጅጉ የተመሠረተ ነው፡፡

##### 2.3.5.2.1 ግሎባላይዜሽን የሚያስከትላቸውን የስራ ስምሪት ፈታኝ ሁኔታዎች የመግታት ስትራቴጂዎች

ውጤታማ በሆነ መልኩ የግሎባላይዜሽን ተጽዕኖዎችን በአግባቡ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተቋማትና ሥርዓት እጥረት የዓለም መገለጫ ባህሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ግሎባላይዜሽን በማደግ

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ላይ ባሉ ሀገሮች የስራ ዕድልን ከመሸርሸር አኳያ ያለው አሉታዊ ተጸዕኖ ከፍተኛ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ የዓለም አቀፍ ተዋናዮችን እንቅስቃሴ በተገቢው ለመከታተልና የስራ ስምሪት ውጤቶችን በየጊዜው በመገምገም የስራ ስምሪትን በዘዴ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለማስቀመጥ በብሔራዊ ደረጃ የአሰራር ስልትና የጥራት ደረጃ መለኪያ ማስቀመጥ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በክፍል 2.4.3 በተጠቀሱት ስትራቴጂዎች አማካኝነት የሰራተኛውን ኃይል ችሎታና የምርታማነት ደረጃ ማሳደግ የአገር ውስጥ የሰራተኛ ኃይልን ተወዳዳሪነት ለማሻሻል ይረዳል፡፡ ዓለም አቀፋዊ የስራ ቋንቋ የሆኑትን እንደ እንግሊዝኛና ሌሎች በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ቋንቋዎችን እንደ ቻይንኛ፣ ጃፓንኛና አረብኛን እንዲሁም የኮምፒዩተር ትምህርትና የተሻሻለ የስራ ባህል በማስተማር የሰራተኛ ኃይሉን የመግባባት ችሎታ ማሳደግ፤ የአገር ውስጥ የሠራተኛ ኃይል ለዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ባለብቶች ያለው መስህብነት እንዲጨምር የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የሠራተኛውን ኃይል የጤና ሁኔታ መጠበቅና ማሻሻል ሌላኛው የሠራተኛውን ኃይል ተወዳዳሪ የማድረጊያ መንገድ ነው፡፡

### 2.3.5.3 የተዘዋዋሪ ሠራተኞችን መብት ማስከበር

በቅርብ ዓመታት ለስራ ፍለጋ ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ አገራት በተለይም ወደ መካከለኛው ምስራቅና ደቡብ አፍሪካ የሚፈልሰው ያልሰለጠነ የሰው ኃይል እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህም የሰው ኃይል እንቅስቃሴ በአገር ውስጥ ያለውን የሥራ አጥነት ጫና በተወሰነ ደረጃ ለመቀነስ ረድቷል፡፡

ግሎባላይዜሽን ለኢንተርናሽናል የሰው ኃይል እንቅስቃሴ ዋነኛ የሚገፋፋ ምክንያት እየሆነ መጥቷል፡፡ ነገር ግን በተለይም ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለሚፈልሱ ወጣት ሴቶች የተፈጠረው የስራ ዕድል በአብዛኛው በቤት ውስጥ ስራ ላይ የተገደበ ነው፡፡ በግለሰብ ቤት ውስጥ ተገድበው በዝቅተኛ ደሞዝ ተቀጥረው ለረጅም ሰዓትና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶም ለጥቃትና ምዝበራ ይጋለጣሉ፡፡ ስለዚህ አሁን የሚገኘውን የስራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ 632/2001 በአግባቡ መተግበር ለስደተኛ ሰራተኞች መብት መከበር ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

#### 2.3.5.3.1 የተዘዋዋሪ ሠራተኞችን መብት የማስከበር ስትራቴጂዎች

የተዘዋዋሪ ሰራኞች መብትን በማስከበር የስራ ዕድሎችን ለማጠናከር የሚከተሉት ስልቶች አስፈላጊ ናቸው፡-

- ስለሚሄዱበት አገር መረጃ መስጠትና ግንዛቤ ማስጨበጥ፡- ተዘዋዋሪ ሰራተኞች በተለይም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚወጡት ስለሚሄዱበት ቦታ፣ የስራ ሁኔታና ጥቅም የመረጃና የግንዛቤ ዕጥረት ስላለባቸው በተሳሳተ መንገድ በመመራት በማያውቁት ሁኔታ ላይ ውሳኔ ወደ መስጠት ይሄዳሉ፡፡ እንዲህ ያሉ ተዘዋዋሪ ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ አደጋ ላይ ይወድቃሉ፡፡ ስለዚህም ተገቢውን የሥራ ገበያ አገልገሎት መስጠትና

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ለተዘዋዋሪ ሠራተኞች አገራቸውን ከመልቀቃቸው አስቀድሞ በተቀናጀና በተደራጀ አሰራር ስለሚሄዱበት አገር የሚገባውን ማሳወቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

- የግል የስራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥን መቆጣጠር፡-በሰው ኃይል ዝውውር ላይ የተሰማሩ የግል የስራ ስምሪት አገልግሎት ሰጪዎች በህጋዊ መንገድ ሊመዘገቡና ዕውቅና ሊሰጣቸው ያስፈልጋል፡፡ ማንኛውንም አግባብ ያልሆነ ተግባር ሲፈፅሙ ቢገኙ ለድርጊታቸው ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል፡፡

- የሥራ ገበያ መረጃ የሚሰጡ ማዕከላትን ማቋቋም፡- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ተጓዳኝ የክልል ቢሮዎች ለተዘዋዋሪ ሠራተኞች ስለሚሄዱበት ሀገር ጠቃሚ የሥራ ገበያ መረጃ የሚሰጡ የአገልግሎት ማዕከላትን ማቋቋም ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.3.5.4 ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን መግታት

ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት በኢትዮጵያ ያለውን የአገር ውስጥ የሰው ኃይል ፍልሰት በእጅጉ የሚወክል ነው፡፡ ለገጠር-ከተማ ፍልሰት የሚገፋፉ ምክንያቶች የመሬት ጫና (የመሬት መራቆት)፣ የአካባቢ መጎሳቆልና ድህነት ስራና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን ፍለጋ ወደ ከተማ የሚደረገውን ጊዜያዊና ቋሚ ፍልሰት የሚያባብሱ ናቸው፡፡ ያልተማሩ፣ ዕድሜያቸው ለስራ ገና ያልደረሰና ዝቅተኛ ክህሎት ያላቸው ግለሰቦች በአብዛኛው ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሱ ሰዎች መገለጫ ናቸው፡፡ እነዚህ ተዘዋዋሪዎች ብዙ ጊዜ መደበኛ ባልሆነው የከተማ የስራ እንቅስቃሴ ስለሚሳተፉ ያለምንም ተቋማዊ ዕውቅና በከተሞች ውስጥ ባለው የስራ አጥነት፣ በስራ የመሰማራት ውድድርና በደሀ ሠራተኞች  ችግር ላይ ጫና ይጨምራሉ፡፡

በእርግጥ የሀገር ውስጥ ፍልሰት በፖሊሲዎችና በተቋማዊ አገልግሎቶች ከተደገፈ በተለያዩ አካባቢዎችዎችና የሥራ ዘርፎች መካከል ውጤታማ የሰው ኃይል ሀብት ክፍፍል እንዲኖር በማስቻል፣ የመዋቅር ሽግግር በማምጣትና በኢኮኖሚው ውስጥ ውህደትን በማሻሻል ለዕድገትና ለድህነት ቅነሳ አስተዎጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ከገጠር ወደ ከተማ ለሚደረግ ፍልሰት የሚገፋፉ ምክንያቶች የሚያሳዳድሩት ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደመሆኑ የትንንሽ ከተሞችን ዕድገት ለማሻሻል ለከተማ ስራ ፈጠራ የተሰጠውን ትኩረት (በአምስት ዓመቱ የሀገሪቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደተጠቀሰው) በመገንዘብ በኢትዮጵያ የሚታየውን የገጠር-ከተማ ፍልሰት ጉዳይ የሚያስተናግድ ጠንካራ ስትራቴጂ ሊነደፍ ይገባል፡፡

#### 2.3.5.4.1 የገጠር-ከተማ ፍልሰትን የመግታት ስትራቴጂ

ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ለመግታት የሚያገለግሉ ስትራቴጂዎች ለፍልሰቱ የሚገፋፉና የሚስቡ ምክንያቶችን በመግታት ላይ በሰፊው ያለሙ መሆን አለባቸው፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

- የግብርና ዳይቨርስፍኬሽንና የገጠር ሽግግርን ማጠናከር፡- የገጠር ልማትን ማሻሻል ስደተኞችን ወደ ከተሞች እንዲፈልሱ የሚገፏፏቸውን ምክንያቶች ከመቀነስ አንጻር ጥሩ ሚና ይጫወታል፡፡ የመሬት ጫና (የመሬት መራቆት)፣አመቺ ያልሆነ የአግሮ ኢኮሎጂ ፣ዝቅተኛ ምርታማነት፣ ደካማ መሰረተ ልማት እና እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ ብድርና ቁጠባ የመሳሰሉ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ዝቅተኛ መሆን ወይም አለመኖር የገጠር ኑሮን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ብሎም ወጣት ገበሬዎችን ስራ ፍለጋ ወደ ከተማ እንዲፈልሱ ያስገድዳቸዋል፡፡ ስለዚህ በገጠር በመካሄድ ላይ ያሉትን ከግብርና ውጪ የሚደረጉ ተግባራትንና የአገሪቱን የአነስተኛ ይዞታ የዳይቨረስፍኬሽን እርሻ እንቅስቃሴዎችን በይበልጥ ማጠናከርና ማሻሻል የገጠር-ከተማ ፍልሰትን ለመቀነስ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

- የገጠር የስነ ሕዝብ አወቃቀር (Demographic) ለውጥ (ሽግግር)፡- ምንም እንኳ የወሊድ ምጣኔ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ከፍተኛ ቢሆንም በአንፃራዊ ሲታይ የገጠሩ ከከተማው ከፍ ያለ ነው፡፡ የሀገሪቱ ከፍተኛ የወሊድና የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ባለበት አቅጣጫ መቀጠል አሁን ላለው የገጠር የህዝብ ክምችት ችግርንና ለገጠር-ከተማ ፍልሰት መባባስ ዋና ምክንያት ነው ተብሎ የሚታመነውን የመሬት ጫናን (የመሬት መራቆት) በማባባስ የራሱን ተጽእኖ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን በማሻሻልና የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ የገጠር የወሊድ መጠንን መቀነስና የገጠር የስነ ሕዝብ አወቃቀር (Demographic) ሽግግርን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

- ከግብርና ውጪ የሚደረግ የስራ ስምሪትንና የገቢ ማስገኛ ምንጭን ማሻሻል እና የገጠር-ከተማ ትስስርን ማጠናከር፡- በኢትዮጵያ የስራና የገቢ ምንጭ ዕድሎችን ለማግኘት የሚደረግ ፍለጋ የገጠር-ከተማ ፍልሰት እንዲጨምር ዋነኛ የሚገፋፉ ምክንያት ነው፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት፣ ከግብርና ተግባራት ጋር በማቆራኘትና ከግብርና ውጪ የሚደረግ የስራ ስምሪትን በማጠናከር ችግሩን በከፊል ለማቃለል ይቻላል፡፡ አጠቃላይ የግብርናና የገጠር ልማት፣ ትናንሽ የከተማ ማዕከላትን እንደ ዕድገት ምሰሶ ማልማትና የገጠር-ከተማ ቁርኝትን ማጠናከር ከግብርና ውጪ ለሚደረግ የስራ ስምሪትና ለገቢ ማስገኛ ዕድሎች መጠናከር አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

- ለስደተኞች የመረጃ አገልግሎትና የተቋም ጥበቃ መስጠት፡- አብዛኛውን ጊዜ የገጠር-ከተማ ፍልሰት ድንገተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ስራ ዕድሎች፣ ቅጥር ሁኔታ እና ጥቅማ ጥቅምና ደሞዝን (ክፍያን) በተመለከተ በመረጃና በተቋም አገልግሎት ለመደገፍ የተመቸ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ለስደተኞች በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በኩል ተቋማዊ አገልግሎትና ሌሎች አገልግሎቶች መስጠት፤ አመቺ ስራዎችን ለስደተኞች ከመፍጠር አንፃር አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

2.3.5.5 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የስራ ቦታ

ምንም እንኳን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት በኢትዮጵያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየቀነሰ ቢመጣም በአመዛኙ በሠራተኛ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለውን ህብረተሰብ ስለሚያጠቃ አሁንም ለኢኮኖሚ ልማትና ድህነት ቅነሳ ጥረቶች ስጋት ነው፡፡ የስራ ዕድልንና ምርታማነትን ከማሳጣት አንጻር በተለይም በሴቶች ላይ በሽታው የሚያስከትለው ጉዳት የከፋ ነው፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በቤተሰብ ውስጥ በበሽታው የተጠቁትንና ህመምተኞችን በመንከባከብ ትልቁን ድርሻ ስለሚወስዱ ፡፡ ይህም ስራ የመፈለግ፣ ስራ ላይ የመቆየት፣ የመማርና ችሎታቸውን የማሻሻል አቅማቸውን በመፈታተን ተጨማሪ ጫና ይፈጥርባቸዋል፡፡

ስለዚህም መንግስት ከልማት አጋሮችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት (anti-retroviral therapy (ART) and prophylactic therapy) መስጠትን መቀጠል ይኖርበታል፡፡ የተመጣጠነ የአመጋገብ ዘዴ መጠቀም እንዲሁ ከበሽታው መቆጣጠሪያ ስትራቴጂዎች ውስጥ እንደ ቁልፍ ጉዳይ መካተት አለበት፡፡

2.3.5.5.1 ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስና የስራ ቦታ ስትራቴጂዎች

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን የስራ ስምሪት ዕድልና ውጤቶችን የማሻሻል ስትራቴጂ የስራ ባልደረቦቻቸውንና በይበልጥም ህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስጨበጥ ላይና እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ. ተጠቂዎችን የመስራትና የመኖር መብትን በማሳወቅ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከስራ ዕድል ጋር ከማቀራኘትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ በተጨማሪ በኤች.አይ.ቪ. ተጠቂዎች ላይ ማግለልና መድሎ እንዳይኖር መከላከል የበሽታውን ስርጭት ለመቀነስ ይረዳል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን የበሽታው ተጠቂዎች ምርታማነታቸውና የችሎታ ደረጃቸው እንዳይቀንስ እንዲጠብቁት ማበረታታት ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ ይህም በስራ ቦታዎች ከለላ በመስጠት፣ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግና በተሻሻለ የአመጋገብ ዘዴ ሊደገፍ ይገባዋል፡፡

2.3.5.6 ሥርዓተ-ጾታን በስራ ፈጠራ ውስጥ ማካተት

በኢትዮጵያ ሴቶች የትምህርትና የሥራ ተሳትፎ ላይ የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎች ይታያሉ፡፡ ነገር ግን በመደበኛው ዘርፍ እና በፕሮፌሽናል (white collar) ስራዎች ላይ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር የሚነፃፀር አይደለም፡፡ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶቹ በ13 በመቶ (75% ለ 88% በ2005 እ.ኤ.አ) ያነሰ ሲሆን፣ ስራ አጥነትና ከፊል ሥራ አጥነት ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ጎልቶ ይታያል፡፡

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰውም አብዛኛዎቹ ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ተከማችተው እንደሚገኙ እውነት ነው፡፡ በመሆኑም የድህነት ቅነሳ ማዕከል የሚያደርገው በሥራ ገበያ ውስጥ ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ችግሮች መቅረፍ ላይ ነው፡፡ የሴቶችን የሠራተኛ ኃይልና የመደበኛው ዘርፍ ተሳትፎ በማሻሻል ስኬታማ የሆነ ውጤት ለማስገኘት

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

መንግስት ለሴቶች ሙያ ማሻሻያ፣ ለምርታማ ሀብት አቅርቦት ተደራሽነትና ለተቋማዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ትኩረት መሰጠት አለበት፡፡

2.3.5.6.1 ስርዓተ-ጾታን በስራ ፈጠራ ውስጥ የማካተት ስትራቴጂዎች

ሴቶችን ትኩረት ያደረጉና ስርዓተ-ጾታን ያካተቱ የስራ ፈጠራ ስትራቴጂዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

- ለሥራ ፈጠራ ከሚዘጋጁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተወሰነው ሴቶችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ለሴቶች ቅድሚያ የመስጠት አሰራርን (affirmative actions) ተግባራዊ ማድረግ፣

- ሴቶች የሙያና የንግድ ስራ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ለሀብት አቅርቦት ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ተቋማት ሴቶችን ዒላማ አድርገው እንዲሰሩ ማበረታታትና ጥረቶችን ማቀናጀት፣

- የሴቶችን አሰልቺ የሆነ የቤት ውስጥ ሥራና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጫና ለመቀነስ ለሴቶች ልማት ተስማሚ የሆኑ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ማበረታታት፣ እንዲሁም ምርታማነታቸውንና ገቢያቸውን በማሻሻል ገቢ የማግኘት አቅማቸውን መጨመር፣

- ለሠራተኛ እናቶች የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

2.3.5.7 የወጣቶችን የስራ ስምሪት ማስፋፋት

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም የህዝብ አወቃቀር እስከ መካከለኛ የጊዜ ዘመን እንደሚቀጥል ይገመታል፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቶች በከተማ ስራ አጥነት፣ በዓለም አቀፍና በሀገር ውስጥ በተለይም ከገጠር-ከተማ ፍልሰት ውስጥ ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

የመደበኛ የሥራ ዕድል ውስንነት፣ ፈጣን የህዝብ ዕድገት፣ የገጠር-ከተማ ፍልሰት፣ የትምህርት ካሪኩለምና የጥራት ደረጃ፣ የሥራ ገበያ ፍላጎትን በሚፈለገው ደረጃ ለማሟላት አለመቻሉ ለወጣቶች ስራ አጥነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በአፍሪካ ያለው ሰፊ የሆነ የወጣቶች ስራ አጥነት #የመንገድ ላይ ወጣቶችን; ለማፍራት ምክንያት ሆኗል፡፡ በኢትዮጵያም ያለው ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ችግሩ አገርን ለቆ ጥሩ የስራ ዕድልና ክፍያ ወዳለበት አካባቢ መሄድን እንዲሁ አበረታቷል፡፡ በስራ ዕድል መጥበብ ምክንያት ወጣት ሴቶች ለመኖር ሲሉ የሚሰማሩበት ተግባር የሴተኛ አዳሪነትን አባብሷል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

መንግስት የትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ጥራትን ለማሻሻል፣ በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑት የስራ ዘርፎች ጥራት ያላቸው ስራዎች እንዲፈጠሩ ለመደገፍ፣ የወጣቶችን ኢንተርፕሪነርሽፕ ለማበረታታትና ለማብቃት፣ ወጣቶች ወደ ስራ የሚገቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የወጣቶችን እንቅስቃሴና የሥራ ዕድል የሚያራምዱ የስራ ስምሪት ማስፋፊያ ስትራቴጂዎችን ለመቀየስ የሚያስችሉ ዕርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

### 2.3.5.7.1 የወጣቶች የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ስትራቴጂዎች

ወጣቶችን ትኩረት ያደረጉ የስራ ስምሪት ስትራቴጂዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የመደበኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ጥራትን ማሻሻል፣
- በስራ ላይ ያለው የወጣቶች ፓኬጅ በተደራጀ ሁኔታ በስፋት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- በመደበኛና መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ ጥራት ያላቸው ስራዎች እንዲፈጠሩ መደገፍ፣
- የወጣቶችን ኢንተርፕሩነርሽፕና ውሳኔ ሰጭነት ማበረታታት፣
- ወጣቶች ወደ ስራ እንዲገቡ መርዳትና የወጣቶችን እንቅስቃሴና የስራ ስምሪት ሊያሻሽሉ የሚችሉና ወጣቱን በሰፊው ስራ ላይ ሊያሰማሩ የሚችሉ ተጨማሪ አሰራሮችን ማመቻቸት፡፡

### 2.3.5.8 ለአካል ጉዳተኞች የስራ ዕድሎችን ማመቻቸት

አሁን በሚገኙ ጥናቶች መሠረት በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ቁጥር በ1999 ዓ.ም በተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት 805,535 እንደነበር ይገመታል፡፡ ምንም እንኳ አካል ጉዳተኞች አንዳንድ ስራዎችን ለማከናወን ቢቸገሩም ሙሉ ለሙሉ ግን ምርታማ ያልሆኑና ጥገኞች አይደሉም፡፡ መደበኛና መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ አካል ጉዳተኞች መገለል እንደሚገጥማቸው የሚያመላክቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ባላቸው ልዩ የሰውነት አቋም ምክንያት አካል ጉዳተኞች በዘመናዊው የግል ዘርፍ ለመቀጠር ለየት ያሉ ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ እነዚህ ችግሮች የአካል ጉዳተኞችን የሥራ ገበያ ተሳትፎ ብሎም ገቢ የማግኛ ዕድሎቻቸውን ይገድባሉ፡፡

ስለዚህ ስራ አጥነት በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የተስፋፋ ነው፡፡ ከድህነት የመውጣት ዕድላቸውም በነዚህ አስቸጋሪ ምክንያቶች አዳጋች ሆኖ ቆይቷል፡፡ የአካል ጉዳተኞች በሥራ ገበያ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማበረታታት መንግስት ተቋማዊ ጥበቃና እኩል የመቀጠር ዕድሎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ የትምህርትና የስራ ስምሪት ተደራሽነትም መንግስት የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማበረታታት ከሚወስዳቸው ዋና ዋና እርምጃዎች ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

### 2.3.5.8.1 ለአካል ጉዳተኞች የስራ ዕድሎችን የማጠናከር ስትራቴጂዎች

አካል ጉዳተኞች ያሉበት ሁኔታ በመደበኛ ዘርፍ ተወዳድሮ ስራ ለመቀጠር የሚያስፈልጉትን ሙያዊ ክህሎቶች ከማግኘት፣ ስለ ስራ ዕድል መረጃ ከማግኘትና ስራ ለመቀጠር ተወዳድሮ ከማሸነፍ ሊያግዳቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት ጥበቃ ላይ ትኩረት ያደረጉ ስትራቴጂዎች የሙያ ክህሎትን ከማዳበር እስከ ስራ ስምሪት ድጋፍ ድረስ ያሉ ጉዳዮችን ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም ስትራቴጂዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡፡

- ለአካል ጉዳተኞች የተለየ ፍላጎት የሚስማሙ የስልጠናና ሌሎች የክህሎት ማዳበሪያ አገልግሎቶችን ማሻሻልና ማስፋፋት፣
- አንዳንድ ጊዜ በመደበኛው ዘርፍ ዘልቆ ለመግባት ስለሚያስቸግራቸው አካል ጉዳተኞች የራሳቸውን ስራ እንዲጀምሩ ድጋፍ መስጠት፣
- በተለያዩ ፎረሞች ላይ በአግባቡ እንዲወከሉና ድምጻቸው እንዲደመጥ የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን መደገፍና ማበረታታት፣
- ለአካል ጉዳተኞች በሚስማማ መልኩ ልዩና ፈጣን የሥራ ገበያ አገልግሎት መስጠት፣
- የተሻለ የብድር አቅርቦት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- የመደበኛው የግል ዘርፍ ማህበረሰብ የአካል ጉዳተኞችን ሁኔታ እንዲረዳና ለፍላጎታቸውም ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ፡፡

### 2.3.5.9 የሕጻናት ጉልበት ስራን መከላከል

በኢትዮጵያ የሕጻናት የጉልበት ስራን የሚከለክሉ ህጎች ተፈፃሚነት ትልቅ ፈተና እንደሆነ ነው፡፡ በድህነት፣ በቂ የትምህርት ዕድል ባለማግኘትና በግንዛቤ ዕጥረት ምክንያት ዕድሜያቸው ገና 5 ዓመት የሆኑ ሕጻናት በቤተሰብ እርሻዎች፣ መደበኛ ባልሆኑ ስራዎችና ብሎም አንዳንዴ በመደበኛው ዘርፍ በዝቅተኛ ክፍያ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡

ለሕጻናት ጥበቃ ለማድረግ ጠንካራ ህግ ከማውጣት በተጨማሪ መንግስት ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት አቅርቦትን ማሳደግ፣ ትምህርትን ግዴታ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት የምግብ አገልግሎት መስጠት (School meals)፣ የጎልማሶችን ደሞዝ መጨመርና የግብርናን ምርታማነትና ገቢ ማሻሻል የመሳሳሉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡ ትምህርትን ግዴታ ማድረግ ከሕጻናት የጉልበት ስራ ጋር የተገናኙ ችግሮችን በቀላሉ ለመፍታት ስለሚያስችል በጣም ውጤታማ ዕርምጃ ነው፡፡

Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

### 2.3.5.9.1 ሕጻናትን ከጉልበት ብዝበዛ የመከላከል ስትራቴጂ

የቤተሰብ ድህነት፣ የቤተሰብ አለመስማማትና ወላጆችን በተለያዩ ምክንያቶች ማጣት ለሕጻናት የጉልበት ስራ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው ተብሎ ይታመናል። ምንም እንኳን ከባድና ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም የቤተሰብን ድህነት መቀነስ የህጻናትን በጉልበት ስራ መሰማራት በመቀነስና ህጻናትን ከጉልበት ብዝበዛ በመጠበቅ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

በዚህ ረገድ በአገሪቱ የሚታየው የድህነት ቅነሳ አቅጣጫ የሕጻናትን በጉልበት ስራ መሰማራት ለመቀነስ ጥሩ አዎንታዊ አስተዎጽኦ ያደርጋል። ለእማ ወራዎችና ብዙ ልጆች ላሏቸው ድሃ ቤተሰቦች የገቢ ምንጭ ዕድሎችን ከማስገኘት አንጻር የሚደረግ ልዩ ድጋፍ በነዚህ ቤተሰቦች ላይ የሚደርሰውን የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ለመቀነስ አስተዎጽኦ ያበረክታል። ተገቢ በሆኑ የማህበራዊ ፖሊሲዎች ለዚህ የሚገፋፉ ምክንያቶችን መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ፤ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የሕግ ከለላዎችን በማድረግና በሕጻናት የሚመረቱ ምርቶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በመቃወምና በማገድ እንዲሁም መሰል ዕርምጃዎችን በመውሰድ ሕጻናትን ለጉልበት ሥራ የሚስቡ ምክንያቶችን መግታት ያስፈልጋል።

ይሁንና ሕጻናት በቤተሰብ ውስጥና ከቤተሰብ ውጭ ለመኖር ሲሉ ተገደው ሊሰሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ በሕጻናት የሚመረቱ ምርቶችን ማግለልና ማገድ ሕጻናቱን ከመጥቀም ይልቅ ጉዳት ሊያስከትልባቸው ይችላል። ስለዚህም መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያስፈልጋቸውን ገቢ እንዲያገኙ በተመቻቸ ሁኔታ እንዲሰሩ በመፍቀድና የወደፊት ሕይወታቸውን የሚያግዝ ትምህርት እንዲያገኙና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ በመርዳት ሚዛናዊ የሆነ እርምጃ መውሰድ አግባብና ትክክለኛ ይሆናል።

### 2.3.5.10 የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ

የአየር ንብረት  ለውጥና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ከግብርና የሚገኝ የገቢ መጠንና ቀጣይነት ላይ ብሎም የግብርና የስራ ስምሪት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ ግብርና የኢኮኖሚው ዋና ምሰሶ እንዲሆን በመርዳት ረገድ መሬት እጅግ ወሳኝ ሀብት ነው። ስለሆነም በሕዝብ ብዛት በሚመጣ ጫና ምክንያት በተለይም በመካከለኛው ደጋማ  አካባቢዎች ያለው የመሬት መራቆትና ከሚገባው በላይ የመጠቀም ሁኔታ የግብርና ምርታማነት ዕድገትን ከመገደብ ባሻገር በግብርና ላይ በተሰማራው ሕዝብ ገቢ የማመንጨት አቅምና የምግብ ዋስትና ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።

በተመሳሳይም የአየር ንብረት ለውጥ ጎርፍ፣ ድርቅና አውሎ ንፋስ በመሳሰሉ የተለያዩ መንገዶች በመከሰት በሰው ልጆች ላይ ትልቅ ስጋትና ከባድ አደጋ ይጥላል። እነዚህ የአካባቢ ችግሮች የግብርናን ምርታማነት ከመቀነስና ኑሮን ለተደጋጋሚ የአየር ንብረት አደጋዎች ከማጋለጥ በተጨማሪ በግብርናና በግብርና ጥገኞች  ላይ ቀጥተኛና ጠንካራ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

በገጠር አካባቢዎች በከፍተኛ የሕዝብ ክምችት የሚከሰት የመሬት መራቆትና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መታየት የጀመሩት ጥሩ ያልሆኑ የአየር ንብረት ለውጦች (በተለይም ድርቅ) ለገጠር-ከተማ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ፍልሰት መጨመርና ለሰዎች የመፈናቀል ሂደት አስተዎጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ምንም እንኳን የገጠር-ከተማ ፍልሰት በረጅም የጊዜ ርቀት በድህነት ላይ ያለው ተጽእና አዎንታዊና ተፈላጊ ቢሆንም እንደነዚህ ዓይነት አስገዳጅ መፈናቀሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች በጣም ከፍተኛ በመሆናቸው የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ስራዎች ላይ ትኩረት መስጠት ግድ ይላል፡፡

### 2.3.5.10.1 የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ስትራቴጂዎች

ኢትዮጵያ የብሔራዊ አካባቢ ጥበቃ ፖሊሲና ስትራቴጂ ስራ ላይ አውላለች፡፡ በአጠቃላይ ውሃና መሬትን ጨምሮ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከመቆጣጠርና ለአለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ጥረት አስተዋጽኦ ከማበርከት አንፃር እነዚህን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የገጠር ኑሮ (Rural livelihood) ጥበቃን ዓላማ ያደረጉ ፕሮግራሞችና እርምጃዎች የአየር ንብረት ለውጥና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፣ በገጠር ስራ ስምሪትና የከተማ ስራ አጥነት ላይ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመከላከል የራሳቸውን ድርሻ ያበረክታሉ[7]፡፡

በገጠር አካባቢዎች የአየር ንብረት ኢንሹራንስ ስርዓትን ጨምሮ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ጉዳት የመቋቋሚያ ዘዴዎች መቀየስ የአየር ንብረት ለውጥና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቀነስ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም በአሉታዊ የአየር ንብረት ክስተቶች ወቅት የማህበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን እንቅስቃሴ ይዞ መቀጠል የገጠር ህዝቦች ጥሪታቸውን እንዳያጡ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡

---

[7] በኑሮ መጋለጥ ሳቢያ የሚመጣ የገጠር ህብረተሰብ መፈናቀል ብዙ ጊዜ ለከተማ ስራአጥነት ችግር አስተዋጽኦ የሚያደርገውን የገጠር-ከተማ ፍልሰትን ያስከትላል፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

## ክፍል ሶስት

## የፖሊሲ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ ተቋማዊ ማዕቀፍ

### 3.1 የፖሊሲ ትግበራ ተቋማዊ ማዕቀፍ

ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ እንዲተገበር በሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትና መንግስታዊ ባልሆኑ ባለድርሻዎች መካከል የተቀናጀ እርምጃ መውሰድን ይጠይቃል። የስራ ስምሪት ጉዳይ መሠረተ ሰፊና ባለብዙ ፈርጅ እንደመሆኑ፤ የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ በፌደራልና በክልል ደረጃ በሚገኙ በተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና የመንግስት አካላት እና ኤጀንሲዎች የሚተገበር ነው። በተጨማሪ በሁሉም የአስተዳደር ደረጃ ላይ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የተለያዩ የድጋፍ አገልግሎቶች በመስጠት በብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ ሂደት ላይ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ።

ከላይ በክፍል ሁለት የተጠቀሱት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ተቋማዊ ቅንጅትንና ክትትልን ይጠይቃል። እንዲህ ላለ የተቀናጀ ትግበራና የስራ ስምሪት ውጤት ክትትል፤ ተቋማዊ የሆነ አሰራር ተግባራዊ ሊሆን ያስፈልጋል። ይህም ከታች በሰፊው እንደተዘረዘረው የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት ምስረታን ይጠይቃል።

### 3.1.1 ብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክርቤት

የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የስራ ስምሪት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አጠቃላይ ትግበራን ለመምራትና ለማስተባበር ብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት በአገር-አቀፍ ደረጃ መቋቋም ይኖርበታል። የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት ዋና ተግባራት፡- የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ በተለያዩ የሀገሪቱ የማክሮ ኢኮኖሚና የሴክተር ፖሊሲዎችና የልማት ስትራቴጂዎች ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥና ሰፊና ባለብዙ ዘርፍ የሆኑ የትግበራ፣ የቅንጅትና ክትትል ስልቶች መቀየስ ናቸው። ምክር ቤቱ የስራ ስምሪት እና ድህነት ተኮር የዕድገት ፖሊሲ ጉዳዮችን በተመለከተ ለመንግስት እንደ አማካሪ አካል ሆኖ የሚያገለግል መሆን አለበት። የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክርቤት የሚከተሉትን የፌደራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚያቅፍና በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የሚመራ ይሆናል፡-

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣

የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር፣

የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር፣

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የትምህርት ሚኒስቴር፣

የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር፣

የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣

የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፣

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣

የፍትህ ሚኒስቴር፣

የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፣

የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣

የክልል መንግስታትና ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮች፡

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች፣
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌደሬሽን፣

የኢትዮጵያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን፣

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣

የኢትዮጵያ የንግድ ምክር ቤት፣

በተጨማሪም የአርሶ አደሮችና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች/መደበኛ ያልሆነ የስራ ዘርፍ ተወካዮችን ማካተት አስፈላጊ ነው፡፡

የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት አበይት ተግባራት የሚከተሉትን በዋነኝነት ያካትታሉ፡፡

ሀ/ የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ በሀገራዊ የልማት ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ (መከታተል)፣

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ለ/ ደረጃቸውን የጠበቁ የትግበራና ክትትል ስልቶችን በማበጀት ተለይተው የተቀመጡትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አተገባበር መከታተል፣

ሐ/ በመንግስት ውስጥና ከመንግስት ውጪ ባሉ የተለያዩ ባለድርሻዎች መካከል ተቀናጅቶ የመስራት ሂደትን መፍጠር፣

መ/ እየተሰራበት ያለውን የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነቱ ሲታመንበት ማሻሻል፡፡ ይህም በስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን ቅድም ተከተል ማስያዝ (Prioritize)፣ መጨመርና/ወይም መቀነስን ሊያካትት ይችላል፡፡

የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት በየጊዜው ለሚያከናውነው ተግባር በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ በተደራጀ ጽ/ቤት አማካይነት ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ ጽ/ቤቱ ውጤታማ ስራ እንዲሰራ በቂ በጀት ይመደብለታል፡፡ ሙሉ ጊዜያቸውን ለጽ/ቤቱ ሥራ የሚያውሉ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችም ይመደቡለታል፡፡

### 3.2 የፖሊሲ ውጤቶች ክትትልና ግምገማ

በብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት አማካኝነት ለፖሊሲና ዕቅድ አውጪዎች ግብረ-መልስ ለመስጠት፤ የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ ሂደትን በየጊዜው መከታተልና መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ያለ የግብረ-መልስ መረጃ ለስትራቴጂዎቹ መተግበር ኃላፊነት ለተሰጣቸውና ለሚመለከታቸው ተቋማት ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ ስትራቴጂዎቹም እንደተፈለገው በማይተገበሩበት ጊዜ ችግሮቹን ለይቶ ለማውጣት፣ ትክክለኛ ዘዴ ለመቀየስና የትግበራ ክፍተቶችን ለመሙላት ይረዳል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ለብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ ኃላፊነት በተሰጣቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች የክትትል ማዕቀፍ ስርዓት ሊበጅ ይገባዋል፡፡

የክትትልና ግምገማው ሥርዓት ከአገራዊ የልማት ዕቅድ አፈፃፀም የክትትልና ግምገማ ዘዴ (PASDEP) ጋር የተገናዘበና ወጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ የተለያዩ የዘርፍና የመድብለ ዘርፍ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶችም ለትግበራው ፈጻሚ አካላት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች ይሆናሉ፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የአምስት ዓመቱ ዕቅድ (PASDEP) የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን የሚያስተባብር ማዕከላዊ አካል ነው፡፡

በዚህ ፖሊሲ አፈጻጸም የክትትል ሥርዓት ቁልፍ የመረጃ ፍላጎቶችን (ማለትም የተለየ /specific/ የፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራን አስመልክቶ ምን ዓይነት መረጃዎች እንደሚያስፈልጉ) መለየት፣ የሚፈለገውን መረጃ ለማመንጨት መረጃውን በመሰብሰብና በመተንተን የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት አካል፣ የመረጃ መሰብሰቢያና ሪፖርት ማድረጊያ የጊዜ ወሰን፣ ወ.ዘ.ተ. በግልጽ ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ምንም እንኳ የየሴክተሩ የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች የተለያዩ ቢሆኑም ከተለያዩ የዘርፍ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ጋር

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በተገቢው በመቀናጀት (በመናበብ) የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የራሱን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት መትጋት ይኖርበታል፡፡

በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚቋቋመው የም/ቤቱ ጽሕፈት ቤት ሁሉንም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርንና የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን ያካተተ የሶስትዮሽ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አገራዊውን የልማት ዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የሚያስተባብር ማዕከላዊ አካል እንደመሆኑ መጠን በዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶቹ አማካኝነት የሁሉንም ዘርፍ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በየወቅቱ በሚካሄዱ የሙሉ ቆጠራና የመስክ ጥናቶች አማካይነት በሚሰበሰቡ መረጃዎችና አግባብነት ያላቸው የፌዴራልና የክልል አካላት በሚያመነጩት አስተዳደራዊ የሥራ ስምሪት መረጃዎች ሊታገዝ ይችላል፡፡ በፌደራል ደረጃ ከዘርፍ አስፈጻሚ አካላት የሚገኘውን መረጃ ከክልል ተጓዳኝ አካላት የሚመነጩትን መረጃዎች ጨምሮ በመሰብሰብና በማቀናጀት አገራዊ ይዘትና ወካይነት እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ዓላማ ምርታማ የስራ ስምሪትንና ድህነት ቅነሳን አስመልክቶ በሁሉም ደረጃ አዎንታዊ ውጤት ማምጣት ነው፡፡ ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ስራ አጥነትን፣ ከፊል ስራ አጥነትንና የአገሪቱን የድህነት ሁኔታ ከመቀነስ አንፃር ያስገኘው ፋይዳ በተመረጡ የውጤት አመልካቾች መዳሰስ ይኖርበታል፡፡

ደረጃውን የጠበቀ የፋይዳ ግምገማ ለማካሄድ ፖሊሲው ከመተግበሩ በፊት የነበረው ሁኔታን በፖሊሲው አፈጻጸም ወቅት ከተገኙ ውጤቶች ጋር ለማነፃፀር እንደመነሻ (Baseline) ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ መረጃዎችን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

ግምገማው ምርታማ የስራ ስምሪትና የድህነት ቅነሳ ውጤቶችን ለማመልከት ባላቸው ጠቀሜታ የተመረጡ ቁልፍ አመልካቾችን (መለኪያዎች) መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

ፖሊሲው ያስገኛቸውን ውጤቶች ለመገምገም የሚከተሉት አመልካቾች ተለይተዋል፡፡

ሀ) የሰው ኃይል ዕድገትና ተሳትፎ ምጣኔዎች በፆታ፣ በክልል ከተሞችና በከተማ መስተዳድሮች፣ በከተማና በገጠር ወ.ዘ.ተ.፣

ለ) የስራ አጥነት ደረጃና ምጣኔ በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በከተማና በገጠር ወ.ዘ.ተ.፣

ሐ) በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎቶች ዘርፍ የመነጨ ተጨማሪ የሥራ መስኮችን የስራ ስምሪት መጣኔ (ከግብርናና ከግብርና ውጪ በሚከናወኑ ተግባራት የተገኘ የስራ ስምሪትና ገቢ ላይ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ መረጃ)፣

መ) የከፊል ሥራ አጥነት ምጣኔዎችና መደበኛ ያልሆነው የስራ ዘርፍ መጠን (መደበኛ ያልሆነው የስራ ዘርፍ አሠሪዎችና ተቀጣሪዎች ቁጥር)፣

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ሠ) የወጣቶች ስራ አጥነትና ስራ ስምሪት ምጣኔ፣

ረ) በሥራ ገበያ ውስጥ የሚገኙ የጾታ ልዩነቶች ምጣኔ (ተቀጣሪ ሴቶችና ወንዶች በዘርፍ) ከሚያገኙት ገቢ መጠን ጋር፣

ሰ) የስደተኛ ሠራተኞች ቁጥር፣መነሻ (ከየትኛው የሀገሪቱ ክፍል)፣ የትምህርት ደረጃና የሚጓዙበት አገር፣

ሸ) የስራ ስምሪት መጠን በመንግሥት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ በግል ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች/ለጋሾች፣ በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና በግል ስራ፣

ቀ) የክፍያ ምጣኔና የወር ደሞዝ (በመንግሥት ሠራተኞች፣ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ በግል ካምፓኒዎች፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች/ለጋሾች፣ በቤተሰብ በሚተዳደር ሥራና በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች)፣

በ) የምርታማነት ምጣኔዎች (የተገኘው የነፍስ ወከፍ ተጨማሪ እሴትና በነፍስ ወከፍ የተገኘ የምርት ውጤት ወ.ዘ.ተ.) በሁሉም ኢንዱስትሪዎች፣

ተ) የቢሮ ሠራተኞችና (white collars) የሌሎች ሠራተኞች የድህነት ምጣኔ (ከድህነት ወለል በታች፣ የድህነት ጥልቀትና የድህነት አስከፊነት)፣

ቸ) የአካል ጉዳተኞች የተሳትፎ ምጣኔዎችና የስራ ስምሪት/ስራ አጥነት ሁኔታ ወ.ዘ.ተ፣

ነ) የየዘርፉ የስራ መደብ አወቃቀር (Information on occupational structure)፣

ኘ) በፍጥነት በማደግ ላይ ባሉና የሰው ኃይልን በብዛት የሚጠቀሙ እንደ ጨርቃ ጨርቅ፣ የምግብና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል የመፍጠር አዝማሚያ አመልካቾች፣

አ) የሕጻናት የጉልበት ስራ ምጣኔ በየዘርፎች (child labour)

ከላይ የተጠቀሱት አመልካቾች ለፓሊሲው አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ተግባር ያላቸውን አዋጭነት በተመለከተ ወቅታዊ ግምገማ ለማድረግ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲና ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በየጊዜው ጥናቶችን ለማከናወን በቅርበት መስራት አለበት፡፡

ጽ/ቤቱ እነዚህን አመልካቾች በየጊዜው ለማመንጨት በሚያገለግሉ ጥናቶች ላይ (በየዓመት ወይም በየአምስት ዓመት) በመመርኮዝ የሚጠበቁ አመልካቾች መገኘታቸውን አስመልክቶ ክትትልና ግምገማ የማድረግ ተግባርና ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ጽ/ቤቱ የሰው ኃይል፣ በጀትና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት ያስፈልጋል፡፡ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚገኘው ጽ/ቤት ከማዕከላዊ ስታትስቲክስና ሌሎች ከሥራ ስምሪት ጋር የሚዛመዱ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

አስተዳደራዊ መረጃዎች ከሚያመነጩ አግባብ ያላቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በቅርበት ተቀናጅቶ መስራት ይኖርበታል። ጽ/ቤቱ በመጨረሻም በዓመታዊ ሪፖርቶቹ አማካይነት ከሥራ ስምሪት ጋር የሚዛመዱ መረጃዎችን ማጠናቀር፣ ማቀናበርና በሪፓርት መልክ ማሰራጨት ይኖርበታል። በማንኛውም ጊዜ በየወቅቱ ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚቀርቡ መረጃዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አመልካቾች ለማመንጨት የሚረዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል። ይህም የጽ/ቤቱ ዋነኛ ተግባር ነው።

### 3.3 የፖሊሲ ትግበራ ስልት

የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውይይት ተደርጎበትና በመጨረሻም ፀድቆ ስራ ላይ ሲውል በሚከተሉት ስልቶች መታገዝ ይኖርበታል።

- የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት ማቋቋም፡- የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራን የማቀናጀትና የማስተባበር ሚና በብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት አመራር ሰጭነት የሚከናወን ነው። ስለዚህ ምክር ቤቱን ማቋቋምና ጽ/ቤቱን በሰው ኃይል ማደራጀት ወደ ፖሊሲው ትግበራ ከመገባቱ በፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊተገበር የሚገባ የመሠረት ድንጋይ ነው።

- በሂደት በጣም አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን፣ በስራ ስምሪት ውጤቶችና ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ላይ የጋራ አመለካከት መያዝ አስፈላጊ ነው። ይህም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ ላይ ከሚሳተፉና ከሚወያዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በሚዘጋጅ አውደጥናት አማካይነት ሊታገዝ ይችላል። እንደአስፈላጊነቱም አንዳንድ ለውጦች ሊደረጉ ይችላሉ። በዚህ ደረጃ እያንዳንዱ አስፈጻሚ ባለድርሻ አካል መሰረታዊ የስራ ስምሪት ጉዳዮችን በፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የልማት ዕቅድ በማውጣት ሂደት ላይ ከግምት ውስጥ ማስገባቱን (ማካተቱን) ለማረጋገጥ የተዘረዘሩ ጉዳዮች ለተለያዩ ሴክተሮችና የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አውጭ ተቋማት (በተከታታይና በቀጣይነት) ሊቀርብላቸው ይገባል።

- ፖሊሲና ስትራቴጂ ከመተግበር፣ መረጃ ከመሰብሰብ፣ ከመተንተን፣ ከመለዋወጥና ከማሰራጨት አንፃር የሚጫወቱትን ሚናና ተጠያቂነት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲና በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ባሉ ቁልፍ አካላት መካከል የአሰራር ቅንጅት ሊፈጠር ይገባል። በተመሳሳይም ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂን በመተግበር ሂደት ላይ የሚመለከታቸው የፌደራል ተቋማትና የክልል አቻዎቻቸው መካተታቸው የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

- የስራ ስምሪት ውጤቶችን ለመለካት በየጊዜው አመልካቾችን ለማዘጋጀት እንዲያስችል እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የተሳሰረና መረጃን በሁለትዮሽ መንገድ የሚያመነጭ (ከታች ወደላይና ከላይ ወደታች) ከአገራዊ (PASDEP) የክትትልና ግምገማ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ስርዓት ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 3.4 የፖሊሲ ክለሳ

እንደማንኛውም ፖሊሲ የስራ ስምሪት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አዳዲስ ለውጦችን በመመርኮዝ ሊቀያየሩ/ሊለወጡና ሊሻሻሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ የኢኮኖሚው መዋቅር ሽግግርና የግሉ ሴክተር ልማት የስራ ስምሪትን ለማስፋፋት ወደሚያስችሉ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች ትኩረት ማዞር የፓሊሲ ክለሳን አስፈላጊ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የሚመጣ መደበኛ ያልሆነው የስራ ዘርፍ እየጠበበ መሄድ መደበኛ ላልሆነው ዘርፍ የሚሰጥ ትኩረት እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት የሚጠበቁ ለውጦችን በክትትልና ግምገማ በታዩ ውጤቶች ከተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች ጋር በመቀመር የፖሊሲ ክለሳ ሊደረግ ይችላል፡፡ በዚህም ዕይታ የመጀመሪያው የብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጂ መጽደቅንና ትግበራ መጀመርን ተከትሎ ከሶስት እስከ አራት ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ የፖሊሲ ክለሳ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ሁኔታዎች ሊያስገድዱ ይችላሉ፡፡ በሀገሪቱ (እንዲሁም በዓለም) ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አካባቢዎች የሚታዩ ሁኔታዎችና አዳዲስ ግኝቶች የስራ ስምሪት አቅም ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ ማገናዘቡ ጠቃሚ መሆኑ እንዳለ ሆኖ የፖሊሲ ክለሳው እንቅስቃሴ ከክትትልና ግምገማው የሚገኙ ውጤቶችን መነሻ ያደርጋል፡፡ የብሔራዊ የስራ ስምሪት ምክር ቤት ይህንን የፖሊሲ ክለሳ ሂደት የማስተባበር ኃላፊነት አለበት፡፡

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional